iBFAM

www.iBFAM.org

ፍሬያማና የምትበዛ ሁን



# በዕርቅ የተገነባ ኅብረት

## ትምህርት 1 የማዕዘን ድንጋይ

*“እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና።”*

ቆላ. 1:19-20

# ፍሬያማና የምትበዛ ሁን

**ተግባራዊ የደቀመዝሙርነት ሞዴል እና ሥርዓተ ትምህርት**

**የማዕዘን ድንጋይ ትምህርት ፡ ከ 1-4 የተዘጋጁ ጠቃሚ ትምህርቶች**

**አሳታሚ ፡** EveryHome for Christ

አድራሻ ፡
Every Home for Christ International
640 Chapel Hills Dr., Colorado Springs, CO 80920 USA
(719)-260-8888
BFAM@ehc.org
www.iBFAM.org

Copyright © 2011 by Every Home for Christ

ይህን የጥናት ማቴሪያል ከዚህ በታች በተገለጸው ደንብ መሠረት እንደገና ማባዛትና ማሰራጨት ይፈቀዳል፡፡

- አዘጋጁ “ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል ነው” በማለት ለደራሲው ተገቢውን ዋጋ በመስጠት፤
- ኤቭሪ ሆም ኢቫንጀሊዝም ይህን ማቴሪያል የትና እንዴት መጠቀም እንደሚገባ የሰጠውን ማሳሰቢያ ጠብቆ በመስራት፤
- ለማባዛት ከሚበዛ ወጪ በስተቀር ለሽያጭ ዓላማ ካልዋለ፡፡

አውዱን ጠብቆ የትርጉምና የማዛመድ ሥራ የሚከተሉትን ነጥቦች እንዲያካትት ይበረታታል፡፡

- ትርጉሙ በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል አስተባባሪነት በኩል ይሠራል፤
- የትርጉምና የጥቅስ አጠቃቀም የባለቤትነት መብት የኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ለመሆኑ እውቅና ለመስጠት ስምምነት ይደረጋል፤
- ማንኛውም ይዘቱን የተመለከተ ከአውዱ ጋር የሚዛመድ ሥራ በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት መጽደቅ ይኖርበታል፤
- የመጨረሻው በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የጸደቀው ቅጂ ለአርካይቭና ለሥርጭት ዓላማ ይቀመጣል፡፡ (ይህ ቅጂ በህትመት መልክና በዲጂታል ቅጂም ይቀመጣል)፡፡

የቢኤፍኤም ትምህርቶች፣ በደቀመዝሙርነት የማስተማር ዘዴ ላይ ያተኮሩ ሲሆን እያንዳንዱ ትምህርት ተገቢውን ጠቀሜታ አስገኝቶ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል፡፡ የቢኤፍኤምን የማስተማር ዘዴ የሚያስጨብጥ ሥልጠናን አግኝተህ ካልሆነ ወይንም ደግሞ የቢኤፍኤምን የሥልጠና መመሪያ ካላገኘህ፣ ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የሥልጠናውን ጊዜ እንዲያመቻችልህ እባክህን በአድራሻችን አግኘን፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከ1963 ዓ.ም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የተወሰደ ነው፡፡

አከፋፋይ ፡ ኤቭሪሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል

# የማዕዘን ድንጋይ

## ትምህርት አንድ — ማውጫ


መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------------- ገጽ 4

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማኝት ሂደት ------------------------------------------ ገጽ 6


## ትምህርቶች


**1.1 እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፈጣሪ** -------------------------------- ገጽ 8

እርሱ ሁሉን ፈጠረ

**1.2 ልዩ ተደርገው የተፈጠሩ ሰዎች** ------------------------------------------ ገጽ 9

ከእግዚአብሔር ጋርና እርስ በእርስም ልዩ ኅብረት እንዲኖራቸው ተደርገው የተፈጠሩ ሰዎች

**1.3 አታላዩ ሰይጣን** --------------------------------------------------------- ገጽ 10

እርሱ ሊሰርቅ፣ ሊያጠፋ፣ ሊገድል መጥቶአል

**1.4 አዳምና ሄዋን እግዚአብሔርን አልታዘዙም**----------------------------- ገጽ 12

በዚህ ጊዜ እኛ በእርግማን ሥር ነን

**1.5 የተመረጠው ቤተሰብ**------------------------------------------------------ ገጽ 12

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ያደረገው ልዩ ኅብረት

**1.6 እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው** ---------------------------------------- ገጽ 13

አብርሃም ለእግዚአብሔር ታዘዘ

**1.7 ከሞት በኋላ ሕይወት አለ** ------------------------------------------------ ገጽ 14

ከሞት በኋላ ያለው ሕይወት በገነት ወይም በሲኦል የሚሆን ነው፤

**1.8 ክርስቶስ ኢየሱስ**------------------------------------------------------------ ገጽ 15

ፍጹም እግዚአብሔርና ፍጹም ሰው

**1.9 እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያደረገው የእርቅ እቅድ** ------------------- ገጽ 16

ስለ ኃጢአት ቅጣትን መቀበልና ኅብረትን ማደስ

**1.10 ኢየሱስ ኃጢአትን ድል ነሣ** ------------------------------------------- ገጽ 17

የእርሱ ትንሣዔ ማን መሆኑን አስመሰከረ

**1.11 ለመዳን ምን ማድረግ አለብኝ**------------------------------------------ ገጽ 18

ማመን

**1.12 ለእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት ምላሽ እንስጥ** ------------------------ ገጽ 19

መናዘዝ

**1.13 እኔ የኢየሱስ ጓደኛ** ------------------------------------------------------ ገጽ 20

እኔ ትዕዛዛቱን በመፈጸም በፍቅሩ እኖራለሁ

**የደቀ መዝሙር ቡድኖችን ማግኘት** ------------------------------------------- ገጽ 21

# ፍሬያማና የምትበዛ ሁን

## መግቢያ

"የፍሬያማና የምትበዛ ሁን" (አፍራ ብዛ) የትምህርት ኮርሶች የደቀመዛሙርነት የማስተማሪያ ስልትና ሥርዓተ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች ከአንዱ እውነተኛ ሕያው እግዚአብሔር ጋር ልዩ የሆነ ኅብረት እንዳላቸው ለማስገንዘብ የተነደፈ ነው። የአፍራ ብዛ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች ከኢየሱስ ጋር ባላቸው ኅብረት የተትረፈረፈ ሕብረት ሊኖራቸው እንደሚችል ለማሳየት የተነደፈ ኮርስ ነው። ሰዎች እርስ በእርስ ኅብረት እንዲኖራቸው ተፈጥረዋል። ከዚህም በላይ፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው ተፈጥረዋል። የኃጢአት ውጤትም ሰዎች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት እንዲቋረጥ አድርጎአል። የተቋረጠው ይህ ኅብረት እኛ ሰዎች እርስ በእርሳችን ከተቋረጠው ተፈጥሮና ከእግዚአብሔር ጋር ውህደት እንዳይኖረን አድርጎአል።

በዚህም ምክንያት በዓለማችን ላይ ጦርነት፣ ረሃብ፣ ግድያ፣ ተላላፊ በሽታ፣ ሕመም፣ ፍርደ ገምድል መሪዎች፣ ፍትህ አልባ ማኅበረሰብም እንዲኖር ሆኖአል። ከኃጢአት የተነሳ ኅብረታችን ተቋርጧል። ኃጢአትን እንዴት እንደምናስወግድና እንዴትስ በተሃድሶ ኅብረትን መመሥረት እንደምንችል እስካልተረዳን ድረስ፣ መልካሙን ሕይወት ለመኖር ከሚያስችለን ሕይወት ርቀናል።

የምስራቹ ቃል እግዚአብሔር ከኃጢአት የመውጫያውን መንገድና፣ የተቋረጠውን ኅብረትም ለማደስ ኃላፊነት እንደወሰደ ያመላክተናል። የአፍራ ብዛ ኮርስ ትኩረትም ይህን ማመልከት ነው። አፍራ ብዛ ሰዎች በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የምሥራቹን ቃል እንዴት እንደሚያነቡና እንደሚገነዘቡ ለማስተማር ይፈልጋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በታማኝነት እውነትን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ቃል ገብቶላቸዋል:: ***"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል"*** (ማቴ. 7፡7-8)። የአፍራ ብዛ ኮርስ ሰዎች እንዴት እንደሚጠይቁ፣ እንደሚፈልጉና እንደሚያንኳኩ ያስተምራል። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንዴት እንደሚያነቡና እውነትን እንዴት እንደሚፈልጉም ያስተምራል። እውነቱም እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ኃላፊነትን እንዲወስድና ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ማደስ እንደሚፈልግ ያስተምራል።

የእግዚአብሔርን እውነት በታማኝነት ለሚፈልጉ ሁሉ፣ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እውነት ማግኘት ለሚፈልጉ፣ ለእነርሱ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ እርቅ እንዲሆንላቸው ቃል ኪዳን ተገብቶላቸዋል። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት ሲታረቅ ያን ጊዜ የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራሉ።

ይህ ኮርስ "ፍሬያማና የምትበዛ ሁን" የተባለበት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት የምንኖረው የመጀመሪያ ደረጃ፤ እግዚአብሔር ፍሬያማ ሕይወት እንድንኖር አድርጎ እንደፈጠረን ለማሳወቅ ነው። ፍሬያማው ሕይወት በመንፈሳዊነት ወደ መባዛት ሕይወትም ያመራል።

# የደቀመዛሙርት ቡድኖችን መምራት

በዚህ ጥናት መጨረሻ ላይ የአፍራ ብዛ ትናንሽ ቡድን ሞዴሎች ተካተዋል። ትናንሾቹ የደቀመዝሙር ሞዴሎች ቡድን፣ ትናንሽ የቡድን ስብሰባ በአፍራ ብዛ የደቀመዝሙር ሞዴልና ሥርዓተ ትምህርት በመጠቀም እንዴት እንደምንመራ ያሳየናል።

# ጠቃሚ የሆኑት ተከታታይ ትምህርቶች

በአፍራ ብዛ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የተካተቱት የመጀመሪያዎቹ 52 ተከታታይ የሆኑ ትምህርቶች ተከታታይ ጠቃሚ ትምህርቶች ይባላሉ። እነኚህ ተከታታይ ትምህርቶች በአራት ክፍለ ትምህርቶች የተመደቡና እያንዳንዳቸው 13 ትምህርቶችን የያዙ የአንድ ዓመት ጥናቶች ናቸው። እነኚህ ጠቃሚ ተከታታይ ትምህርቶች ልክ ቤትን በመገንባት መልክ የተዋቀሩ ናቸው። አራቱ የተለያዩ ክፍለ ትምህርቶችም የማዕዘን ድንጋይ፣ መሠረት፣ ግድግዳና ጣራን ያካትታሉ። ከዚህ በታች የእነኚህ አራት ትምህርቶች ይዘት ተብራርቷል።



## የማዕዘን ድንጋይ ክፍለ ትምህርት - የማስታረቅ ኅብረት

የማዕዘን ድንጋይ ክፍለ ትምህርቶች በማስታረቅ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። እግዚአብሔር እንዴት ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ከሚያስረዳው ፍጥረተ ትምህርትም ይጀምራል። ይህ እውነትም ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ንጽረተ ዓለም ያስጨብጠናል። ሁለተኛው ትምህርትም የሰው ልጅ ከሌላው ፍጥረት የተለየ ሆኖ እንደተፈጠረ ያስጨብጠናል። እኛ የተፈጠርነው ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ኅብረት እንዲኖረን ነው። ሦስተኛውና አራተኛው ትምህርትም የሰው ልጅ እንዴት በሰይጣን እንደተታለለ ያሳያል። የመጀመሪያው ሰው እግዚአብሔርን አልታዘዘም፤ በዚህም ምክንያት እኛ ሁላችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕብረት ተቋረጠ። የቀረው የትምህርቱ ክፍል እግዚአብሔር ይህን የተቋረጠ ኅብረት እንደገና ለማደስና የሰውን ልጅ ለመዋጀት የዘረጋውን የማስታረቅ ዕቅድ ያሳየናል።



## መሠረት የመጣል ክፍለ ትምህርት - ከክርስቶስ ጋር መዝለቅ

ይህ የትምህርት ክፍል መሠረት ያደረገው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዛት የመፈጸምን አስፈላጊነት ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር ***“ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።”*** (ማቴ. 7:24) መሠረት የመጣል ክፍለ ትምህርት በመታዘዝ የአኗኗር ዘዴ ውስጥ የሚገኘውን ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትን ያሳያል።



## የግድግዳ ክፍለ ትምህርት - የተትረፈረፈ ሕይወት

የአንድ ቤት ግድግዳ ከቤቱ ውጪ ያሉ ሰዎች ሁሉ በግልጽ የሚመለከቱት ነው። የክርስቶስ ተከታዮችም ልክ እንደዚሁ ናቸው። የክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔርን በምድር ላይ የሚወክሉ ናቸው። እነኝህ የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔር ተወካይ እንደመሆናቸው መጠን በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች እግዚአብሔርን በመምሰልና በድርጊታቸውም በመግለጽ የሚያሳዩ መሆን ይገባቸዋል። ይህ ክፍለ ትምህርት በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን ቤተሰቦች አስፈላጊነት ዓላማ ላይ ያተኩራል።




## የጣሪያ ክፍለ ትምህርት - ጠቃሚ እውነት

ይህ የመጨረሻ ክፍለ ትምህርት የክርስትናን እምነት መሠረታዊ እውነት ያካትታል። ጣራው ውጫዊ ወይም አላስፈላጊ የሆነውን ነገር እንድንከላከል ተደርጎ ተነድፎአል። የጣሪያ ክፍለ ትምህርት የሐሰት ትምህርትን ለመከላከል የክርስትናን እምነት መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በማሳየት የሐሰትን ትምህርት የመከላከል ንድፍ ነው።




***“እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።”*** ኤፌ. 2:19-22

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማኝት ሂደት




**የትምህርቱ ጭብጥ** - መሬቱን ማዘጋጀት

የትምህርቱ ጭብጥ ደቀመዝሙር ለሚሆኑት ሰዎች ዘር የሚዘራበትን አዕምሮና ልብን በማሳደግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገኘው እውነት እነርሱን ማዘጋጀት ነው።

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ** - ዘሩን መዝራት

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በለማው መሬት ውስጥ የሚዘራው ዘር ሲሆን ከተዘራ በኋላ የእውቀትና የአርነት ፍሬን የሚያፈራ ይሆናል።

**የመገንዘብ ሂደት** - ውኃና ማዳበሪያ

የግንዛቤ ሂደት ጥያቄዎች ዘሩን ውኃ እንደማጠጣትና ማዳበሪያ እንደመጠቀም ነው። የእግዚአብሔር ቃል፣ የታሪኩን እውነት ለመግለጥ ይረዳል።

**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት** - ማጣት / መግረዝ

ተጨማሪ የቃሉ ጥናት በታሪኩ ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚገነባ / አስተምህሮ እንዳይኖርም ይከላከላል።

**የተግባር ጥያቄዎችና መደምደሚያ** -

የተግባር ጥያቄዎችና መደምደሚያው በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ያለውን የአዝመራውን ውጤት ለመሰብሰብና በሕይወታችን ውስጥ የተረዳነውን እውነት እንድንተገብረው ይረዳናል።

# የትምህርቱ ቅደም ተከተል

## ደረጃ 1 - መሬቱን ማዘጋጀት *የትምህርቱ ጭብጥ*

## ደረጃ 2 - ዘር መዝራት *የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ*

## ደረጃ 3 - ውኃና ማዳበሪያ *የግኝት ሂደት*

### ታሪኩን ማወቅ - መጠየቅ

**ማን ነው? ተግባሩ ምንድን ነው? ታሪኩን በጥልቀት ማወቅ፤**

- በታሪኩ ውስጥ ያሉት ገጸ ባሕርያት እነማን ናቸው?
- የገጸ ባሕርያቱ ድርጊት ምንድን ናቸው?
- በታሪክ ውስጥ ያለው ግልጽ የሆነ ጥልቅ ጉዳይ ምንድን ነው?

### ታሪኩን መረዳት - መፈለግ

**ፍልቅ ስሜት፣ የመነሻ ምክንያትና ምርጫ**

- ገጸ ባሕርያቱ የተሰማቸው ፍልቅ ስሜት ምን ይመስላል;
- ገጸ ባሕርያቱን ለድርጊት ያነሳሳቸው መነሻ ምክንያት ምንድን ነው;
- ገጸ ባሕርያቱ የወሰዱአቸው ልዩ ልዩ ምርጫዎች ምንድን ናቸው?

### የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታን ማግኘት - ማንኳኳት

**ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤና ርምጃ**

- የገጸ ባሕርያቱን ድርጊት፣ ጥልቅ ጉዳይ፣ ፍልቅ ስሜት፣ መነሻ ምክንያትና ምርጫ በጥንቃቄ ስትመለከት ምን ትማራለህ?

## ደረጃ 4 - መግረዝ *ተጨማሪ የቃሉ ጥናት*

## ደረጃ 5 - መከሩን መሰብሰብ *የማዛመድ ጥያቄና መደምደሚያ*

***"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።"*** 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17

በታሪክ ውስጥ በተዳሰሰው ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳትና ተግባራዊነት መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ (ማስተማር)

- እኔ የተሳሳተ ግንዛቤና ድርጊት አለኝን; (ተግሳጽ)፤
- የተሳሳተ ግንዛቤዬንና ተግባሬን እንዴት ማስተካከል እችላለሁ (ማቅናት)፤
- እንዴት ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታና ግንዛቤ ጨብጬ መጓዝ እችላለሁ? (ሥልጠና)

# እግዚአብሔር - የሰማይና የምድር ፈጣሪ

## እርሱ ሁሉን ፈጠረ

ትምህርት **1-1**

## የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ። እርሱ ሁሉን ያውቃል፣ ታላቅ ኃይል አለው፣ በየትኛውም ቦታ ይገኛል፣ በየትም ቦታ ይኖራል፣ ከባዶ ነገር ተነስቶ ሁሉን ፈጠረ። የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ዓለማትን ሁሉ ፈጥሮአል። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እጅግ መልካም አድርጎ ፈጥሮአል፤ ምክንያቱም አርሱ ፍጹም አምላክ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፥ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ፥ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው።"*** ኤር. 51፡15

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

***የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡***

ከሁሉም በመጀመሪያ እግዚአብሔር ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ በስድስት ቀን እንደፈጠረ ይነግረናል። በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት እግዚአብሔር ብርሃን፣ ፀሐይን፣ ጨረቃን፣ ከዋክብትን፣ ሰማይን፣ ውሃና መሬትን ፈጠረ። እንዲሁም አትክልቶችንና በባሕር ያሉትን ሁሉንም አይነት እንስሳትንና የሰማይ አዕዋፋትን፣ እርስ በእርስ እንዲዋለዱ አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ከተመለከተም በኋላ ሁሉም መልካም እንደሆነ አወጀ፤ የእኛም ታሪክ በስድስተኛው ቀን ጀመረ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"እግዚአብሔርም አለ፦ ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፥ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ፥ ታውጣ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፥ እንስሳውንም እንደ ወገኑ፥ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።"*** ዘፍ. 1፡24-28

## የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

## ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ቆላ. 1፡16፤ ራዕ. 4፡11፤ መዝ. 33፡6-9፤ ኢሳ. 40፡21-28፤ ዕብ. 11፡3)

**የማዛመድ ጥያቄዎች** - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - ዓለማትንና በውስጡ ያሉት ሁሉ በድንገተኛ አጋጣሚ የመጡ አይደሉም። አንድ ፈጣሪ አላቸው፤ እርሱም እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉም ፍጹም ነው።

# በአፈጣጠሩ ልዩ የሆነው ሕዝብ

ትምህርት 1-2

**ከእግዚአብሔር ጋርና እርስ በእርስም ልዩ ኅብረት እንዲኖረው ተደርጎ የተፈጠረ ፍጡር፤**

## የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማለስለስ*

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ከእንስሳት በጣም እንዲለይ አድርጎ ነው። ሰዎች የተፈጠሩት የእግዚአብሔር ባሕርይ እንዲያንጸባርቁ ነው። እግዚአብሔር ሰው ከእርሱ ጋር ልዩ ሕብረት እንዲኖረው አድርጎ ሰርቶታል። እግዚአብሔር ሰውን ረዳት አድርጎ ፈጥሮታል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች።"*** *መዝ.* 139፡14

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

*መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን እንደፈጠረና በእነርሱም ውስጥ ፍጥረት እንደሚገኝና እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ "መልካም" መሆኑን እንዳወጀ ይገልጽልናል።*

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።" . . . "እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት። እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ፤ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው፤ አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ያው ሆነ። አዳምም ለእንስሳት ሁሉ፥ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፥ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው፤ ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር። እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም፤ ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት።"*** ዘፍ. 2፡7፣ 18-22

## የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

## ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(*መዝ.* 24፡1፣ *መዝ.* 100፡3፣ *መዝ.* 139፡13-16፤ ኤፌ. 5፡28፣ 31፤ ሮሜ 8፡38-39)

## የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** **-** እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ በልዩ መንገድ ፈጠራቸው፤ ሁለቱም እኩል ናቸው። እነርሱ እርስ በእርስ ኅብረት እንዲኖራቸው ተደርገው ተፈጥረዋል። ከእግዚአብሔርም ጋርም ኅብረት እንዲኖራቸው ተደርገው ተሰርተዋል።

# አሳቹ ሰይጣን

ትምህርት 1-3

## እርሱ ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ይመጣል፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ሰይጣን ክፉ ጠላት ነው፡፡ ያለመታከት ይዋጋናል፡፡ ሰይጣን እግዚአብሔርንና እርሱ ፍጹም አድርጎ የፈጠረውን ፍጥረት ይጠላል፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጹም ፍጥረት ሰይጣን ስለጠላ፣ አጥፊ ሆኖ ወደ ምድር በመምጣት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ልዩ ኅብረት ለማጥፋት መጣ፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ፡፡"*** ዮሐ. 10፡10

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

እግዚአብሔር፡- አዳምና ሔዋንን ውብ በሆነ ለምለም ስፍራ እንዲኖሩ አደረገ፡፡ እግዚአብሔር ሰውን በአትክልቱ ስፍራ ከአንዲት ዛፍ ፍሬ በቀር የወደደውን ዛፍ ፍሬ እንዲበላ ነገረው፡፡ እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፤ ***"ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፣ ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፣ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞት ትሞታለህና፤"*** አንድ ቀን ሰይጣን በከፍተኛ ጥላቻ በእባብ ተመስሎ ወደ እነርሱ መጣና ሔዋንን አሳታት፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ፡፡ ሴቲቱንም፡፡ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት፡፡ ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፡- በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፡- እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም፡፡ እባብም ለሴቲቱ አላት፡- ሞትን አትሞቱም፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ፡፡ ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ፡፡" "እግዚአብሔር አምላክም ሴቲቱን፡- ይህ ያደረግሽው ምንድር ነው? አላት፡፡ ሴቲቱም አለች፡- እባብ አሳተኝና በላሁ፡፡ እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፡- ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፤ በሆድህም ትሄዳለህ፥ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ፡፡ በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ፡፡"***
>
> ዘፍ. 3፡1-6፣ 13-15

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማር. 1፡9-13፤ 2 ተሰ. 2፡8-10፤ ራዕ. 12፡9፤ 1 ጴጥ. 5፡8)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

***መደምደሚያ*** - የሰይጣን ክፉ የሆነው ፍላጎቱ እግዚአብሔርን መቃወምና የእግዚአብሔርን እቅድ ማፍረስ ነዳው፡፡ የሰይጣን የክፋት ተግባር ሔዋንን በመፈተን ተጀመረ፡፡ ሰይጣን ሔዋንን ለእግዚአብሔር እንዳትታዘዝ በማድረግ ጀመረ፡፡ ሰይጣን የሰው ልጆችንና፣ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ልዩ ኅብረት ይጠላል፡፡

# አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን አልታዘዙም

ትምህርት 1-4

### እኛ አሁን በእርግማን ሥር ነን፤

## የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ሰይጣን ሔዋን ለእግዚአብሔር እንዳትታዘዝ አሳታት። እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቀጣል። የአዳምና የሔዋን አለመታዘዝ የመጨረሻ ውጤቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ኅብረት ማቋረጡ ነበር። የኃጢአት የመጨረሻ ውጤቱ ህመም፣ ሥቃይና ሞት ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤. . ."*** ሮሜ. 5:12

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠራቸው ወንድና ሴት አዳምና ሔዋን ይባሉ ነበር። በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሰችው ዛፍ ክፉና ደጉን የምታስታውቅ ዛፍ በመባል ትታወቃለች። እግዚአብሔር ከዚች ዛፍ በስተቀር ከሌላ ማንኛውም ዛፍ መብላት ትችላላችሁ በሚል ተናግሮ ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ። የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፥ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ። እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ። እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው። እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም። እግዚአብሔርም አለው፦ ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን? አዳምም አለ፦ ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ። እግዚአብሔር አምላክም ሴቲቱን፦ ይህ ያደረግሽው ምንድር ነው? አላት። ሴቲቱም አለች፦ እባብ አሳተኝና በላሁ።" ለሴቲቱም አለ፦ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል። አዳምንም አለው፦ የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና።"*** ዘፍ. 3፡6-13፣ 16-19

## የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

## ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ያዕ. 1፡13-15፤ ኢሳ. 59፡2፤ ሮሜ 3፡23፤ ሮሜ 6፡23፤ 1 ዮሐ. 3፡5)

## የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - እግዚአብሔርን መጠራጠርና አለመታዘዝ ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ያበላሻል። ፍጹም የሆነው እግዚአብሔር አምላክ ኃጢአትን መታገስ አይችልም። ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው። የኃጢአት ውጤትም ሕመም፣ ሥቃይና ሞት ነው።

# የተመረጠው ቤተሰብ

ትምህርት 1-5

## እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ያደረገው ልዩ ኅብረት

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

የአዳምና ሔዋን የኃጢአት ውጤት ወደ ሰዎች ሁሉ ተላለፈ፡፡ እግዚአብሔርም ከሰው ልጅ ጋር ኅብረቱን ለማደስ እቅድ አወጣ፡፡ እግዚአብሔር አብርሃም ከተባለ ሰው ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ እግዚአብሔር በአብርሃም ቤተሰብ አማካኝነት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚታረቁ ቃል ኪዳን አደረገ፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"እግዚአብሔርም አብራምን አለው፡- ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።"* ዘፍ. 12፡1-3

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

አብርሃም እግዚአብሔር ሲናገረው የታዘዘ ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔር የአብርሃምን ቤተሰብ በመምረጥ የሰይጣንን ሥራ በማፍረስ የሰው ልጆችን ሁሉ ለመባረክ ወደደ፡፡ አብርሃም እግዚአብሔር ከሚስቱ ልጅ እንደሚሰጠው አላመነም ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ አብርሃም የእግዚአብሔርን መንገድ ሳይሆን የራሱን መንገድ ሄደ፡፡ አብረሃምና ሚስቱ ልጅ ስላልነበራቸው አብርሃም ከሚስቱ ሠራተኛ ልጅ አገኘ፡፡ ይህ ልጅ እስማኤል ይባላል፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

*"አብራምም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና፤ እኔ ኤልሻዳይ ነኝ፤ በፊቴ ተመላለስ፥ ፍጹምም ሁን፤ ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ፥ እጅግም አበዛሃለሁ አለው። አብራምም በግምባሩ ወደቀ፤ እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- እነሆ፥ ቃል ኪዳኔ ከአንተ ጋር ነው፤ ለብዙ አሕዛብም አባት ትሆናለህ። ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና። እጅግም አበዛሃለሁ፥ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ። ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ፥ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ አምላክ እሆን ዘንድ።" . . . "እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፡- የሚስትህን የሦራን ስም ሦራ ብለህ አትጥራ፥ ስምዋ ሣራ ይሆናል እንጂ። እባርካታለሁ፥ ደግሞም ከእርስዋ ልጅ እሰጥሃለሁ፤ እባርካትማለሁ፥ የአሕዛብም እናት ትሆናለች፤ የአሕዛብ ነገሥታት ከእርስዋ ይወጣሉ። አብርሃምም በግምባሩ ወደቀ፥ ሳቀም፥ በልቡም አለ። የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ ትወልዳለችን? አብርሃምም እግዚአብሔርን፡- እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር አለው። እግዚአብሔርም አለ፡- በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ።"* ዘፍ. 17፡1-7፤ 15-19

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ዘፍ. 15፡1-6፤ *ዕብ.* 11፡8-12፤ *ገላ.* 3፡16-18፤ ኢሳ. 51፡1-2፤ *ያዕ.* 2፡23)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ *ገጽ* 7 ተመልከት)፡፡

***መደምደሚያ*** - እግዚአብሔር ሰውን ከእርሱ ከራሱ ጋር የማስታረቅ ሥራ የጀመረው በአብርሃም ነው፡፡ እግዚአብሔር በአብርሃም ቤተሰብ አማካኝነት ምድር ሁሉ እንደምትባረክ ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአተኞች አንድ ቀን በአብርሃም ቤተሰብ አማካኝነት ከኃጢአት መንጻትን እንደሚያገኙ ቃል ኪዳን ገባ፡፡

# እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው

ትምህርት 1-6

## አብርሃም እግዚአብሔርን ታዘዘ፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት የተስፋ ቃል ኪዳን ሁሉ በይስሃቅ በሕይወት መኖር ላይ የተመሰረተ ነው። አብርሃም በእግዚአብሔር ተፈተነ። አብርሃም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ታዘዘ። አብርሃም እግዚአብሔር እንደማይዋሽ በመታመን ኖረ።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"አብርሃም በተፈተነበት ጊዜ ይስሐቅን በእምነት አቀረበ፥ የተስፋን ቃል የተቀበለው። በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል የተባለለት እርሱም አንድ ልጁን አቀረበ፤ እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው እንዲቻለው አስቦአልና፥ ከዚያም ደግሞ በምሳሌ አገኘው።"*** ዕብ. 11፡17-19

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

በቀደሙት ዘመናት እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት የደም መሥዋዕት እንዲቀርብ አድርጎ ነበር። መሥዋዕትን ማቅረብም ሃይማኖታዊ የመንጻት ሥርዓት ነበር፤ የአምልኮ ሥርዓትም ነበረ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ። አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ፥ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፥ እንጨትንም ለመሥዋዕት ሰነጠቀ፤ ተነሥቶም እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ። በሦስተኛውም ቀን አብርሃም ዓይኑን አነሣና ቦታውን ከሩቅ አየ። አብርሃምም ሎሌዎቹን አላቸው፦ አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ፤ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን፥ ወደ እናንተም እንመለሳለን። አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤ እርሱም እሳቱንና ቢላዋውን በእጁ ያዘ፥ ሁለቱም አብረው ሄዱ። ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ተናገረው፤ አባቴ ሆይ አለ፦ እርሱም እነሆኝ ልጄ አለው። እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤ የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው? አለ። አብርሃምም ልጄ ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው፤ ሁለቱም አብረው ሄዱ። እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ፤ አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ፥ እንጨትንም ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው። አብርሃምም እጁን ዘረጋ፥ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ። የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ ጠራና፤ አብርሃም አብርሃም አለው። እርሱም እነሆኝ አለ። እርሱም፦ በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ። አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።"*** ዘፍ. 22፡2-13

### የግኘት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሮሜ 4፡1-24፤ *ያዕ.* 2፡21-22፤ ዘፍ. 22፡15-18)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - አብርሃም ልጁን ይስሃቅን ለመሥዋዕትነት ማቅረቡ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ያሳያል። አብርሃም እግዚአብሔርን ታዘዘ። አብርሃም በእግዚአብሔር በተፈተነ ጊዜ እርሱ በእግዚአብሔር በመታመን ታዘዘ። የአብርሃም ታሪክ ከተፈጸመ ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ መሥዋዕት የሚሆነው ፍጹም የሆነና አንድ ጊዜ መሥዋዕት የሆነውን አቀረበ።

# ከሞት በኋላ ሕይወት አለ

**ትምህርት 1-7**

## አብርሃም እግዚአብሔርን ታዘዘ፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ቃሉ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ያስተምረናል፡፡ ከሞት በኋላ ሰዎች ሁሉ ወደ መንግስተ ሰማያት ወይም ወደ ሲዖል ይሄዳሉ፡፡ መንግሥተ ሰማያት እግዚአብሔር የሚገኝበት በመሆኑ ብዙ ደስታ አለበት፡፡ ሲዖል ደግሞ የመጨረሻው የክፉ ቅጣት የሚፈጸምበት ነው፡፡ በሲዖል ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከእግዚአብሔር ይለያሉ፡፡ እግዚአብሔር በሁሉም ሰው ላይ ፍርዱን ይሰጣል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው፡፡"*** **ሮሜ 6:23**

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ለማስተማር ምሳሌዎችን ይጠቀማል፡፡ ምሳሌዎቹ ጥልቅ ትርጉም ያላቸው ታሪኮች ናቸው፡፡ በእነኚህ ታሪኮች ውስጥ "የሰው ልጅ" የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ስም ነው፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፦ መንግሥተ ሰማያት በእርሻው መልካም ዘርን የዘራን ሰው ትመስላለች፡፡ ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ፡፡ ስንዴውም በበቀለና በአፈራ ጊዜ እንክርዳዱ ደግሞ ያን ጊዜ ታየ፡፡ የባለቤቱም ባሮች ቀርበው፡፡ ጌታ ሆይ፥ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ? አሉት፡፡ እርሱም፦ ጠላት ይህን አደረገ አላቸው፡፡ ባሮቹም፦ እንግዲህ ሄደን ብንለቅመው ትወዳለህን? አሉት፡፡ እርሱ ግን፦ እንክርዳዱን ስትለቅሙ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉት አይሆንም፡፡ ተዉአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜም አጫጆችን እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ፥ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ፡፡" "እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤ እርሻውም ዓለም ነው፤ መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤ እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፥ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፥ አጫጆችም መላእክት ናቸው፡፡ እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፥ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፡፡ የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፡፡ በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ፡፡ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ፡፡"*** ማቴ. 13:24-30፣ 37-43

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ራዕ. 20:12-15፣ ራዕ. 21:22፤ 1ተሰ. 4:13-18፤ ዮሐ. 14:1-3፤ ፊሊ. 3:20፤ ማቴ. 13:47-50፤ ማቴ. 25:31-46፤ ማር. 9:47-48፤ ዕብ. 9:27)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

***መደምደሚያ*** **-** እግዚአብሔር ከሞት በኋላ በሁሉም ሰው ላይ ፍርዱን ይሰጣል፡፡ መንግስተ ሰማይ ሙሉ የሆነ ሕይወትና ደስታ የሞላበት ቦታ ነው፡፡ ሲዖልም ሐዘንና ሥቃይ የሞላበት ቦታ ነው፡፡

# ኢየሱስ ክርስቶስ

ትምህርት
1-8

## ፍጹምእግዚአብሔርና ፍጹም ሰው ነው፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር የነበረውን መልካም ኅብረት እንደገና ለመመለስ ሲል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ እንደገና የመታደስ እቅድ ዘርግቶአል። የእቅዱ ጊዜ ሲደርስም አንድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ከእግዚአብሔር እንዲያስታርቅ ወደ ምድር ላከው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።"*** ኢሳ. 7፡14

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ በአብርሃም አማካኝነት ከዳዊት ዘር እንደሚመጣ ይነግረናል።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። በነቢይ ከጌታ ዘንድ፦ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው። ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ እጮኛውንም ወሰደ፤ የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው።"*** ማቴ. 1፡18-25

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማቴ. 16፡13-20፣ ማቴ. 26፡63-64፤ ሉቃ. 1፡28-35፤ ዮሐ. 1፡1-14፣ ዮሐ. 3፡16፤ ፊሊ. 2፡5-11፤ ቆላ. 1፡15-20፣ ቆላ. 2፡9)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** **-** ጌታ ኢየሱስ ፍጹም እግዚአብሔርና ፍጹም ሰው ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውና በእግዚአብሔር መሃከል የተቋረጠውን ግንኙነት ለማደስ ተልኳል።

# ለሰው ልጅ እግዚአብሔር ያዘጋጀው የማስታረቅ እቅድ

ትምህርት 1-9

## ስለ ኃጢአት የሚከፈለውን ቅጣት በመቀበል ኅብረትን ማደስ

## የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ይወዳል። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር በመልካም ፍቅርና ኅብረት እንዲኖሩ ተፈጥረዋል። ሰይጣን አዳምና ሔዋን ለእግዚአብሔር እንዳይታዘዙ አሳመጻቸው። እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ኃጢአት ነው። ኃጢአት በእግዚአብሔርና በሰው መሃከል የነበረውን ፍጹም ኅብረት አበላሸው። እግዚአብሔር በሰውና በእርሱ መሃከል የፈረሰው ፍጹም ኅብረት እንደገና እንደሚገነባ ለሰው ልጅ ቃል ገባ። እግዚአብሔር አንድ ቀን አንድ ሰው ከአዳም ትውልድ ውስጥ ወጥቶ የሰይጣንን አናት እንደሚቀጠቅጥ ለአዳም ቃል ኪዳን ገባለት። እግዚአብሔር በአብርሃም ዘር አማካኝነት የምድርን ፍጥረት ሁሉ እንደሚባርክም ቃል ገባ። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስ በመላክ ይህን ቃል ኪዳኑን ፈጸመው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና።"*** **ሮሜ** 5፡6

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

### የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።

እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ላከ። የእርሱም ስም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አወላለዱም ተዓምራዊ ነው። እርሱ ፍጹም እግዚአብሔርና ፍጹም ሰውም ነው። እርሱ በምድር ላይ በተመላለሰበት እድሜው ሁሉ አንዴም ኃጢአትን አላደረገም። እርሱ በርካታ ተዓምራቶችንና ጥበብን የተሞሉ ትምህርቶችንም አስተማረ። በርካታ የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን አይወዱትም ነበር፤ እንዲያውም ሊገድሉት ወስነው ነበር። የመንግሥት ባለሥልጣን የሆነ ገዢም ኢየሱስን ጠይቆት ንጽሕናውን አረጋግጦት ነበር። ይህ ገዢ ሕዝቡን ለማስደሰት ሲል ኢየሱስን እንዲወግሩትና በመስቀል ላይ እንዲሰቅሉት ፈቀደላቸው። መስቀል ሰዎች ተሰቃይተው የሚሞቱበት መግደያ ነው። እግዚአብሔር ልጁ ይህን ሁሉ ስቃይ መቀበሉ ስለ እያንዳንዳችን ኃጢአት እንደሆነ ይገልጻል።

### *የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤*

*"በዚያን ጊዜ የገዢው ወታደሮች ኢየሱስን ወደ ገዢው ግቢ ውስጥ ወሰዱት ጭፍራውንም ሁሉ ወደ እርሱ አከማቹ። ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት፥ ከእሾህም አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ፥ በቀኝ እጁም መቃ አኖሩ፥ በፊቱም ተንበርክከው፦ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ ዘበቱበት፤ ተፉበትም መቃውንም ይዘው ራሱን መቱት። ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፥ ልብሱንም አለበሱት ሊሰቅሉትም ወሰዱት። ሲወጡም ስምዖን የተባለው የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት። ትርጓሜው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሆን ጎልጎታ ወደሚባለው ስፍራ በደረሱ ጊዜም፥ በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፤ ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም። ከሰቀሉትም በኋላ ልብሱን ዕጣ ጥለው ተካፈሉ፥ በዚያም ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር። ይህ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው የሚል የክሱን ጽሕፈት ከራሱ በላይ አኖሩ። በዚያን ጊዜ ሁለት ወንበዶች አንዱ በቀኝ አንዱም በግራ ከእርሱ ጋር ተሰቀሉ።" "ከስድስት ሰዓትም ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም፦ አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው። በዚያም ከቆሙት ሰዎች ሰምተው፦ ይህስ ኤልያስን ይጠራል አሉ። ወዲያውም ከእነርሱ አንዱ ሮጠ፤ ሰፍነግም ይዞ ሆምጣጤ ሞላበት፥ በመቃም አድርጎ አጠጣው። ሌሎቹ ግን፦ ተው፥ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደ ሆን እንይ አሉ። ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ።"* ማቴ. 27፡27-38፤ 45-50

## የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

## ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ጢሞ.1፡15፤ 1 ጴጥ. 2፡24፤ ማር. 10፡45፤ ኤፌ. 1፡7፤ ዮሐ. 1፡29፤ ኢሳ. 53፡5-6)

## የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት የሰው ልጆች ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ኅብረት እንዲመሰርቱ መንገዱን አዘጋጅቶአል። ጌታ ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለኃጢአታችን ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት አቀረበ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ፈንታ ቦታውን ያዘ። እኛ ግን ይህን ልዩ ሥጦታ ከበሬታ አልሰጠነውም። ይህ ልዩ ሥጦታ ለኛ የሚገባንም አይደለም። እግዚአብሔር ግን ሰዎችን ሁሉ ስለሚወድ ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ሰጠን። በኢየሱስ የሚያምኑና በክርስቶስ ኢየሱስ የተደረገውን ሥጦታ የተቀበሉ ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ ናቸው።

# እየሱስ ሞትን ድል ነሣ!
# ፈተነው

ትምህርት 1-10

## ትንሣኤው የእርሱን ማንነት አሳየ

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ፣ ስለ ኃጢአታችን እንደሚሞትና ከሞትም እንደሚነሳ ተናግሮ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ እንደገና ከሞት ተነስቶአል። እርሱ ከሞት በተነሳ ጊዜ በእርግጥም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ተረጋግጦአል። እርሱ ያላቸው ነገሮችና ትዕዛዛቱም እውነት ሆኑ።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፦ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፥ . ."*** 1ኛ ቆሮ. 15፡3-4

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

***የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።***

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ጥቂት ወዳጆቹ በድኑን ወስደው ነበር። ኢየሱስንም በድንጋይ በተዋቀረ መቃብር ውስጥ ቀበሩት። የሃገሩ ገዢም የመቃብሩ በር በግዙፍ ድንጋይ እንዲዘጋ አዘዘ። ሰዎችም ከፍተው አስክሬኑን እንዳይሰርቁት ወታደሮች ይጠብቁት ነበር። ከሞተ ከሦስት ቀናት በኋላ ሁለት ሴቶች ወደ መቃብሩ ደጃፍ መጡ። የመቃብሩ መዝጊያ ድንጋይ ተንከባሎ ሁለት መላዕክትም ተቀምጠውበት አገኙ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፦ እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤ እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ። ፈጥናችሁም ሂዱና፦ ከሙታን ተነሣ፥ እነሆም፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው። እነሆም፥ ነገርኋችሁ፤ በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፥ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ።"*** ማቴ. 28፡5-8

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ቆሮ. 15፡12-22፤ ሮሜ 1፡3-4፣ ሮሜ 8፡33-34፤ ሐዋ. ሥራ 2፡22-24፤ 1 ጴጥ. 1፡3)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - ኢየሱስ ከሞት ተነሳ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን ሞት ሊይዘው አልቻለም። ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነው። እርሱ ስለ ኃጢአት የተሰጠ ፍጹም ሥጦታ ነው። ጌታ ኢየሱስ የነፍስ አምላክ ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም መምህር ወይም ነብይ ብቻ አልነበረም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ሁሉና ኃይልም እንዳለው አስመሰከረ። ጌታ ኢየሱስ የምድር ገገር መሆኑንም አስረገጠ።

# ለመዳን ምን ማድረግ አለብኝ?

ትምህርት 1-11

## ማመን

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ሞቶ በመነሳቱ ሰዎች ሁሉ ሕይወትን አግኝተዋል። ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በማመን በክርስቶስ ኢየሱስ እምነት እንዲኖራቸው ተጠርተዋል። ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን በማመንና እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን በአንደበታቸው በመመስከርና በመናዘዝ ከኃጢአት ቅጣት ሊድኑ ይችላሉ። በእግዚአብሔር አምኖ መዳን ወይም እርሱን ያለመቀበል ምርጫ ለሰዎች ሁሉ ተሰጥቶአቸዋል። የእግዚአብሔር ፍላጎት ግን ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።"* ዮሐ. 3:16-17

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ጌታ ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ታያቸው። ከጌታ ደቀ መዛሙርት አንዱ የሆነው ቶማስ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጽ እርሱ አልነበረም። ቶማስ ጌታ ከተሰቀለ በኋላ ዳግመኛ አልተመለከተውም። አንድ ነገር ሳናይ እውነት እንደሆነ ተቀብለን ማመን ወይም መስማማት እምነት ይባላል።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

*"ነገር ግን ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም። ሌሎቹም ደቀ መዛሙርቱ ጌታን አይተነዋል አሉት። እርሱ ግን የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው። ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፦ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ከዚያም በኋላ ቶማስን፦ ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። ቶማስም፦ ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው። ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።"* ዮሐ. 20:24-31

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ኤፌ. 2:8-9፤ ገላ. 2:20፣ ገላ. 3፤ ሐዋ. *ሥራ* 10:43፣ ሐዋ. 16:25-31፤ ዕብ. 11፤ ሮሜ 6:23፣ ሮሜ 10:9-10፤ ዮሐ. 3:16-21)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17) ገጽ ተመልከት።

**መደምደሚያ** - ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት ቅጣትን ተቀበለ። ቃሉ፣ ሰዎች እግዚአብሔር እርሱን ከሞት እንዳስነሳው ቢያምኑ የዘላለም ሕይወት እንደሚኖራቸው ይናገራል። ያለ እምነት ክርስቲያን ነኝ ብሎ ማለት የማይቻል ነው። እምነት ማለት ያለ እይታ በኢየሱስ ማመንና በእርሱ መደገፍ ነው። እምነት ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን በሞት ሞትን ድል እንዳደረገ ማመን ነው።

# ለእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት ምላሽ እንሰጣለን?

ትምህርት 1-12

**መናዘዝ**

## የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

መናዘዝ ማለት የልብና የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። መናዘዝ ማለት ስለ ኃጢአትና ስለ እግዚአብሔር የነበረንን የቀድሞ አስተሳሰብና ድርጊት መለወጥ ነው። መናዘዝ ማለት እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላ ሁሉ እኛም ኃጢአትን መጥላት ነው። የመናዘዝ ውጤቱ የኃጢአተኛነት ባሕርይን በመቀየር ይገለጻል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤. . ."*** **ሐዋ. 17፡30**

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ጌታ ኢየሱስ ታላቅ መምህር ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ታላላቅ ተአምራቶችንና ፈውስ ያደረገ ነው። ኢየሱስ በሄደበት ቦታ ሁሉ ብዙ ሕዝብ ያጨናንቁትም ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ወደ ኢያሪኮም ገብቶ ያልፍ ነበር። እነሆም ዘኬዎስ የሚባል ሰው፥ እርሱም የቀራጮች አለቃ ነበረ፥ ባለ ጠጋም ነበረ። ኢየሱስንም የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱም አጭር ነበረና ስለ ሕዝቡ ብዛት አቃተው። በዚያችም መንገድ ያልፍ ዘንድ አለውና ያየው ዘንድ ወደ ፊት ሮጦ በአንድ ሾላ ላይ ወጣ። ኢየሱስም ወደዚያ ስፍራ በደረሰ ጊዜ፥ አሻቅቦ አየና፦ ዘኬዎስ ሆይ፥ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው። ፈጥኖም ወረደ በደስታም ተቀበለው። ሁሉም አይተው ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ ብለው አንጐራጐሩ። ዘኬዎስ ግን ቆሞ ጌታን፦ ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኵሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ አለው። ኢየሱስም፦ እርሱ ደግሞ የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፤ የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።"*** **ሉቃ. 19፡1,10**

## የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

## ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሐዋ. 2፡31-41፤ ሐዋ. 3፡19-20፤ ማቴ. 3፡2፣ ማቴ. 4፡17፤ ማር. 1፡15፤ ሉቃ. 5፡32፣ ሉቃ. 13፡15)

## የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17 ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - በጌታ ኢየሱስ ላይ ያለን እምነት ኃጢአታችንን ወደ መናዘዝ ይመራናል። ኃጢአታችንን በምንናዘዝበት ጊዜ ልባችንን አዕምሮአችን፣ ድርጊታችንም ይቀየራል። በኢየሱስ ያመኑና የተደገፉበት ሁሉ በአካባቢያቸው ካሉ በኢየሱስ ከማያምኑና በእርሱ ከማይደገፉ ሰዎች አኗኗራቸው የተለየ ነው።

# እኔ የኢየሱስ ወዳጅ ነኝ

**ትምህርት 1-13**

## ለእርሱ ሕግጋት በመታዘዝ በፍቅሩ ውስጥ እኖራለሁ፡፡

**የትምህርቱ ጭብጥ -** *መሬቱን ማዘጋጀት*

የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን ሁሉ የእርሱም ወዳጆች ነን፡፡ የእግዚአብሔር ወዳጆች እርሱን በልዩ መንገድ ያውቃሉ፡፡ የእግዚአብሔር ወዳጆች እርሱን ይወዳሉ፤ ሌሎችንም ይወዳሉ፡፡ የእግዚአብሔር ወዳጆች በእግዚአብሔር ትዕዛዛት ይታመናሉ፤ ሕጎቹንም ይታዘዛሉ፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኛማል፤ . . ."*** ዮሐ. 10፡27

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ** - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

ጌታ ኢየሱስ ለሐዋርያት መመሪያ እንደሰጣቸው ነገራቸው፡፡ ለእርሱ የሚነግረውም እግዚአብሔር አባቱ እንደሆነ ተናገረ፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ፊልጶስ፡- ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው፡፡ ኢየሱስም አለው፡- አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ?" . . . "አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ፡፡ እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ፡፡ ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ፡፡ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት፡፡ ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም፡፡ እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና፡፡"*** ዮሐ. 14፡8-9፤ 15፡9-15

**የግኝት ሂደት -** *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት -** *መግረዝ*

(ማቴ. 7፡16-20፤ 2 ጴጥ.1፡3-8፤ ዮሐ. 14፡15-23፤ 1 ዮሐ. 4፡7-8፣ 1 ዮሐ. 5፡1-5፤ ቆላ. 1፡10)

**የማዛመድ ጥያቄዎች -** *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17) ገጽ ተመልከት፡፡

***መደምደሚያ*** **-** የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን፤ የእግዚአብሔር ወዳጆች ነን፡፡ የእግዚአብሔር ወዳጆች እንደመሆናችን የእርሱን ድምጽ በመስማት መታዘዝ ይገባናል፡፡ የእግዚአብሔር ወዳጆች እንደመሆናችን ልክ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደወደደን ሌሎችን ለመውደድ ተጠርተናል፡፡

# የደቀመዝሙር ቡድንን መምራት

## አምልኮና ጸሎት

- እግዚአብሔር በስብሰባው መሃል እንዲሆን በጸሎትና በአምልኮ ጋብዙት፤
- ምስጋናን ለማቅረብና ለምስክርነት ጊዜ መድቡ፡፡

## የትምህርቱ ግኝትና የማዛመድ ጊዜ

### ደረጃ 1 - የትምህርቱ ጭብጥ

- ከቡድኑ ጋር የትምህርቱን ጭብጥና የቁልፍ ቃሉን ሃሳብ ተከፋፈሉ፡፡

### ደረጃ 2 - የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

- የመግቢያውን ነጥብና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን ሃሳብ ከቡድኑ ጋር ተከፋፈሉ፡፡

### ደረጃ 3 - የግኝት ሂደት

- ታሪኩን እወቁት፣
- ታሪኩን ተረዱት፣
- የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ጨብጡ፡፡

### ደረጃ 4 - ተጨማሪ የቃሉ ጥናት

- ቡድኑ ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንዳገኘ ለማወቅ ተገቢው መጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ተግባራዊ ርምጃ መኖሩን ፈትሹ፡፡

### ደረጃ 5 - ማዛመድና መደምደሚያ

ከታሪኩ በተገኘው ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤና ተግባራዊ ርምጃ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ፡፡ (ማስተማር)

- እኔ የተሳሳተ ግንዛቤና የተሳሳተ የድርጊት ርምጃ አለኝን; (ወቀሳ)
- እንዴት አስተሳሰቤንና የድርጊት ርምጃዬን ማስተካከል እችላለሁ; (ራስን ማረም)
- እንዴት ትክክለኛ አስተሳሰብና የድርጊት እርምጃን በቋሚነት በመያዝ መቀጠል እችላለሁ? (ሥልጠና)

## በማኅበረሰቡ ውስጥ መኖር

### በክርስቶስ ማደግ

- የቡድኑ አባላት ባለፈው የደቀመዝሙር ትምህርት ላይ የተማሩትን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ጠይቃቸው፡፡

### ከሌሎች ጋር የተማሩትን እውነት መከፋፈል

- የቡድኑ አባላት ባለፈው የደቀመዝሙር ትምህርት ላይ የተማሩትን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ጠይቃቸው፡፡ በቡድኑ ውስጥ በአሁኑ ጥናትና በሚቀጥለው የደቀመዝሙር ጥናት መሃከል የሚነሱ ትምህርቶችን እንዴት ለሌሎች የቡድኑ አባላት እንደሚያካፍሉ ጠይቃቸው፡፡

### ርዳታ የሚፈልጉትን መንከባከብ

- ካለፈው የቡድኑ የአገልግሎት ትምህርት በመነሳት ከማኅበረሰቡ እርዳታ የሚፈልጉትን እንዴት ባለ ምላሽ መርዳት እንደሚችሉ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው፤
- በቡድኑ ውስጥ ማናቸውም ዓይነት አዲስ የሆነ ትኩረት የሚሻ ችግር ወይም ማኅበረሰቡ ግንዛቤ ሊያገኝበት የሚያስፈልግ ጉዳይ ካለ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው፤
- ቡድኑ ትኩረት ለሚሻው ጉዳይ ወይም ችግር እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው፡፡

# ወደ ፍሬያማነትና መብዛት

## መጠራት

በተፈጥሮ ውስጥ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሲፈጥር “ፍሬያማና” “የመባዛት” ችሎታ ያለው አድርጎ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የፍጥረት አሰራር የሚያመላክተን ሁሉም ሕያው ፍጥረታት “ራሳቸውን መሰል ፍጡር” ለመውለድ እንደተፈጠሩ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውንም ሲፈጥረው ይህ የፍሬያማነትና የመባዛት መርህ አልተለወጠም፡፡ ***“እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው። ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።”*** ዘፍ. 1፡27-28

እኛ ከመጀመሪያውም ፍሬን እንድናፈራና ምድርን እንድንሞላ በእግዚአብሔር ተባርከን የተፈጠርን ነን፡፡ ላለፉት 6000 ዓመታት የሰው ልጅ ይህንን ሕግ በመታዘዝና ምድርን በመሙላት እየተጋ ይገኛል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜም የሰው ልጆች ዳግመኛ በመወለድ የሚገኘውን መንፈሳዊነትና እንደገና የመወለድን አስፈላጊነት እንዲለማመዱ አስተማረ፡፡ ዳግመኛ ካልተወለዱ በስተቀር ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት እንደማይቻልም አስረግጦ ተናገረ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሲመልስም፤ ***“ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።”*** ዮሐ. 3፡5-6

ክርስቶስ ወደ አዲስ ሕይወት ጠርቶናል፡፡ ይህ አዲስ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ እንደገና መወለድ ነው፡፡ ዳግመኛ አዲስ መወለዳችንን በሕዝብ ፊት በውኃ በመጠመቅ እናሳያለን፡፡ ፍሬን እንድናፈራና እንድንበዛ የተሰጠን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በእኛ ዳግመኛ በመንፈስ መወለድ ይከናወናል፡፡ በክርስቶስ ባገኘነው አዲስ ሕይወት ውስጥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለመዋለድ ትዕዛዙና እድሉ ተሰጥቶናል፡፡ ***“ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”***

ማቴ. 28፡18-20

ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት በማምጣት ደቀ መዝሙር ለማድረግና ለማጥመቅ በክርስቶስ ተጠርተናል፡፡ መንፈሳዊ ፍሬን የሚያፈራና በመንፈስ ዳግመኛ በመዋለድ የሚበዛ ሕይወት እንዲኖረን ተጠርተናል፡፡ ፍሬያማ የመሆንና ደቀ መዝሙርን የማብዛት ሥርዓተ ትምህርት ስልት የክርስቶስን ተከታዮች ደቀ መዝሙር ለማድረግ የተዘጋጀ ንድፍና እነርሱንም በማባዛት ውስጥ ወዳለ የመንፈሳዊ ፍሬያማነት ውጤት የሚያመራ ነው፡፡ ***“ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።”*** 1ኛ ጴጥ. 1፡23

ጌታ አምላካችን በአስገራሚ ፍሬያማነትና በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ ውስጥም በመንፈስ ዳግም ውልደት መብዛት በእውነት ይባርካችሁ፡፡ ይህች ምድራችንም ለእግዚአብሔር መንግስት በተወለዱ ሰዎች ተሞልታ ለማየት ያብቃን!

www.iBFAM.org
*Version 2.01*

iBFAM

www.iBFAM.org

ፍሬያማና የምትበዛ ሁን!



# በዕርቅ የተገነባ ኅብረት

## ትምህርት 2 መሠረት

*"በእኔ ኑሩ እኔም እናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም።" ዮሐ. 15፡4*

# ፍሬያማና የምትበዛ ሁን

**ተግባራዊ የደቀመዝሙርነት ሞዴል እና ሥርዓተ ትምህርት**

**የማዕዘን ድንጋይ ትምህርት ፡ ከ 1-4 የተዘጋጁ ጠቃሚ ትምህርቶች**

**አሳታሚ ፡** Every Home for Christ


አድራሻ ፡
Every Home for Christ International
640 Chapel Hills Dr., Colorado Springs, CO 80920 USA
(719)-260-8888
BFAM@ehc.org
www.iBFAM.org



Copyright © 2011 by Every Home for Christ

ይህን የጥናት ማቴሪያል ከዚህ በታች በተገለጸው ደንብ መሠረት እንደገና ማባዛትና ማሰራጨት ይፈቀዳል።

- አዘጋጁ "ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል ነው" በማለት ለደራሲው ተገቢውን ዋጋ በመስጠት፤
- ኤቭሪ ሆም ኢቫንጀሊዝም ይህን ማቴሪያል የትና እንዴት መጠቀም እንደሚገባ የሰጠውን ማሳሰቢያ ጠብቆ በመስራት፤
- ለማባዛት ከሚበዛ ወጪ በስተቀር ለሽያጭ ዓላማ ካልዋለ።

አውዱን ጠብቆ የትርጉምና የማዛመድ ሥራ የሚከተሉትን ነጥቦች እንዲያካትት ይበረታታል።

- ትርጉሙ በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል አስተባባሪነት በኩል ይሠራል፤
- የትርጉምና የጥቅስ አጠቃቀም የባለቤትነት መብት የኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ለመሆኑ እውቅና ለመስጠት ስምምነት ይደረጋል፤
- ማንኛውም ይዘቱን የተመለከተ ከአውዱ ጋር የሚዛመድ ሥራ በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት መጽደቅ ይኖርበታል፤
- የመጨረሻው በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የጸደቀው ቅጂ ለአርካይቭና ለሥርጭት ዓላማ ይቀመጣል። (ይህ ቅጂ በህትመት መልክና በዲጂታል ቅጂም ይቀመጣል)።


**የቢኤፍኤም ትምህርቶች፣ በደቀመዝሙርነት የማስተማር ዘዴ ላይ ያተኮሩ ሲሆን እያንዳንዱ ትምህርት ተገቢውን ጠቀሜታ አስገኝቶ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። የቢኤፍኤምን የማስተማር ዘዴ የሚያስጨብጥ ሥልጠናን አግኝተህ ካልሆነ ወይንም ደግሞ የቢኤፍኤምን የሥልጠና መመሪያ ካላገኘህ፣ ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የሥልጠናውን ጊዜ እንዲያመቻችልህ እባክህን በአድራሻችን አግኘን።**


በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከ1963 ዓ.ም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የተወሰደ ነው።

አከፋፋይ ፡ ኤቭሪሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል

# የማዕዘን ድንጋይ

## ትምህርት ሁለት ማውጫ


መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------------- ገጽ 4

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የግኝት ሂደት ------------------------------------------ ገጽ 6


## ትምህርቶች


**"M! መጠመቅ** ------------------------------------------------------------------ **ገጽ** 8

በጌታ ማመን

2.2 **እኛ የዓለም ብርሃን ነን** ----------------------------------------------- **ገጽ** 9

ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለዓለም ተናገር

2.3 **ከሌሎች ጋር ታረቅ** --------------------------------------------------- **ገጽ** 10

የበደሉህን ይቅር በል

2.4 **ዝሙትን አትፈጽም** ---------------------------------------------------- **ገጽ** 11

በክፉ ምኞት ወደ ሌላ አትመልከት

2.5 **ጋብቻ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው**---------------------------------- **ገጽ** 12

እግዚአብሔር መፋታትን አይወድም

2.6 **ለግፍ ምላሽ መስጠት**-------------------------------------------------- **ገጽ** 13

የእግዚአብሔር ፍቅር ምሳሌ በመሆን ኑር

2.7 **ጠላቶችህን ውደድ**------------------------------------------------------ **ገጽ** 14

እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ይወዳል፤

2.8 **ለሌሎች ስጥ** ------------------------------------------------------------ **ገጽ** 15

በችግር ላይ ላሉት የእግዚአብሔር ጥንቃቄ

2.9 **ጸሎት** ---------------------------------------------------------------------- **ገጽ** 16

ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና እርሱን ማዳመጥ

2.10 **ኅብረትን በሰማይ ማከማቸት** ------------------------------------------ **ገጽ** 17

እግዚአብሔርን በኑሮአችንና በንብረታችን ማክበር

2.11 **አትዘን**------------------------------------------------------------------- **ገጽ** 18

እግዚአብሔር የሚያስፈልግህን ያውቃልም፣ ይጠነቀቅልሃልም፤

2.12 **በሌሎች ላይ አትፍረድ** ------------------------------------------------ **ገጽ** 19

እግዚአብሔር ፈራጅ ነው

2.13 **ጠይቅ፣ ፈልግ፣ አንኳኳ** ---------------------------------------------- **ገጽ** 20

እግዚአብሔር አሁን ለጸለይነው ጸሎት ምላሽ አለው፤

**የደቀ መዝሙር ቡድኖችን መምራት**-------------------------------------------- **ገጽ** 21

# ፍሬያማና የምትበዛ ሁን

## *መግቢያ*

“የፍሬያማና የምትበዛ ሁን” (አፍራ ብዛ) የትምህርት ኮርሶች የደቀመዛሙርነት የማስተማሪያ ስልትና ሥርዓተ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች ከአንዱ እውነተኛ ሕያው እግዚአብሔር ጋር ልዩ የሆነ ኅብረት እንዳላቸው ለማስገንዘብ የተነደፈ ነው፡፡ የአፍራ ብዛ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች ከኢየሱስ ጋር ባላቸው ኅብረት የተትረፈረፈ ሕብረት ሊኖራቸው እንደሚችል ለማሳየት የተነደፈ ኮርስ ነው፡፡ ሰዎች እርስ በእርስ ኅብረት እንዲኖራቸው ተፈጥረዋል፡፡ ከዚህም በላይ፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው ተፈጥረዋል፡፡ የኃጢአት ውጤትም ሰዎች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት እንዲቋረጥ አድርጎአል፡፡ የተቋረጠው ይህ ኅብረት እኛ ሰዎች እርስ በእርሳችን ከተቋረጠው ተፈጥሮና ከእግዚአብሔር ጋር ውህደት እንዳይኖረን አድርጎአል፡፡

በዚህም ምክንያት በዓለማችን ላይ ጦርነት፣ ረሃብ፣ ግድያ፣ ተላላፊ በሽታ፣ ሕመም፣ ፍርደ ገምድል መሪዎች፣ ፍትህ አልባ ማኅበረሰብም እንዲኖር ሆኖአል፡፡ ከኃጢአት የተነሳ ኅብረታችን ተቋርጧል፡፡ ኃጢአትን እንዴት እንደምናስወግድና እንዴትስ በተሃድሶ ኅብረትን መመሥረት እንደምንችል እስካልተረዳን ድረስ፣ መልካሙን ሕይወት ለመኖር ከሚያስችለን ሕይወት ርቀናል፡፡

የምስራቹ ቃል እግዚአብሔር ከኃጢአት የመውጪያውን መንገድና፣ የተቋረጠውን ኅብረትም ለማደስ ኃላፊነት እንደወሰደ ያመላክተናል፡፡ የአፍራ ብዛ ኮርስ ትኩረትም ይህን ማመልከት ነው፡፡ አፍራ ብዛ ሰዎች በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የምሥራቹን ቃል እንዴት እንደሚያነቡና እንደሚገነዘቡ ለማስተማር ይፈልጋል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በታማኝነት እውነትን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ቃል ገብቶላቸዋል:: ***“ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል”*** (ማቴ. 7፡7-8)፡፡ የአፍራ ብዛ ኮርስ ሰዎች እንዴት እንደሚጠይቁ፣ እንደሚፈልጉና እንደሚያንኳኩ ያስተምራል፡፡ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንዴት እንደሚያነቡና እውነትን እንዴት እንደሚፈልጉም ያስተምራል፡፡ እውነቱም እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ኃላፊነትን እንዲወስድና ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ማደስ እንደሚፈልግ ያስተምራል፡፡

የእግዚአብሔርን እውነት በታማኝነት ለሚፈልጉ ሁሉ፣ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እውነት ማግኘት ለሚፈልጉ፣ ለእነርሱ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ እርቅ እንዲሆንላቸው ቃል ኪዳን ተገብቶላቸዋል፡፡ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት ሲታረቅ ያን ጊዜ የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራሉ፡፡

ይህ ኮርስ “ፍሬያማና የምትበዛ ሁን” የተባለበት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት የምንኖረው የመጀመሪያ ደረጃ፤ እግዚአብሔር ፍሬያማ ሕይወት እንድንኖር አድርጎ እንደፈጠረን ለማሳወቅ ነው፡፡ ፍሬያማው ሕይወት በመንፈሳዊነት ወደ መባዛት ሕይወትም ያመራል፡፡

# የደቀመዛሙርት ቡድኖችን መምራት

በዚህ ጥናት መጨረሻ ላይ የአፍራ ብዛ ትናንሽ ቡድን ሞዴሎች ተካተዋል፡፡ ትናንሾቹ የደቀመዝሙር ሞዴሎች ቡድን፣ ትናንሽ የቡድን ስብሰባ በአፍራ ብዛ የደቀመዝሙር ሞዴልና ሥርዓተ ትምህርት በመጠቀም እንዴት እንደምንመራ ያሳየናል፡፡

# ጠቃሚ የሆኑት ተከታታይ ትምህርቶች

በአፍሪ ብዛ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የተካተቱት የመጀመሪያዎቹ 52 ተከታታይ የሆኑ ትምህርቶች ተከታታይ ጠቃሚ ትምህርቶች ይባላሉ። እነኚህ ተከታታይ ትምህርቶች በአራት ክፍለ ትምህርቶች የተመደቡና እያንዳንዳቸው 13 ትምህርቶችን የያዙ የአንድ ዓመት ጥናቶች ናቸው። እነኚህ ጠቃሚ ተከታታይ ትምህርቶች ልክ ቤትን በመገንባት መልክ የተዋቀሩ ናቸው። አራቱ የተለያዩ ክፍለ ትምህርቶችም የማዕዘን ድንጋይ፣ መሠረት፣ ግድግዳና ጣራን ያካትታሉ። ከዚህ በታች የእነኚህ አራት ትምህርቶች ይዘት ተብራርቷል።



## የማዕዘን ድንጋይ ክፍለ ትምህርት - የማስታረቅ ኅብረት

የማዕዘን ድንጋይ ክፍለ ትምህርቶች በማስታረቅ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። እግዚአብሔር እንዴት ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ከሚያስረዳው ፍጥረተ ትምህርትም ይጀምራል። ይህ እውነትም ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ንጽረተ ዓለም ያስጨብጠናል። ሁለተኛው ትምህርትም የሰው ልጅ ከሌላው ፍጥረት የተለየ ሆኖ እንደተፈጠረ ያስጨብጠናል። እኛ የተፈጠርነው ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ኅብረት እንዲኖረን ነው። ሦስተኛውና አራተኛው ትምህርትም የሰው ልጅ እንዴት በሰይጣን እንደተታለለ ያሳያል። የመጀመሪያው ሰው እግዚአብሔርን አልታዘዘም፤ በዚህም ምክንያት እኛ ሁላችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕብረት ተቋረጠ። የቀረው የትምህርቱ ክፍል እግዚአብሔር ይህን የተቋረጠ ኅብረት እንደገና ለማደስና የሰውን ልጅ ለመዋጀት የዘረጋውን የማስታረቅ ዕቅድ ያሳየናል።



## መሠረት የመጣል ክፍለ ትምህርት - ከክርስቶስ ጋር መዝለቅ

ይህ የትምህርት ክፍል መሠረት ያደረገው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዛት የመፈጸምን አስፈላጊነት ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር ***"ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።"*** (ማቴ. 7:24) መሠረት የመጣል ክፍለ ትምህርት በመታዘዝ የአኗኗር ዘዴ ውስጥ የሚገኘውን ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትን ያሳያል።



## የግድግዳ ክፍለ ትምህርት - የተትረፈረፈ ሕይወት

የአንድ ቤት ግድግዳ ከቤቱ ውጪ ያሉ ሰዎች ሁሉ በግልጽ የሚመለከቱት ነው። የክርስቶስ ተከታዮችም ልክ እንደዚሁ ናቸው። የክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔርን በምድር ላይ የሚወክሉ ናቸው። እነኝህ የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔር ተወካይ እንደመሆናቸው መጠን በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች እግዚአብሔርን በመምሰልና በድርጊታቸውም በመግለጽ የሚያሳዩ መሆን ይገባቸዋል። ይህ ክፍለ ትምህርት በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን ቤተሰቦች አስፈላጊነት ዓላማ ላይ ያተኩራል።




## የጣሪያ ክፍለ ትምህርት - ጠቃሚ እውነት

ይህ የመጨረሻ ክፍለ ትምህርት የክርስትናን እምነት መሠረታዊ እውነት ያካትታል። ጣራው ውጫዊ ወይም አላስፈላጊ የሆነውን ነገር እንድንከላከል ተደርጎ ተነድፎአል። የጣሪያ ክፍለ ትምህርት የሐሰት ትምህርትን ለመከላከል የክርስትናን እምነት መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በማሳየት የሐሰትን ትምህርት የመከላከል ንድፍ ነው።




*"እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።"* ኤፌ. 2:19-22

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የግኝት ሂደት




**የትምህርቱ ጭብጥ** - መሬቱን ማዘጋጀት

የትምህርቱ ጭብጥ ደቀመዝሙር ለሚሆኑት ሰዎች ዘር የሚዘራበትን አዕምሮና ልብን በማሳደግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገኘው እውነት እነርሱን ማዘጋጀት ነው።

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ** - ዘሩን መዝራት

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በለማው መሬት  ውስጥ የሚዘራው ዘር ሲሆን ከተዘራ በኋላ የእውቀትና የአርነት ፍሬን የሚያፈራ ይሆናል።

**የመገንዘብ ሂደት** - ውኃና ማዳበሪያ

የግንዛቤ ሂደት ጥያቄዎች ዘሩን ውኃ እንደማጠጣትና ማዳበሪያ እንደመጠቀም ነው። የእግዚአብሔር ቃል፣ የታሪኩን እውነት ለመግለጥ ይረዳል።

**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት** - ማጣት / መግረዝ

ተጨማሪ የቃሉ ጥናት በታሪኩ ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚገነባ / አስተምህሮ እንዳይኖርም ይከላከላል።

**የተግባር ጥያቄዎችና መደምደሚያ** -

የተግባር ጥያቄዎችና መደምደሚያው በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ያለውን የአዝመራውን ውጤት ለመሰብሰብና በሕይወታችን ውስጥ የተረዳነውን እውነት እንድንተገብረው ይረዳናል።

# የትምህርቱ ቅደም ተከተል

## ደረጃ 1 - መሬቱን ማዘጋጀት የትምህርቱ ጭብጥ

## ደረጃ 2 - ዘር መዝራት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

## ደረጃ 3 - ውኃና ማዳበሪያ የግኝት ሂደት

### ታሪኩን ማወቅ - መጠየቅ

**ማን ነው? ተግባሩ ምንድን ነው? ታሪኩን በጥልቀት ማወቅ፤**

- በታሪኩ ውስጥ ያሉት ገጸ ባሕርያት እነማን ናቸው?
- የገጸ ባሕርያቱ ድርጊት ምንድን ናቸው?
- በታሪክ ውስጥ ያለው ግልጽ የሆነ ጥልቅ ጉዳይ ምንድን ነው?

### ታሪኩን መረዳት - መፈለግ

**ፍልቅ ስሜት፣ የመነሻ ምክንያትና ምርጫ**

- ገጸ ባሕርያቱ የተሰማቸው ፍልቅ ስሜት ምን ይመስላል;
- ገጸ ባሕርያቱን ለድርጊት ያነሳሳቸው መነሻ ምክንያት ምንድን ነው;
- ገጸ ባሕርያቱ የወሰዱአቸው ልዩ ልዩ ምርጫዎች ምንድን ናቸው?

### የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታን ማግኘት - ማንኳኳት

**ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤና ርምጃ**

- የገጸ ባሕርያቱን ድርጊት፣ ጥልቅ ጉዳይ፣ ፍልቅ ስሜት፣ መነሻ ምክንያትና ምርጫ በጥንቃቄ ስትመለከት ምን ትማራለህ?

## ደረጃ 4 - መግረዝ ተጨማሪ የቃሉ ጥናት

## ደረጃ 5 - መከሩን መሰብሰብ የማዛመድ ጥያቄና መደምደሚያ

***"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።"*** 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17

በታሪክ ውስጥ በተዳሰሰው ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳትና ተግባራዊነት መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ (ማስተማር)

- እኔ የተሳሳተ ግንዛቤና ድርጊት አለኝን; (ተግሳጽ)፤
- የተሳሳተ ግንዛቤዬንና ተግባሬን እንዴት ማስተካከል እችላለሁ (ማቅናት)፤
- እንዴት ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታና ግንዛቤ ጨብጬ መጓዝ እችላለሁ? (ሥልጠና)

# መጠመቅ

## በጌታ ማመን

## የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

የውኃ ጥምቀት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ጌታን ከተቀበልን በኋላ መጠመቅ እንዳለብን ይናገራል። ጥምቀት የሚባለው አዲስ አማኞች ውኃ ውስጥ በመጥለቅና እንደገና በመውጣት የሚያሳዩት ነው። ጥምቀት ክርስቲያን ከሆንን በኋላ በመንፈሳዊ ሕይወት እንደገና መወለዳችንን የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ጥምቀት የክርስቶስ ተከታዮች መሆናችንን ለሌሎች የምናሳይበት ምሳሌ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" ማቴ. 28፡19***

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ፊሊጶስ የእግዚአብሔር መንግሥትን የምስራች ቃል የሚያውጅ የክርስቶስ ተከታይ ነው።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው። ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ። ርኵሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤ በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ። ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው ግን፦ እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ፥ እየጠንቈለ የሰማርያንም ወገን እያስገረመ ቀድሞ በከተማ ነበረ። ከታናናሾችም ጀምሮ እስከ ታላላቆቹ ድረስ፤ ታላቁ የእግዚአብሔር ኃይል ይህ ነው እያሉ ሁሉ ያደምጡት ነበር። ከብዙ ዘመንም ጀምሮ በጥንቈላ ስላስገረማቸው ያደምጡት ነበር። ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ፊልጶስን ባመኑት ጊዜ፥ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ። ሲሞንም ደግሞ ራሱ አመነ፤ ተጠምቆም ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር፤ የሚደረገውንም ምልክትና ታላቅ ተአምራት ባየ ጊዜ ተገረመ።"***
ሐዋ. 8፡5-13

## የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

## ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሐዋ. 2፡38፤ ሐዋ. 18፡8፤ ሮሜ 6፡4-5፤ ቆላ. 2፡12፤ ገላ. 3፡27)

**የማዛመድ ጥያቄዎች -** *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ -*** መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች መጠመቅ እንዳለባቸው ይናገራል። የውኃ ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ ጌታና አዳኝ መሆኑን በልባችን ውስጥ እንዳመንን የምናሳይበት ምሳሌ ነው። ጥምቀት የክርስቶስ ተከታዮች መሆናችንን ለሌሎች የምናሳይበት ምሳሌ ነው።

# እኛ የዓለም ብርሃን ነን

ትምህርት 2-2

## ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለዓለም ተናገር

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተል ሰው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን የዓለም ብርሃን በመሆን ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለዓለም ያሳያል ይላል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል። መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።"* ማቴ. 5፡14-16

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

*የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።*

ኢየሱስ በጉድጓድ አጠገብ ተቀምጦ ነበር። አንዲት ሴትም ውኃ ፈልጋ መጣች። ኢየሱስም የሚጠጣ ውኃ እንድትሰጠው ጠየቃት። ኢየሱስም ለሴቲቱ ለዘላለም ሕይወት የሚሆን ሕያው ውኃ ሊሰጣት እንደሚችል ነገራት። ጌታ ኢየሱስ ለዚያች ሴት በመለኮታዊ እውቀት ብቻ ሊገለጽ የሚችለውን የእርሷን ማን መሆን ነገራት። ኢየሱስ እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነም ገለጸላት። ሴቲቱም ኢየሱስ በተናገረው ነገር ተገርማ የነገራትን በሙሉ አመነች።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> *"ሴቲቱም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች ለሰዎችም፦ ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? አለች። ከከተማ ወጥተው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።" . . . "ሴቲቱም፦ ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለ መሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት። የሰማርያ ሰዎችም ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ለመኑት፤ በዚያም ሁለት ቀን ያህል ኖረ። ስለ ቃሉ ከፊተኞች ይልቅ ብዙ ሰዎች አመኑ፤ ሴቲቱንም፦ አሁን የምናምን ስለ ቃልሽ አይደለም፥ እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና፤ እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደ ሆነ እናውቃለን ይሉአት ነበር።"* ዮሐ. 4፡28-30፤ 39-42

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሐዋ. 1፡8፤ ማር. 16፤15-16፤ ሉቃ. 11፡33-36)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - ኢየሱስ እውነተኛ ብርሃንና የዓለም አዳኝ ነው። ኢየሱስ ለተከታዮቹ ወደ ዓለም እንዲሄዱና ብርሃን በመሆን ሰዎች እርሱን ማየት እንዲችሉ እንዲያደርጉ ነገራቸው።

# ከሌሎች ጋር ታረቅ

ትምህርት 2-3

## የበደሉህን ይቅር በል

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ የእርሱን ደቀ መዛሙርት እርስ በእርስ በሰላም እንዲኖሩ አስተማራቸው። ክርስቲያኖች ለሌሎች ሰዎች ትሁት እንዲሆኑና እነርሱን የበደሉዋቸውን ምህረት እንዲያደርጉላቸው ተምረዋል። እርስ በእርስ በሰላም እንድንኖር፤ እኛን ያስቀየሙንን ወይም የጎዱንን ሰዎች ይቅር ማለት ይገባናል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።"***

ማቴ. 5፡23-24

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

***የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።***

ከጌታ ደቀ መዛሙርት አንዱ የበደሉትን ሰዎች ምን ያህል ጊዜ ይቅር ማለት እንደሚገባው ጌታን ጠየቀው። በምላሹም ጌታ የሚከተለውን ምሳሌ ተናገረ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤*

***"ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቈጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች። መቈጣጠርም በጀመረ ጊዜ፥ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። የሚከፍለውም ቢያጣ፥ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ። ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና፦ ጌታ ሆይ፥ ታገሠኝ ሁሉንም እከፍልሃለሁ አለው። የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፥ ዕዳውንም ተወለት። ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘና፦ ዕዳህን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው። ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ፦ ታገሠኝ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው። እርሱም አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው። ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ። ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ፦ አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤ እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው። ጌታውም ተቈጥቶ ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚሣቅዩት አሳልፎ ሰጠው። ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።"*** ***ማቴ. 18፡23-35***

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማቴ. 6፡14፤ ሉቃ. 11፡4፣ ሉቃ. 17፡3-4፤ 2 ቆሮ. 2፡5-11፤ ቆላ. 3፡12-14፤ ኤፌ. 4፡32፤ ማር. 11፡25-26)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - የክርስቶስ ተከታዮች ልክ እግዚአብሔር እኛን እያንዳንዳችንን ይቅር እንዳለን ሌሎችን ሰዎች ይቅር ልንል ይገባል። የክርስቶስ ተከታዮች በአካባቢያቸው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር በሰላም እንዲኖሩ ታዘዋል።

ትምህርት 2-4

# ዝሙትን አትፈጽም

## በክፉ ምኞት ወደ ሌላ አትመልከት

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ዝሙትን እንዳይፈጽሙ አስተምሯቸዋል። ጌታ ኢየሱስ ወደ ሌላ ሰው መመልከትና መመኘትም ኃጢአት እንደሆነ አስተምሯል፡

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።" ማቴ. 5:27-28***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

***የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።***

ዳዊት ዝነኛ የሆነ የእሥራኤል ንጉስ ነበር። ይህ ንጉስ አንዲት ሴት ገላዋን ስትታጠብ ከሰገነቱ ላይ ሆኖ ተመለከተ። ይህች ሴት የዳዊት ወታደራዊ ተቋም ኮማንደር የነበረ ሰው ሚስት ነበረች። ስሙም ኦሪዮ ይባል ነበር። ዳዊት ይህችን ሴት እንዲያመጡዋት አገልጋዮቹን አዘዛቸው። እርሷም ከእርሱ አረገዘች። ዳዊትም ኦሪዮን ወደ ጦርነት እንዲሄድና በዚያ እንዲሞት አደረገው። እግዚአብሔርም በሁኔታው አዘነ። ናታን የተባለውን ነብይም ወደ ዳዊት እንዲሄድ እግዚአብሔር አደረገ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"እግዚአብሔርም ናታንን ወደ ዳዊት ላከ፥ ወደ እርሱም መጥቶ አለው። በአንድ ከተማ አንዱ ባለጠጋ አንዱም ድሀ የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩ። ባለጠጋውም እጅግ ብዙ በግና ላም ነበረው። ለድሀው ግን ከገዛት አንዲት ታናሽ በግ በቀር አንዳች አልነበረውም፤ አሳደጋትም፥ ከልጆቹም ጋር በእርሱ ዘንድ አደገች፤ እንጀራውንም ትበላ፥ ከዋንጫውም ትጠጣ፥ በብብቱም ትተኛ ነበር፥ እንደ ልጁም ነበረች። ወደ ባለጠጋውም እንግዳ በመጣ ጊዜ ከበጉና ከላሙ ወስዶ ለዚያ ወደ እርሱ ለመጣው እንግዳ ያዘጋጅለት ዘንድ ሳሳ፤ የዚያንም የድሀውን ሰው በግ ወስዶ ለዚያ ለመጣው ሰው አዘጋጀ። ዳዊትም በዚያ ሰው ላይ እጅግ ተቈጥቶ ናታንን፦ ሕያው እግዚአብሔርን! ይህን ያደረገ ሰው የሞት ልጅ ነው። ይህን አድርጎአልና፥ አላዘነምና ስለ አንዲቱ በግ አራት ይመልስ አለው። ናታንም ዳዊትን አለው፦ ያ ሰው አንተ ነህ፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በእስራኤል ላይ ንጉሥ ልትሆን ቀባሁህ፥ ከሳኦልም እጅ አዳንሁህ፤ የጌታህንም ቤት ሰጠሁህ፥ የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ ጣልሁልህ፤ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ፤ ይህም አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር። አሁንስ በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልህ? ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መትተሃል፥ ሚስቱንም ለአንተ ሚስት ትሆን ዘንድ ወስደሃል፤ እርሱንም በአሞን ልጆች ሰይፍ ገድለሃል።"*** 2ኛ ሳሙ. 12:1-9

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ዘጸ. 20:14፤ ዕብ. 13:4፤ ኤፌ. 5:3-5፤ 1 ቆሮ. 6:13-20፤ ቆላ. 3:1-11፤ 1 ተሰ. 4:3-8፤ ምሳ. 6:32)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - በጋብቻ ኅብረት ውስጥ ዝሙትን መፈጸም ታማኝነትን ማጉደል ነው። ዝሙት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ነው። ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በወሲብ ግንኙነት ሥነ ምግባር የጎደላቸው እንዳይሆኑ አስተማራቸው። ጌታ ኢየሱስ ወደ ሌላ ሰው መመልከትና በክፉ መመኘት የዝሙትን ያህል እንደሆነ አስተማረ።

# ጋብቻ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው

**ትምህርት 2-5**

## እግዚአብሔር መፋታትን አይወድም

**የትምህርቱ ጭብጥ -** *መሬቱን ማዘጋጀት*

ጌታ ኢየሱስ የትዳር ኅብረት ቅዱስ እንደሆነና ለእግዚአብሔርም አስፈላጊ እንደሆነ አስተማረ፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።"*** **ማቴ. 5፡32**

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ -** *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

ጌታ ኢየሱስ ብዙዎችን ይፈውስና ያስተምር ስለነበር ብዙ ሕዝብ ይከተሉት ነበር፡፡ ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ በመቅረብ በርካታ ጥያቄዎችን ያቀርቡለት ነበር፡፡ ፈሪሳውያን የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ፡፡ እነኚህ ፈሪሳውያን እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጣቸውን በርካታ የሃይማኖት ሕግጋት ይከተሉ ነበር፡፡ ሙሴ ጌታ ኢየሱስ ከመወለዱ በርካታ ዓመታት በፊት እሥራኤልን ሲመራ የነበረ ሰው ነው፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡና ሲፈትኑት፦ ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት። እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ፦ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥ አለም፦ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው። እነርሱም፦ እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቱአት ስለ ምን አዘዘ? አሉት። እርሱም፦ ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።" ማቴ. 19፡3-9***

**የግኝት ሂደት -** *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት -** *መግረዝ*

(ኤፌ. 5፡21-28፤ ዘፍ. 2፡20-24፤ 1 ቆሮ. 7)

**የማዛመድ ጥያቄዎች -** *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

***መደምደሚያ*** **-** ትዳር በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው፡፡ ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ነው፡፡ የክርስቶስ ተከታዮች ትዳራቸውን ለመጠበቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

# ለግፍ ምላሽ መስጠት

ትምህርት 2-6

## የእግዚአብሔር ፍቅር ምሳሌ በመሆን ኑር

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዴት ለግፍ ተግባር ምላሽ እንደሚሰጡ አስተማራቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በእነርሱ ላይ ክፋትን በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ በበቀል እንዳይመልሱ ነገራቸው፡፡ ክርስቲያኖች ለሰዎች ሁሉ በፍቅርና በደግነት መልካም ምሳሌ እንዲሆኑ አስተማረ፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤ እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፤ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ።" ማቴ. 5:39-41***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ይሁዳ ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር፡፡ የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን ለመግደል ይፈልጉ ነበር፡፡ ይሁዳ ለገንዘብ ብሎ ኢየሱስን አሳልፎ ሰጠ፡፡ በዚህ ታሪክ፣ ኢየሱስ ከይሁዳ በስተቀር ለሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ተላልፎ እንደሚሰጥ ነግሮአቸው ነበር፡፡ ኢየሱስ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ያውቅ ነበር፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ገናም ሲናገር እነሆ ሰዎች መጡ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱም ይሁዳ የሚባለው ይቀድማቸው ነበር፥ ሊስመውም ወደ ኢየሱስ ቀረበ። ኢየሱስ ግን፦ ይሁዳ ሆይ፥ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን? አለው። በዙሪያውም የነበሩት የሚሆነውን ባዩ ጊዜ ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን? አሉት። ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው። ኢየሱስ ግን መልሶ፦ ይህንስ ፍቀዱ አለ፤ ጆሮውንም ዳስሶ ፈወሰው። ኢየሱስም ወደ እርሱ ለመጡበት ለካህናት አለቆችና ለመቅደስ አዛዦች ለሽማግሌዎችም፦ ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጕመድ ይዛችሁ ወጣችሁን? በመቅደስ ዕለት ዕለት ከእናንተ ጋር ስሆን እጃችሁን አልዘረጋችሁብኝም፤ ይህ ግን ጊዜያችሁና የጨለማው ሥልጣን ነው አላቸው።"***
ሉቃ. 22:47-53

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሉቃ. 6:32፤ ኤፌ. 5:1-2፤ ሮሜ 12:17-21፤ ዮሐ. 4:7-8፣ ዮሐ. 13:34፤ ማር. 12:28-31፤ 1 ጴጥ. 1:22፤ 1 ዮሐ. 3:11፤ 1 ቆሮ. 4:12፤ 1 ጴጥ. 3:9፤ 2 ቆሮ. 12:10)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

**መደምደሚያ** - ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሰዎች በደልን ቢፈጽሙባቸው የበቀል ምላሽ እንዳይሰጡ ነገራቸው፡፡ የኢየሱስ ተከታዮች ከሌሎች ሰዎች በተለየ በደል ሲደርስባቸው ምላሽ የሚሰጡበት መንገድ የተለየ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ የኢየሱስን ፍቅር ያውቃሉ፡፡ ኢየሱስ ክርስቲያኖችን ለሰዎች ሁሉ በፍቅርና በደግነት መልካም ምሳሌ በመሆን እንዲኖሩ አስተማረ፡፡

# ጠላቶችህን ውደድ

ትምህርት 2-7

## እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ይወዳል፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠላቶቻቸውን እንዲወዱና እንዲጸልዩላቸው አስተማራቸው። ጌታ ኢየሱስ እንደሚገባ የማይንከባከቡንን ሰዎች መውደድ አስቸጋሪ ነው ይላል። ጌታ ደቀ መዛሙርቱንም ሲያስተምር እነርሱ ከሌሎች ሰዎች የተለዩ መሆናቸውን ገለጸ፤ ስለዚህም ምክንያቱ ሊወደዱ የማይገባቸውን ሰዎች መውደድ መቻላቸው እንደሆነ ይነግራቸዋል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።" ማቴ. 5፡44-45*

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ጌታ ኢየሱስ በምድር በተመላለሰበት ጊዜ በርካታ ጠላቶች ነበሩት። እነኚህ ጠላቶች ኢየሱስን ይጠሉት ነበር። ጌታ ኢየሱስ በእነኚህ ጠላቶቹ ከተሰቃየ በኋላ ተገድሎአል።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

*"በወሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መስቀሉን እንዲሸከም ጫኑበት። ዋይ ዋይ ከሚሉና ሙሾ ከሚያወጡ ሴቶችና ከሕዝቡ እጅግ ብዙዎች ተከተሉት።" . . . "ሌሎችንም ሁለት ክፉ አድራጊዎች ደግሞ ከእርሱ ጋር ይገድሉ ዘንድ ወሰዱ። ቀራንዮም ወደሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ፥ በዚያ እርሱን ክፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ። ኢየሱስም፦ አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ። ልብሱንም ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉበት። ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር። መኳንንቱም ደግሞ፦ ሌሎችን አዳነ፤ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ፥ ራሱን ያድን እያሉ ያፌዙበት ነበር። ጭፍሮችም ደግሞ ወደ እርሱ ቀርበው ሆምጣጤም አምጥተው አንተስ የአሁድ ንጉሥ ከሆንሁ፥ ራስህን አድን እያሉ ይዘብቱበት ነበር። ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው ተብሎ በግሪክና በሮማይስጥ በዕብራይስጥም ፊደል የተጻፈ ጽሕፈት ደግሞ በእርሱ ላይ ነበረ። ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ። አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው። ሁለተኛው ግን መልሶ፦ አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን? ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም ብሎ ገሠጸው። ኢየሱስንም፦ ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው። ኢየሱስም፦ እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።"*

ሉቃ. 23፡26-27፤ 32-43

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማር. 12፡28-31፤ ዮሐ. 13፡34፤ ሮሜ 12፡17-21፤ ሉቃ. 6፡27-38)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - ጌታ ኢየሱስ በእኛ ላይ መከራ የሚያደርሱብንን ሰዎች እንድንወዳቸውና እንድንጸልይላቸው አስተማረን። ጌታ ኢየሱስ መከራን ላደረሱበትና ለገደሉት ሰዎች ምህረትን አደረገላቸው። የክርስቶስ ተከታዮች ጌታ ኢየሱስ እንዳደረገው ሁሉ ለጠላቶቻቸው መልካም ምላሽን ሊሰጡ ይገባል።

# ለሌሎች ስጥ

ትምህርት 2-8

## በችግር ላይ ላሉት የእግዚአብሔር ጥንቃቄ

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ጌታ ኢየሱስ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች እንዲረዱ ደቀ መዛሙርቱን አስተማረ። የክርስቶስ ተከታዮች ለሌሎች ልግስናን ሲያደርጉ በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች እንዲያዩዋቸው ለታይታ መሆን የለበትም። ክርስቲያኖች ለችግረኞች ልግስናን ሲያደርጉ በእግዚአብሔር ይታያሉ፤ እርሱም በሰማይ ሽልማታቸውን ይሰጣቸዋል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።" ማቴ. 6፡3-4***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በዓለም ፍጻሜ ምን እንደሚሆን ጌታን ጠየቁት። ጌታ ኢየሱስ በዓለም መጨረሻ እርሱ ንጉሥ ሆኖ በሰዎች ላይ ፍርድን እንደሚበይን ነገራቸው።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል። ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና። ጻድቃንም መልሰው ይሉታል፦ ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን? ንጉሡም መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል። በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፦ እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ። ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና። እነርሱ ደግሞ ይመልሱና፦ ጌታ ሆይ፥ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል። ያን ጊዜ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል። እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።"*** ማቴ. 25፡32-46

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ምሳ. 19፡17፣ ምሳ. 28፡27፤ መዝ. 82፡3፤ ማቴ. 5፡42፣ ማቴ. 19፡21፤ ኤር. 22፡3)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - ጌታ ኢየሱስ ለችግረኞች እንክብካቤ ያደርግ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ለተከታዮቹ፤ ለተቸገሩት ልግስናን እንዲያደርጉ አዘዛቸው። ጌታ ኢየሱስ ለሌሎች የሚያካፍሉትን ይሸልማቸዋል።

# ጸሎት

ትምህርት
2-9

## ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና እርሱን ማዳመጥ

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ሁል ጊዜ መጸለይ እንዳለባቸው አስተማራቸው። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና እግዚአብሔርን መስማት ነው። በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር ይሰማናል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል። ማቴ. 6፡6***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ሄሮድስ የተባለው ፍርደ ገምድል ንጉሥ ክርስቲያኖችን ይጠላቸው ነበር። ንጉሥ ሄሮድስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የቆሙትን ሁሉ መግደሉን ተያይዞት ነበር። ጴጥሮስ የተባለውን የቤተ ክርስቲያን መሪም የሄሮድስ ወታደሮች አስረው ሊገድሉት እየተዘጋጁ ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር። ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ፥ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለት ታስሮ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር፤ ጠባቂዎችም በደጁ ፊት ሆነው ወኅኒውን ይጠብቁ ነበር። እነሆም፥ የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ፤ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አነቃውና፡- ፈጥነህ ተነሣ አለው፤ ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ። መልአኩም፡- ታጠቅና ጫማህን አግባ አለው፥ እንዲሁም አደረገ። ልብስህንም ልበስና ተከተለኝ አለው። ወጥቶም ተከተለው፤ ራእይንም የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ በመልአኩ የሚደረገው ነገር እውነት እንደ ሆነ አላወቀም። የመጀመሪያውንና የሁለተኛውንም ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚያወጣው ወደ ብረቱ መዝጊያ ደረሱ፤ እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው፤ ወጥተውም አንዲት ስላች አለፉ ወዲያውም መልአኩ ከእርሱ ተለየ። ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ። ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ። ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ። ጴጥሮስም የደጁን መዝጊያ ባንኳኳ ጊዜ ሮዴ የሚሉአት አንዲት ገረድ ትሰማ ዘንድ ቀረበች፤ የጴጥሮስ ድምፅ መሆኑንም ባወቀች ጊዜ ከደስታዋ የተነሣ ደጁን አልከፈተችም፥ ነገር ግን ወደ ውስጥ ሮጣ ጴጥሮስ በደጅ ፊት ቆሞ እንዳለ አወራች። እነርሱም፡- አብደሻል አሉአት። እርስዋ ግን እንዲሁ እንደ ሆነ ታስረግጥ ነበር። እነርሱም፡- መልአኩ ነው አሉ። ጴጥሮስ ግን ማንኳኳቱን አዘወተረ፤ ከፍተውም አዩትና ተገረሙ። ግን ዝም እንዲሉ በእጁ ጠቅሶ ጌታ ከወኅኒ እንዴት እንዳወጣው ተረከላቸውና። ይህን ለያዕቆብና ለወንድሞች ንገሩ አላቸው። ወጥቶም ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ።" ሐዋ. 12፡5-17***

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ኤር. 29፡12፤ ማቴ. 5፡44፤ ማቴ. 7፡11፤ 2 ዜና 7፡14፤ መዝ. 32፡5-11፤ ኤር. 42፡3፤ 1 ተሰ. 5፡17)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17) ገጽ ተመልከት።

**መደምደሚያ** - ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲጸልዩ ነገራቸው። በምትጸልይ ጊዜ እግዚአብሔር ይሰማሃል። ጌታ ኢየሱስ የሚያስፈልገን ነገር ሲኖር እንድንጸልይ ተናገረ። በምትጸልይ ጊዜ ተአምራዊ ነገሮች ይሆናሉ።

# ንብረትን በሰማይ ማከማቸት

ትምህርት 2-10

## እግዚአብሔርን በኑሮአችንና በንብረታችን ማክበር

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ሰዎች በመንግሥተ ሰማይ የሚቀበሉት ሽልማት፣ በምድር ሕይወታቸውና ኑሮአቸው እግዚአብሔርን በምን መንገድ እንዳከበሩት የሚገልጸው አኗኗራቸው ይወስነዋል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።" ማቴ. 6፡19-21*

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

*የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።*

ጌታ ኢየሱስ በእነ አልአዛር ቤት በክብር እንግድነት ተገኝቶ ነበር። በዚያው ሰሞን ጌታ ኢየሱስ አልአዛርን ከሞት አስነስቶት ነበር። በቤት ውስጥ ያሉት እንግዶችም አልአዛር፣ እህቶቹ ማርታና ማርያም እንዲሁም ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤*

*"ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ። በዚያም እራት አደረጉለት፤ ማርታም ታገለግል ነበር፤ አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበረ። ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጕርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ። ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ። ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሽጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው? አለ። ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው። ኢየሱስም፦ ለምቀበርበት ቀን እንድትጠብቀው ተውአት፤ ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ።" ዮሐ. 12፡1-8*

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ጢሞ. 6፡17-19፤ ሉቃ. 12፡32-34፤ 1 ቆሮ. 3፡10-17፤ ማር. 8፡34-38)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - *ጌታ ኢየሱስ ለዘለዓለማዊው መንግሥት የሚያበቃ ተግባርን እንድንፈጽም* ነግሮናል። እግዚአብሔር በኑሮአቸውና በሕይወታቸው የሚያከብሩትን ይሸልማል።

# አትዘን

ትምህርት
2-11

## እግዚአብሔር የሚያስፈልግህን ያውቃል፤ ይጠነቀቅልሃልም፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ጌታ ኢየሱስ ለእኛ ሕይወት እንደሚጠነቀቅና በችግሮቻችንም እንደሚረዳን ተናግሮአል፡፡ በችግራችን ጊዜ የምንጨነቅ ከሆነ እምነት የለንም ማለት ነው፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ - *"ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል፡፡" ማቴ. 6፡34***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በባህር ዳርቻ ነበር፡፡ ብዙዎቹ የጌታ ደቀ መዛሙርት በዚህ ባሕር ላይ በአንድ ወቅት አሳ አጥማጅ በመሆን ሰርተዋል፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"በዚያም ቀን በመሸ ጊዜ ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው፡፡ ሕዝቡንም ትተው በታንኳ እንዲያው ወሰዱት፥ ሌሎች ታንኳዎችም ከእርሱ ጋር ነበሩ፡፡ ብርቱ ዐውሎ ነፋስም ተነሣና ውኃ በታንኳይቱ እስኪሞላ ድረስ ማዕበሉ በታንኳይቱ ይገባ ነበር፡፡ እርሱም በስተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር፡፡ አንቅተውም፦ መምህር ሆይ፥ ስንጠፋ አይገድህምን? አሉት፡፡ ነቅቶም ነፋሱን ገሠጸው ባሕሩንም፦ ዝም በል፥ ፀጥ በል አለው፡፡ ነፋሱም ተወ ታላቅ ፀጥታም ሆነ፡፡ እንዲህ የምትፈሩ ስለ ምን ነው? እንዴትስ እምነት የላችሁም? አላቸው፡፡ እጅግም ፈሩና፦ እንግዲህ ነፋስም ባሕርም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? ተባባሉ፡፡"***
>
> ማር. 4፡35-41

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ምሳ. 3፡5-6፤ ሉቃ. 12፡22-25፤ ዕብ. 11፡8-12፤ ገላ. 2፡20፤ 1 ጴጥ. 1፡21)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

**መደምደሚያ -** ጌታ ኢየሱስ ስለ እያንዳንዱ የሕይወታችን ክስተት ጥበቃውን ያደርጋል፡፡ እኛ በእርሱ በመታመን ተስፋችንን ልንጥልበት ይገባል፡፡

# በሌሎች አትፍረድ

ትምህርት 2-12

## እግዚአብሔር ፈራጅ ነው፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

በሌሎች ሰዎች መፍረድ ስህተት ነው። ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው፤ በጽድቅ መፍረድ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል። በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፥ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም?"* ማቴ. 7፡1-3

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ፈሪሳውያን የሃይማኖት ሕግን ጠንቅቀው ያውቃሉ፤ ሕዝቡም ይህን የሃይማኖት ሕግ መታዘዝ እንደሚገባው በእርግጠኝነት ያምናሉ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

*"ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። ተቀምጦም ያስተምራቸው ነበር። ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርሱዋን አቁመው፦ መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች። ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት። የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ። ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤ መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ፦ ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው። ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ። እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች። ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ፦ አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት። እርስዋም፦ ጌታ ሆይ፥ አንድ ስንኳ አለች። ኢየሱስም፦ እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።"* ዮሐ. 8፡2-11

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ያዕ. 4፡12፤ ዮሐ. 8፡14-18፤ 1 ቆሮ. 4፡3-5፤ ሉቃ. 6፡37)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው፤ ሰዎች በጽድቅ ሊፈርዱ አይችሉም።

# ጠይቅ፣ ፈልግ፣ አንኳኳ

ትምህርት 2-13

## እግዚአብሔር አሁን ለጸለይነው ጸሎት ምላሽ አለው፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ጌታ ኢየሱስ እርሱን በምንጠይቅ፣ በምንፈልግ፣ በምናንኳኳ ጊዜ እርሱ ምላሹን እንደሚሰጥ አስተማረ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት መሠረት እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ ልንጠይቀው እንችላለን፡፡ አልፎ አልፎ የጸሎት ጥያቄያችን ወዲያውኑ ላይመለስ ይችላል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል፡፡ የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል፡፡"*** ማቴ. 7፡7-8

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሁል ጊዜ መጸለይ እንዳለባቸውና ተስፋ መቁረጥ እንደማያስፈልግ በምሳሌ አስረዳቸው፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"እንዲህ ሲል፡- በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ፡፡ በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፥ ወደ እርሱም እየመጣች፡፡ ከባላጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር፡፡ አያሌ ቀንም አልወደደም፤ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ፡- ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር፥ ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜም እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ፡፡ ጌታም አለ፡- ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ፡፡ እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? እላችኋለሁ፥ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?" ሉቃ. 18፡2-8***

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ዮሐ. 3፡21-22፣ 1 ዮሐ. 5፡14-15፤ *ዕብ.* 4፡16፤ *ያዕ.* 4፡2-3፣ *ያዕ.* 5፡16፤ ኤፌ. 6፡18፤ ቆላ. 4፡12)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17) ገጽ ተመልከት፡፡

**መደምደሚያ** - ጌታ ኢየሱስ ሁልጊዜ መጸለይ እንዳለብንና ልባችን መውደቅ እንደማይገባው አስተማረ፡፡ በአሁኑ ወቅትም በምንጸልይበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ ምላሽ ይሰጣል፡፡

# የደቀመዝሙር ቡድንን መምራት

## አምልኮና ጸሎት

- እግዚአብሔር በስብሰባው መሃል እንዲሆን በጸሎትና በአምልኮ ጋብዙት፤
- ምስጋናን ለማቅረብና ለምስክርነት ጊዜ መድቡ።

## የትምህርቱ ግኝትና የማዛመድ ጊዜ

### ደረጃ 1 - የትምህርቱ ጭብጥ

- ከቡድኑ ጋር የትምህርቱን ጭብጥና የቁልፍ ቃሉን ሃሳብ ተከፋፈሉ።

### ደረጃ 2 - የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

- የመግቢያውን ነጥብና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን ሃሳብ ከቡድኑ ጋር ተከፋፈሉ።

### ደረጃ 3 - የግኝት ሂደት

- ታሪኩን እወቁት፣
- ታሪኩን ተረዱት፣
- የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ጨብጡ።

### ደረጃ 4 - ተጨማሪ የቃሉ ጥናት

- ቡድኑ ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንዳገኘ ለማወቅ ተገቢው መጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ተግባራዊ ርምጃ መኖሩን ፈትሹ።

### ደረጃ 5 - ማዛመድና መደምደሚያ

ከታሪኩ በተገኘው ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤና ተግባራዊ ርምጃ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ። (ማስተማር)

- እኔ የተሳሳተ ግንዛቤና የተሳሳተ የድርጊት ርምጃ አለኝን; (ወቀሳ)
- እንዴት አስተሳሰቤንና የድርጊት ርምጃዬን ማስተካከል እችላለሁ; (ራስን ማረም)
- እንዴት ትክክለኛ አስተሳሰብና የድርጊት እርምጃን በቋሚነት በመያዝ መቀጠል እችላለሁ? (ሥልጠና)

## በማኅበረሰቡ ውስጥ መኖር

### በክርስቶስ ማደግ

- የቡድኑ አባላት ባለፈው የደቀመዝሙር ትምህርት ላይ የተማሩትን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ጠይቃቸው።

### ከሌሎች ጋር የተማሩትን እውነት መከፋፈል

- የቡድኑ አባላት ባለፈው የደቀመዝሙር ትምህርት ላይ የተማሩትን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ጠይቃቸው። በቡድኑ ውስጥ በአሁኑ ጥናትና በሚቀጥለው የደቀመዝሙር ጥናት መሃከል የሚነሱ ትምህርቶችን እንዴት ለሌሎች የቡድኑ አባላት እንደሚያካፍሉ ጠይቃቸው።

### ርዳታ የሚፈልጉትን መንከባከብ

- ካለፈው የቡድኑ የአገልግሎት ትምህርት በመነሳት ከማኅበረሰቡ እርዳታ የሚፈልጉትን እንዴት ባለ ምላሽ መርዳት እንደሚችሉ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው፤
- በቡደኑ ውስጥ ማናቸውም ዓይነት አዲስ የሆነ ትኩረት የሚሻ ችግር ወይም ማኅበረሰቡ ግንዛቤ ሊያገኝበት የሚያስፈልግ ጉዳይ ካለ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው፤
- ቡድኑ ትኩረት ለሚሻው ጉዳይ ወይም ችግር እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው።

# ወደ ፍሬያማነትና መብዛት

## መጠራት

በተፈጥሮ ውስጥ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሲፈጥር "ፍሬያማና" "የመባዛት" ችሎታ ያለው አድርጎ እንደሆነ እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊው የፍጥረት አሰራር የሚያመላክተን ሁሉም ሕያው ፍጥረታት "ራሳቸውን መሰል ፍጡር" ለመውለድ እንደተፈጠሩ ነው። እግዚአብሔር ሰውንም ሲፈጥረው ይህ የፍሬያማነትና የመባዛት መርህ አልተለወጠም። ***"እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው። ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።"*** ዘፍ. 1፡27-28

እኛ ከመጀመሪያውም ፍሬን እንድናፈራና ምድርን እንድንሞላ በእግዚአብሔር ተባርከን የተፈጠርን ነን። ላለፉት 6000 ዓመታት የሰው ልጅ ይህንን ሕግ በመታዘዝና ምድርን በመሙላት እየተጋ ይገኛል። ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜም የሰው ልጆች ዳግመኛ በመወለድ የሚገኘውን መንፈሳዊነትና እንደገና የመወለድን አስፈላጊነት እንዲለማመዱ አስተማረ። ዳግመኛ ካልተወለዱ በስተቀር ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት እንደማይቻልም አስረግጦ ተናገረ። ጌታ ኢየሱስ ሲመልስም፤ ***"ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።"*** ዮሐ. 3፡5-6

ክርስቶስ ወደ አዲስ ሕይወት ጠርቶናል። ይህ አዲስ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ እንደገና መወለድ ነው። ዳግመኛ አዲስ መወለዳችንን በሕዝብ ፊት በውኃ በመጠመቅ እናሳያለን። ፍሬን እንድናፈራና እንድንበዛ የተሰጠን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በእኛ ዳግመኛ በመንፈስ መወለድ ይከናወናል። በክርስቶስ ባገኘነው አዲስ ሕይወት ውስጥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለመዋለድ ትዕዛዙና እድሉ ተሰጥቶናል። ***"ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"***

ማቴ. 28፡18-20


ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት በማምጣት ደቀ መዝሙር ለማድረግና ለማጥመቅ በክርስቶስ ተጠርተናል። መንፈሳዊ ፍሬን የሚያፈራና በመንፈስ ዳግመኛ በመዋለድ የሚበዛ ሕይወት እንዲኖረን ተጠርተናል። ፍሬያማ የመሆንና ደቀ መዝሙርን የማብዛት ሥርዓተ ትምህርት ስልት የክርስቶስን ተከታዮች ደቀ መዝሙር ለማድረግ የተዘጋጀ ንድፍና እነርሱንም በማባዛት ውስጥ ወዳለ የመንፈሳዊ ፍሬያማነት ውጤት የሚያመራ ነው። ***"ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።"*** 1ኛ ጴጥ. 1፡23

ጌታ አምላካችን በአስገራሚ ፍሬያማነትና በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ ውስጥም በመንፈስ ዳግም ውልደት መብዛት በእውነት ይባርካችሁ። ይህች ምድራችንም ለእግዚአብሔር መንግስት በተወለዱ ሰዎች ተሞልታ ለማየት ያብቃን!

# አፍራ ብዛ

www.iBFAM.org

ፍሬያማና የምትበዛ ሁን!



# የተትረፈረፈ ሕይወት

## ትምህርት 3 ግድግዳው

*“ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ::” ዮሐ. 10:10*

# ፍሬያማና የምትበዛ ሁን
## ተግባራዊ የደቀመዝሙርነት ሞዴል እና ሥርዓተ ትምህርት

**የማዕዘን ድንጋይ ትምህርት ፡ ከ 1-4 የተዘጋጁ ጠቃሚ ትምህርቶች**

አሳታሚ ፡ Every Home for Christ

አድራሻ ፡
Every Home for Christ International
640 Chapel Hills Dr., Colorado Springs, CO 80920 USA
(719)-260-8888
BFAM@ehc.org
www.iBFAM.org

Copyright © 2011 by Every Home for Christ

ይህን የጥናት ማቴሪያል ከዚህ በታች በተገለጸው ደንብ መሠረት እንደገና ማባዛትና ማሰራጨት ይፈቀዳል፡፡

- አዘጋጁ "ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል ነው" በማለት ለደራሲው ተገቢውን ዋጋ በመስጠት፤
- ኤቭሪ ሆም ኢቫንጀሊዝም ይህን ማቴሪያል የትና እንዴት መጠቀም እንደሚገባ የሰጠውን ማሳሰቢያ ጠብቆ በመስራት፤
- ለማባዛት ከሚበዛ ወጪ በስተቀር ለሽያጭ ዓላማ ካልዋለ፡፡

አውዱን ጠብቆ የትርጉምና የማዛመድ ሥራ የሚከተሉትን ነጥቦች እንዲያካትት ይበረታታል፡፡

- ትርጉሙ በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል አስተባባሪነት በኩል ይሠራል፤
- የትርጉምና የጥቅስ አጠቃቀም የባለቤትነት መብት የኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ለመሆኑ እውቅና ለመስጠት ስምምነት ይደረጋል፤
- ማንኛውም ይዘቱን የተመለከተ ከአውዱ ጋር የሚዛመድ ሥራ በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት መጽደቅ ይኖርበታል፤
- የመጨረሻው በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የጸደቀው ቅጂ ለአርካይቭና ለሥርጭት ዓላማ ይቀመጣል፡፡ (ይህ ቅጂ በህትመት መልክና በዲጂታል ቅጂም ይቀመጣል)፡፡

| |
|---|
| የቢኤፍኤም ትምህርቶች፣ በደቀመዝሙርነት የማስተማር ዘዴ ላይ ያተኮሩ ሲሆን እያንዳንዱ ትምህርት ተገቢውን ጠቀሜታ አስገኝቶ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል፡፡ የቢኤፍኤምን የማስተማር ዘዴ የሚያስጨብጥ ሥልጠናን አግኝተህ ካልሆነ ወይንም ደግሞ የቢኤፍኤምን የሥልጠና መመሪያ ካላገኘህ፣ ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የሥልጠናውን ጊዜ እንዲያመቻችልህ እባክህን በአድራሻችን አግኘን፡፡ |

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከ1963 ዓ.ም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የተወሰደ ነው፡፡

አከፋፋይ ፡ ኤቭሪሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል

# ግድግዳው

## ትምህርት 3 ማውጫ


መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------------- ገጽ 4

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የግኝት ሂደት ---------------------------------------- ገጽ 6


## ትምህርቶች


**3.1 ክርስቶስን መከተል** ---------------------------------------------------- **ገጽ 8**

ኢየሱስ እንድንከተለው ጠርቶናል

**3.2 ክርስቶስን መከተል** ---------------------------------------------------- **ገጽ 9**

ክርስቶስን መከተል በእርሱ ተስፋ ማድረግና መታመንን ይጠይቃል

**3.3 ክርስቶስ መከተል** ---------------------------------------------------- **ገጽ 10**

ክርስቶስን የሚከተሉ ሁሉ ሌሎችን ይደርሳሉ

**3.4 ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ተናገር** -------------------------------------------- **ገጽ 11**

ሌሎች ኢየሱስን እንዲከተሉ መምራት

**3.5 ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ተናገር** -------------------------------------------- **ገጽ 12**

ለሌሎች የምስራቹን ቃል ተናገር

**3.6 ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ተናገር** -------------------------------------------- **ገጽ 13**

በርካታ ሰዎች የምሥራቹን ቃል ለመስማት ዝግጁ ናቸው

**3.7 እግዚአብሔርን መውደድ** ------------------------------------------------ **ገጽ 14**

ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትን ማድረግ ዋና ጉዳይ ነው

**3.8 እግዚአብሔርን መውደድ** ------------------------------------------------ **ገጽ 15**

መልካሙን እረኛ ማወቅ

**3.9 ሌሎችን መውደድ** ---------------------------------------------------- **ገጽ 16**

ከሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ጋር አንድነትን በመጠበቅ መኖር

**3.10 ሌሎችን መውደድ** ---------------------------------------------------- **ገጽ 17**

ለዓለም ብርሃን መሆን

**3.11 ደቀመዛሙርትን ማፍራት** ------------------------------------------------ **ገጽ 18**

በጎቼን መግቡ፤

**3.12 ደቀመዛሙርትን ማፍራት** ------------------------------------------------ **ገጽ 19**

ሌሎችን ደቀመዛሙርት በማድረጉ ሥራ ኢየሱስ ከኛ ጋር ነው፤

**3.13 ደቀመዛሙርትን ማፍራት** ------------------------------------------------ **ገጽ 20**

አማኞችን ማጠናከርና ማበረታታት

**የደቀ መዝሙር ቡድኖችን መምራት** -------------------------------------------- **ገጽ 21**

# ፍሬያማና የምትበዛ ሁን

## መግቢያ

"የፍሬያማና የምትበዛ ሁን" (አፍራ ብዛ) የትምህርት ኮርሶች የደቀመዛሙርነት የማስተማሪያ ስልትና ሥርዓተ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች ከአንዱ እውነተኛ ሕያው እግዚአብሔር ጋር ልዩ የሆነ ኅብረት እንዳላቸው ለማስገንዘብ የተነደፈ ነው። የአፍራ ብዛ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች ከኢየሱስ ጋር ባላቸው ኅብረት የተትረፈረፈ ሕብረት ሊኖራቸው እንደሚችል ለማሳየት የተነደፈ ኮርስ ነው። ሰዎች እርስ በእርስ ኅብረት እንዲኖራቸው ተፈጥረዋል። ከዚህም በላይ፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው ተፈጥረዋል። የኃጢአት ውጤትም ሰዎች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት እንዲቋረጥ አድርጎአል። የተቋረጠው ይህ ኅብረት እኛ ሰዎች እርስ በእርሳችን ከተቋረጠው ተፈጥሮና ከእግዚአብሔር ጋር ውህደት እንዳይኖረን አድርጎአል።

በዚህም ምክንያት በዓለማችን ላይ ጦርነት፣ ረሃብ፣ ግድያ፣ ተላላፊ በሽታ፣ ሕመም፣ ፍርደ ገምድል መሪዎች፣ ፍትህ አልባ ማኅበረሰብም እንዲኖር ሆኖአል። ከኃጢአት የተነሳ ኅብረታችን ተቋርጧል። ኃጢአትን እንዴት እንደምናስወግድና እንዴትስ በተሃድሶ ኅብረትን መመሥረት እንደምንችል እስካልተረዳን ድረስ፣ መልካሙን ሕይወት ለመኖር ከሚያስችለን ሕይወት ርቀናል።

የምስራቹ ቃል እግዚአብሔር ከኃጢአት የመውጫውን መንገድና፣ የተቋረጠውን ኅብረትም ለማደስ ኃላፊነት እንደወሰደ ያመላክተናል። የአፍራ ብዛ ኮርስ ትኩረትም ይህን ማመልከት ነው። አፍራ ብዛ ሰዎች በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የምሥራቹን ቃል እንዴት እንደሚያነቡና እንደሚገነዘቡ ለማስተማር ይፈልጋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በታማኝነት እውነትን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ቃል ገብቶላቸዋል:: ***"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል"*** (ማቴ. 7፡7-8)። የአፍራ ብዛ ኮርስ ሰዎች እንዴት እንደሚጠይቁ፣ እንደሚፈልጉና እንደሚያንኳኩ ያስተምራል። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንዴት እንደሚያነቡና እውነትን እንዴት እንደሚፈልጉም ያስተምራል። እውነቱም እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ኃላፊነትን እንዲወስድና ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ማደስ እንደሚፈልግ ያስተምራል።

የእግዚአብሔርን እውነት በታማኝነት ለሚፈልጉ ሁሉ፣ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እውነት ማግኘት ለሚፈልጉ፣ ለእነርሱ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ እርቅ እንዲሆንላቸው ቃል ኪዳን ተገብቶላቸዋል። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት ሲታረቅ ያን ጊዜ የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራሉ።

ይህ ኮርስ "ፍሬያማና የምትበዛ ሁን" የተባለበት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት የምንኖረው የመጀመሪያ ደረጃ፤ እግዚአብሔር ፍሬያማ ሕይወት እንድንኖር አድርጎ እንደፈጠረን ለማሳወቅ ነው። ፍሬያማው ሕይወት በመንፈሳዊነት ወደ መባዛት ሕይወትም ያመራል።

# የደቀመዛሙርት ቡድኖችን መምራት

በዚህ ጥናት መጨረሻ ላይ የአፍራ ብዛ ትናንሽ ቡድን ሞዴሎች ተካተዋል። ትናንሾቹ የደቀመዝሙር ሞዴሎች ቡድን፣ ትናንሽ የቡድን ስብሰባ በአፍራ ብዛ የደቀመዝሙር ሞዴልና ሥርዓተ ትምህርት በመጠቀም እንዴት እንደምንመራ ያሳየናል።

# ጠቃሚ የሆኑት ተከታታይ ትምህርቶች

በአፍራ ብዛ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የተካተቱት የመጀመሪያዎቹ 52 ተከታታይ የሆኑ ትምህርቶች ተከታታይ ጠቃሚ ትምህርቶች ይባላሉ። እነኚህ ተከታታይ ትምህርቶች በአራት ክፍለ ትምህርቶች የተመደቡና እያንዳንዳቸው 13 ትምህርቶችን የያዙ የአንድ ዓመት ጥናቶች ናቸው። እነኚህ ጠቃሚ ተከታታይ ትምህርቶች ልክ ቤትን በመገንባት መልክ የተዋቀሩ ናቸው። አራቱ የተለያዩ ክፍለ ትምህርቶችም የማዕዘን ድንጋይ፣ መሠረት፣ ግድግዳና ጣራን ያካትታሉ። ከዚህ በታች የእነኚህ አራት ትምህርቶች ይዘት ተብራርቷል።



## የማዕዘን ድንጋይ ክፍለ ትምህርት - የማስታረቅ ኅብረት

የማዕዘን ድንጋይ ክፍለ ትምህርቶች በማስታረቅ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። እግዚአብሔር እንዴት ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ከሚያስረዳው ፍጥረተ ትምህርትም ይጀምራል። ይህ እውነትም ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ንጽረተ ዓለም ያስጨብጠናል። ሁለተኛው ትምህርትም የሰው ልጅ ከሌላው ፍጥረት የተለየ ሆኖ እንደተፈጠረ ያስጨብጠናል። እኛ የተፈጠርነው ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ኅብረት እንዲኖረን ነው። ሦስተኛውና አራተኛው ትምህርትም የሰው ልጅ እንዴት በሰይጣን እንደተታለለ ያሳያል። የመጀመሪያው ሰው እግዚአብሔርን አልታዘዘም፤ በዚህም ምክንያት እኛ ሁላችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕብረት ተቋረጠ። የቀረው የትምህርቱ ክፍል እግዚአብሔር ይህን የተቋረጠ ኅብረት እንደገና ለማደስና የሰውን ልጅ ለመዋጀት የዘረጋውን የማስታረቅ ዕቅድ ያሳየናል።



## መሠረት የመጣል ክፍለ ትምህርት - ከክርስቶስ ጋር መዝለቅ

ይህ የትምህርት ክፍል መሠረት ያደረገው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዛት የመፈጸምን አስፈላጊነት ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር ***"ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።"*** (ማቴ. 7፡24) መሠረት የመጣል ክፍለ ትምህርት በመታዘዝ የአኗኗር ዘዬ ውስጥ የሚገኘውን ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትን ያሳያል።




## የግድግዳ ክፍለ ትምህርት - የተትረፈረፈ ሕይወት

የአንድ ቤት ግድግዳ ከቤቱ ውጪ ያሉ ሰዎች ሁሉ በግልጽ የሚመለከቱት ነው። የክርስቶስ ተከታዮችም ልክ እንደዚሁ ናቸው። የክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔርን በምድር ላይ የሚወክሉ ናቸው። እነኝህ የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔር ተወካይ እንደመሆናቸው መጠን በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች እግዚአብሔርን በመምሰልና በድርጊታቸውም በመግለጽ የሚያሳዩ መሆን ይገባቸዋል። ይህ ክፍለ ትምህርት በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን ቤተሰቦች አስፈላጊነት ዓላማ ላይ ያተኩራል።




## የጣሪያ ክፍለ ትምህርት - ጠቃሚ እውነት

ይህ የመጨረሻ ክፍለ ትምህርት የክርስትናን እምነት መሠረታዊ እውነት ያካትታል። ጣራው ውጫዊ ወይም አላስፈላጊ የሆነውን ነገር እንድንከላከል ተደርጎ ተነድፎአል። የጣሪያ ክፍለ ትምህርት የሐሰት ትምህርትን ለመከላከል የክርስትናን እምነት መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በማሳየት የሐሰትን ትምህርት የመከላከል ንድፍ ነው።




***"እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።"*** ኤፌ. 2፡19-22

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማኝት ሂደት






**የትምህርቱ ጭብጥ - መሬቱን ማዘጋጀት**

የትምህርቱ ጭብጥ ደቀመዝሙር ለሚሆኑት ሰዎች ዘር የሚዘራብትን አዕምሮና ልብን በማሳደግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገኘው እውነት እነርሱን ማዘጋጀት ነው፡፡



**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - ዘሩን መዝራት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በለማው መሬት  ውስጥ የሚዘራው ዘር ሲሆን ከተዘራ በኋላ የእውቀትና የአርነት ፍሬን የሚያፈራ ይሆናል፡፡



**የመገንዘብ ሂደት - ውኃና ማዳበሪያ**

የግንዛቤ ሂደት ጥያቄዎች ዘሩን ውኃ እንደማጠጣትና ማዳበሪያ እንደመጠቀም ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል፣ የታሪኩን እውነት ለመግለጥ ይረዳል፡፡



**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - ማጣት / መግረዝ**

ተጨማሪ የቃሉ ጥናት በታሪኩ ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚገነባ / አስተምህሮ እንዳይኖርም ይከላከላል፡፡



**የተግባር ጥያቄዎችና መደምደሚያ -**

የተግባር ጥያቄዎችና መደምደሚያው በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ያለውን የአዘመራውን ውጤት ለመሰብሰብና በሕይወታችን ውስጥ የተረዳነውን እውነት እንድንተገብረው ይረዳናል፡፡



# የትምህርቱ ቅደም ተከተል

## ደረጃ 1 - መሬቱን ማዘጋጀት — የትምህርቱ ጭብጥ

## ደረጃ 2 - ዘር መዝራት — የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

## ደረጃ 3 - ውኃና ማዳበሪያ — የግኝት ሂደት

### ታሪኩን ማወቅ - መጠየቅ

**ማን ነው? ተግባሩ ምንድን ነው? ታሪኩን በጥልቀት ማወቅ፤**

- በታሪኩ ውስጥ ያሉት ገጸ ባሕርያት እነማን ናቸው?
- የገጸ ባሕርያቱ ድርጊት ምንድን ናቸው?
- በታሪክ ውስጥ ያለው ግልጽ የሆነ ጥልቅ ጉዳይ ምንድን ነው?

### ታሪኩን መረዳት - መፈለግ

**ፍልቅ ስሜት፣ የመነሻ ምክንያትና ምርጫ**

- ገጸ ባሕርያቱ የተሰማቸው ፍልቅ ስሜት ምን ይመስላል;
- ገጸ ባሕርያቱን ለድርጊት ያነሳሳቸው መነሻ ምክንያት ምንድን ነው;
- ገጸ ባሕርያቱ የወሰዱአቸው ልዩ ልዩ ምርጫዎች ምንድን ናቸው?

### የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታን ማግኘት - ማንኳኳት

**ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤና ርምጃ**

- የገጸ ባሕርያቱን ድርጊት፣ ጥልቅ ጉዳይ፣ ፍልቅ ስሜት፣ መነሻ ምክንያትና ምርጫ በጥንቃቄ ስትመለከት ምን ትማራለህ?

## ደረጃ 4 - መግረዝ — ተጨማሪ የቃሉ ጥናት

## ደረጃ 5 - መከሩን መሰብሰብ — የማዛመድ ጥያቄና መደምደሚያ

> ***"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።"*** 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17

በታሪክ ውስጥ በተዳሰሰው ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳትና ተግባራዊነት መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ (ማስተማር)

- እኔ የተሳሳተ ግንዛቤና ድርጊት አለኝን; (ተግሳጽ)፤
- የተሳሳተ ግንዛቤዬንና ተግባሬን እንዴት ማስተካከል እችላለሁ (ማቅናት)፤
- እንዴት ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታና ግንዛቤ ጨብጬ መጓዝ እችላለሁ? (ሥልጠና)

# ክርስቶስን መከተል

ትምህርት 3-1

## ኢየሱስ እንድንከተለው ጠርቶናል

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ሰዎች እንዲከተሉት ይፈልጋል። የክርስቶስ ተከታዮች የእርሱን መንገድና ትምህርት በማጤን የሚከተሉት ናቸው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፡- እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል።" ማቴ. 16፡24-25***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

***የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።***

ጌታ ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎቱን በጀመረበት ወቅት ካደረጋቸው የመጀመሪያ ተግባሮቹ ውስጥ አንዱ ደቀ መዛሙርቱ እርሱን እንዲከተሉትና የእርሱን መንገድ እንዲማሩ መጥራቱ ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስም ሁለት ወንድማማች ጴጥሮስ የሚሉትን ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። እርሱም፡- በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው። ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት። ከዚያም እልፍ ብሎ ሌሎችን ሁለት ወንድማማች የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በታንኳ መረባቸውን ሲያበጁ አየ፤ ጠራቸውም። እነርሱም ወዲያው ታንኳይቱንና አባታቸውን ትተው ተከተሉት።"*** **ማቴ. 4፡18-22**

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማቴ. 19፡21፤ ዮሐ. 8፡12፣ ዮሐ. 10፡27፤ ሉቃ. 9፡57-62)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - ኢየሱስ የእርሱን መንገድ እንድናጤንና እንድንከተል ጠርቶናል።

# ክርስቶስን መከተል

ትምህርት 3-2

## ክርስቶስን መከተል በእርሱ ተስፋ ማድረግና መታመንን ይጠይቃል

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ክርስቶስን መከተል ማለት እምነታችንና ተስፋችን በሙሉ በእርሱ ላይ ማስቀመጥ ነው፡፡ በሕይወታችን ውስጥ ያለ ማንኛውም እምነትና ተስፋ ኢየሱስን በሙላት እንድንከተል የሚረዳን መሸጋገሪያ ሊሆን ይችላል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል።" ማቴ. 16:24-25***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

ሐብት ሰዎች እምነትና ተስፋቸውን ከሚያኖሩባቸው ነገሮች አንዱ ነው፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ የምንመለከተው ወደ ኢየሱስ የቀረበው ሰው ሐብታም ነበረ፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"እነሆም፥ አንድ ሰው ቀርቦ፦ መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? አለው። እርሱም፦ ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው። እርሱም፦ የትኞችን? አለው። ኢየሱስም፦ አትግደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው። ጐበዙም፦ ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ፥ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው? አለው። ኢየሱስም፦ ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሄደህ ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው። ጐበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ።"*** ማቴ. 19:16-22

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማቴ. 6:19-21፤ ምሳ. 3:5-6፤ ሮሜ 15:13፤ 1 ተሰ. 1:3)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

**መደምደሚያ -** የክርስቶስ ተከታዮች እምነታቸውንና ተስፋቸውን በእርሱ ላይ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

# ክርስቶስን መከተል

**ትምህርት 3-3**

## ክርስቶስን የሚከተሉ ሁሉ ሌሎችን ይደርሳሉ፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ የጠፋትን ለመፈለግና ለማዳን መጣ፡፡ የክርስቶስ ተከታይ መሆን ማለት ልክ ኢየሱስ እንዳደረገ የጠፉትን በወንጌል መድረስ ማለት ነው፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል።" ማቴ. 16፡24-25***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

ጌታ ኢየሱስ በመላው ሃገር እውነትን አስተማረ፡፡ በርካታ ሰዎችም ኢየሱስ ያስተማረውን ትምህርት ለመስማት መጡ፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ደግሞም በባሕር አጠገብ ወጣ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡና አስተማራቸው። ሲያልፍም በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረውን የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን አየና። ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው። በቤቱም በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጡ፤ ብዙ ነበሩ ይከተሉትም ነበር። ጻፎችና ፈሪሳውያንም ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ሲበላ አይተው ለደቀ መዛሙርቱ፦ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር የሚበላና የሚጠጣ ስለ ምንድር ነው? አሉ። ኢየሱስም ሰምቶ፦ ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው።" ማር. 2፡13-17***

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ምሳ. 19፡17፤ ሉቃ. 15፡1-31፣ ሉቃ. 19፡10፤ ገላ. 6፡9-10፤ ያዕ. 3፡18)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

**መደምደሚያ -** እንደ ክርስቶስ ተከታይነታችን፣ ልክ ኢየሱስ የጠፉትን እንደፈለገ እኛም በአካባቢያችን ያሉትን፣ የጠፉትን ሰዎች እንደርሳቸዋለን፡፡

# ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ተናገር

ትምህርት 3-4

## ሌሎች ኢየሱስን እንዲከተሉ መምራት

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ኅብረት ማድረግ ይፈልጋል። እንደ ክርስቶስ ተከታይ ሌሎች ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው ልንመራ ተጠርተናል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?" ሮሜ. 10:14-15***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ስምዖን ጴጥሮስ የጌታ ተከታይ ከመሆኑ በፊት የሰለጠነ አሣ አጥማጅ ነበር። በዚህ ታሪክ ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን የሰው አጥማጅ እንዲሆን ሲጠራው እናያለን።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃል እየሰሙ ሲያስጠብቡት ሳሉ፥ እርሱ ራሱ በጌንሳሬጥ ባሕር ዳር ቆሞ ነበር፤ በባሕር ዳርም ቆመው የነበሩትን ሁለት ታንኳዎች አየ፤ ዓሣ አጥማጆች ግን ከእነርሱ ውስጥ ወጥተው መረቦቻቸውን ያጥቡ ነበር። ከታንኳዎቹም የስምዖን ወደ ነበረች ወደ አንዲቱ ገብቶ ከምድር ጥቂት ፈቀቅ እንዲያደርጋት ለመነው፤ በታንኳይቱም ተቀምጦ ሕዝቡን ያስተምር ነበር። ነገሩንም ከጨረሰ በኋላ፥ ስምዖንን፦ ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ አለው። ስምዖንም መልሶ፦አቤቱ፥ ሌሊቱን ሁሉ አድረን ስንደክም ምንም አልያዝንም፤ ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ አለው። ይህንም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረቦቻቸውም ተቀደዱ። በሌላ ታንኳም የነበሩትን ጓደኞቻቸውን መጥተው እንዲያግዙአቸው ጠቀሱ፤ መጥተውም ሁለቱ ታንኳዎች እስኪሰጥሙ ድረስ ሞሉአቸው። ስምዖን ጴጥሮስ ግን ባየ ጊዜ በኢየሱስ ጒልበት ላይ ወድቆ፤ ጌታ ሆይ፥ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከኔ ተለይ አለው። ስላጠመዱት ዓሣ እርሱ ከእርሱ ጋርም የነበሩ ሁሉ ተደንቀዋልና፥ እንዲሁም ደግሞ የስምዖን ባልንጀሮች የነበሩ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ተደነቁ። ኢየሱስም ስምዖንን፦ አትፍራ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ አለው። ታንኳዎችንም ወደ ምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ተከተሉት።"*** ሉቃ. 5:1-11

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማቴ. 28:18-19፤ 2 ጴጥ. 3:9፤ ዮሐ. 4:39-42)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - እግዚአብሔር ከሁላችንም ጋር ግንኙነት ይፈልጋል። የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን ሌሎች ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኙ የመምራት እድል ተሰጥቶናል።

# ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ተናገር

ትምህርት 3-5

## ለሌሎች የምሥራቹን ቃል ተናገር፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

መጽሐፍ ቅዱስ ሁላችንም የጌታን የምስራች ቃል ለሌሎች ሰዎች እንድንናገር ያዘናል። በዓለማችን ላይ ያሉ ሰዎች በሙሉ ይህንን ጌታ የሰጠውን የምሥራች ቃል የመስማት እድል ሊኖራቸው ይገባል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?" ሮሜ. 10፡14-15***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ጳውሎስ የታወቀ የወንጌል ሰባኪና አስተማሪ ነበር። በዚህ ታሪክ ውስጥ ጳውሎስ ወንጌልን ይሰብክ ነበር። ወንጌል እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ኅብረትን እንደሚፈልግ የሚናገር የምሥራች ቃል ነው። እኛ ከጌታ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት የቻልነውም ጌታ ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን በመሞቱ ምክንያት ነው።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ራዕይም ለጳውሎስ በሌሊት ታየው፤ አንድ የመቄዶንያ ሰው። ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን እያለ ቆሞ ሲለምነው ነበር። ራዕዩንም ካየ በኋላ ወዲያው ወደ መቄዶንያ ልንወጣ ፈለግን፥ ወንጌልን እንሰብክላቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ጠራን መስሎናልና። ከጢሮአዳም ተነሥተን በቀጥታ ወደ ሳሞትራቄ በነገውም ወደ ናጱሌ በመርከብ ሄድን፤ ከዚያም ወደ ፊልጵስዩስ ደረስን፤ እርስዋም የመቄዶንያ ከተማ ሆና የወረዳ ዋና ከተማና ቅኝ አገር ናት፤ በዚህችም ከተማ አንዳንድ ቀን እንቀመጥ ነበር። በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ስፍራ በዚያ መሆኑን ስላሰብን ወደ ወንዝ አጠገብ ወጣን፤ ተቀምጠንም ለተሰበሰቡት ሴቶች ተናገርን። ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት። እርስዋም ከቤተ ሰዎችዋ ጋር ከተጠመቀች በኋላ፡- በጌታ የማምን እንድሆን ከፈረዳችሁልኝ፥ ወደ ቤቴ ገብታችሁ ኑሩ ብላ ለመነችን፤ በግድም አለችን።"*** ሐዋ. 16፡9-15

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማቴ. 10፡7-8፣ ማቴ. 28፤19-20፤ ማር. 16፡15፤ 1 ቆሮ. 2፡1-5፤ ሮሜ 1፡16-17)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ኢየሱስን የሚከተሉ ሁሉ የተጠሩት ለሌሎች የምሥራቹን ቃል እንዲናገሩና እያንዳንዱ ሰው በግሉ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረው ነው ይላል።

# ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ተናገር

ትምህርት 3-6

## በርካታ ሰዎች የምሥራቹን ቃል ለመስማት ዝግጁ ናቸው፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ክርስቶስ መከሩ ብዙ እንደሆነና ሠራተኞች ግን ትንሽ እንደሆኑ ይነግረናል። የምሥራቹን ቃል ለመስማት የሚጠባበቁ ብዙ ሰዎች አሉ። የክርስቶስ ተከታዮች የሆንን ለእነዚህ ሰዎች የምሥራቹን ቃል መንገር አለብን።

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?" ሮሜ 10:14-15***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዴት የምስራቹን ቃል ለሰዎች መናገር እንዳለባቸው መመሪያ ሰጥቷቸዋል።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ከዚህም በኋላ ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ፥ ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው። አላቸውም፦ መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዴህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት። እነሆ፥ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ። ኮረጆም ከረጢትም ጫማም አትያዙ፤ በመንገድም ለማንም እጅ አትንሡ። ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ፦ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ። በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር፥ ሰላማችሁ ያድርበታል፤ አለዚያም ይመለስላችኋል። በዚያም ቤት ከእነርሱ ዘንድ ካለው እየበላችሁና እየጠጣችሁ ተቀመጡ፤ ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና። ከቤት ወደ ቤት አትተላለፉ። ወደምትገቡባትም ከተማ ሁሉ ቢቀበሉአችሁ፥ ያቀረቡላችሁን ብሉ፤ በእርስዋም ያሉትን ድውዮችን ፈውሱና፦ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀረበች በሉአቸው።" ሉቃ.*** 10:1-9

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

(ገጽ 7 ተመልከት)

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ማቴ. 9:35-38፤ ዮሐ.4:35-38፤ ኢሳ. 6:8፤ ገላ. 6:9-10)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17) ገጽ ተመልከት።

**መደምደሚያ -** እኛ ሁላችን ለወንጌል የምሥራች ቃል ትልቅ ፍላጎት ሊኖረን ይገባል። በዙሪያችን ላለው የዓለም ሕዝብ ይህን የምሥራች ቃል የማካፈል ዕድሉ አለን።

# እግዚአብሔርን መውደድ

ትምህርት 3-7

## ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ ዋና ጉዳይ ነው፤

**የትምህርቱ ጭብጥ -** *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ለተከታዮቹ ብዙ ነገር እንዲያደርጉ ጠየቋቸው ነበር። በጣም የሚያስፈልገው ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት፤ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።" ማር. 12፡30***

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ** - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ማርያምና ማርታ የኢየሱስ ተከታዮችና ከእርሱም ጋር ጥሩ ኅብረት የነበራቸው ነበሩ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ሲሄዱም እርሱ ወደ አንዲት መንደር ገባ፤ ማርታ የተባለች አንዲት ሴትም በቤትዋ ተቀበለችው። ለእርስዋም ማርያም የምትባል እኅት ነበረቻት፥ እርስዋም ደግሞ ቃሉን ልትሰማ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ ነበረች። ማርታ ግን አገልግሎት ስለ በዛባት ባከነች፤ ቀርባም፦ ጌታ ሆይ፥ እኄ እንድሠራ እኅቴ ብቻዬን ስትተወኝ አይገድህምን? እንኪያስ እንድታግዘኝ ንገራት አለችው። ኢየሱስም መልሶ፦ ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት።" ሉቃ.*** 10፡38-42

**የግኝት ሂደት -** *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት -** *መግረዝ*

(ዮሐ. 14፡15፤ ማቴ. 11፡28-30፤ ፊሊ. 2፡12-13፤ ሉቃ. 6፡47-49)

**የማዛመድ ጥያቄዎች -** *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ -*** በኢየሱስ ከተሰጡት ትዕዛዛት በጣም አስፈላጊ የሆነው በፍጹም ልባችን፣ በፍጹም ነፍሳችን፣ በፍጹም ሃሳባችንና በፍጹም ኃይላችን እርሱን መውደዳችን ነው።

# እግዚአብሔርን መውደድ

ትምህርት 3-8

## መልካሙን እረኛ ማወቅ

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

የክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔር አምላካቸውን በሁለመናቸው ሊወዱት ይገባል። እግዚአብሔርን በሁለንተናችን እንድንወደው ታድያ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ማወቅ አለብን።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት፤ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።" ማር. 12፡30***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ እርሱን የሚከተሉትን በበግ ምሳሌነት የገለፃቸው ሲሆን በጎቹ እረኛቸውን ይከተላሉ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ኢየሱስም ደግሞ አላቸው፤- እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ። ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸውም። በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል። ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ። መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኵላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል። ሞያተኛ ስለ ሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል። መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ።" ዮሐ. 10፡7-14***

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(*መዝ.* 23፣ *መዝ.* 100፤ *ማቴ.* 9፡35-36)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - እግዚአብሔርን ስናውቀው እንወደዋለን።

# ሌሎችን መውደድ

ትምህርት 3-9

## ከሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ጋር አንድነትን በመጠበቅ መኖር

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

የክርስቶስ ተከታዮች በአንድነት ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በሰላምና በአንድነት እንድትኖር ይፈልጋል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ. . .።" ማር. 12፡31*

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ዘመን ይቃወሙት የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች፤ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ኢየሱስ እንዳይሰብኩና እንዳይመሰክሩ ያዟቸው ነበር። ቤተ ክርስቲያንም እግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጥ በኅብረት ትጸልይ ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> *"አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው። ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ። ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፥ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም። ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው። በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፥ በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር፤ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር።* ሐዋ. 4፡29-35

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ቆሮ. 12፡12-31፣ 1 ቆሮ. 14፡26፤ ኤፌ. 4፡1-16፤ ሮሜ 12፡3-21)

**የማዛመድ ጥያቄዎች -** *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ -** እኛ ከሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ጋር በኅብረት እንድንኖር ተጠርተናል።

# ሌሎችን መውደድ

ትምህርት 3-10

## ለዓለም ብርሃን መሆን

**የትምህርቱ ጭብጥ -** *መሬቱን ማዘጋጀት*
ኢየሱስ ተከታዮቹን ሌሎች ሰዎችን እንዲወዱ አዟቸው ነበር። ክርስቲያኖች የተስፋን መልዕክት በማምጣት ለዓለም ሰላም እንዲሆኑ ተጠርተዋል። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፍቅር ለተጠሙ ፍቅሩን እንዲያሳዩ ታዘዋል።

**ቁልፍ ጥቅስ - *"ሁለተኛይቱም፦ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም።" ማር. 12፡31***

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ** - *ዘሩን መዝራት*
**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**
መጽሐፍ ቅዱስ ጎረቤታችንን እንድንወድ ያስተምረናል። የሃይማኖት አዋቂው ኢየሱስን የኔ ጎረቤት ማነው ሲል ጠየቀው። ኢየሱስ መልሱን ሲሰጥ የካህኑን፣ የሌዋዊውንና፣ የሰማርያዊውን ሰው ምሳሌ ነገረው። ሌዋዊያንና ካህናቱ በሃይማኖት የበረቱ ነበሩ። ሰማሪያውያን ደግሞ ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት ሰዎች ጋር የማይዛመዱ ሰዎች ናቸው።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፦ አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ። ድንገትም አንድ ካህን በዚያ መንገድ ወረደ አይቶትም ገለል ብሎ አለፈ። እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ ወደዚያ ስፍራ መጣና አይቶት ገለል ብሎ አለፈ። አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት፥ ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቍስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው፥ በራሱ አህያም ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደርያ ወሰደው ጠበቀውም። በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና፦ ጠብቀው፥ ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው። እንግዲህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል? እርሱም፦ ምሕረት ያደረገለት አለ። ኢየሱስም፦ ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ አለው።" ሉቃ. 10፡30-37***

**የግኝት ሂደት -** *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት -** *መግረዝ*
(1 ዮሐ. 3፡16-18፣ 1 ዮሐ. 4፡7-12፤ ዮሐ. 13፡34-35፤ ማቴ. 5፡14-16፤ ኤፌ. 4፡1-3፤ 1 ቆሮ. 13)

**የማዛመድ ጥያቄዎች -** *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ -** እርዳታ ለሚፈልጉ እርዳታ ስንሰጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች እናሳያለን። ለሌሎች ሰዎች በምናሳየው እንክብካቤ የእግዚአብሔርን ፍቅር እናሳያለን።

# ደቀ መዛሙርትን ማፍራት

ትምህርት 3-11

**በጎቼን መግቡ**

## የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

የእግዚአብሔር ፍቅር ሌሎችን እንድናሰለጥንና እንድንንከባከብ ያነሳሳናል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጒብኙት።" 1ኛ ጴጥ. 5፡2*

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ ተሰቅሎ ከሙታንም ተነስቶ ነበር። አንድ ቀን ጠዋት ኢየሱስ ተከታዮቹን አሣ ሲያጠምዱ አገኛቸው።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ኢየሱስም፡ ኑ፥ ምሳ ብሉ አላቸው። ከደቀ መዛሙርቱ አንድ ስንኳ አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊመረምረው የደፈረ አልነበረም፤ ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና። ኢየሱስም መጣና እንጀራ አንሥቶ ሰጣቸው፥ እንዲሁም ዓሣውን። ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥላቸው ይህ ሦስተኛው ጊዜ ነበረ። ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፤ ግልገሎቼን አሰማራ አለው። ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው። ሦስተኛ ጊዜ፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው። ሦስተኛ ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ኢየሱስም፦ በጎቼን አሰማራ።" ዮሐ. 21፡12-17***

## የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

## ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ተሰ. 5፡11፤ ማቴ. 28፡19-20፤ 2 ጢሞ. 2፡2፣ 2 ጢሞ. 4፡2-5፤ ሐዋ. 20፡28፤ 1 ቆሮ. 9፡16-18)

**የማዛመድ ጥያቄዎች** - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - ኢየሱስ ለተከታዮቹ ደቀ መዛሙርትን እንዲያፈሩ ነግሮአቸው ነበር። ደቀ መዛሙርት ማፍራት ማለት አማኞችን መደገፍና ማስተማር ሲሆን ከዚህም የተነሳ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ኅብረት እንዲያድጉ ማድረግ ይሆናል።

# ደቀ መዛሙርትን ማፍራት

ትምህርት 3-12

## ሌሎችን ደቀ መዛሙርት በማድረግ ሥራ ኢየሱስ ከእኛ ጋር ነው፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ሁሉንም ሰው ከመውደዱ የተነሳ ያላመኑትን ሰዎች ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጓቸው ለተከታዮቹ ተናግሮአል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ጌታን ለማያውቁት ሄደው ሲመሰክሩ አብሮአቸው እንደሚሆንና እንደሚረዳቸው ቃል ገብቶአል።

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት።" 1ኛ ጴጥ. 5፡2***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

***የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።***

ኢየሱስ ተሰቅሎ በመቃብር ውስጥ ለሦስት ቀናት ቆይቶአል። የእርሱ ተከታዮች በሦስተኛው ቀን መቃብሩ ባዶ እንደነበር አውቀዋል።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወዳዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ፥ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ። ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" ማቴ. 28፡16-20***

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ዮሐ. 14፡15-17፤ ዕብ. 13፡5-6፤ 2 ጢሞ. 2፡2፤ ሐዋ. 2፡42-47)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17) ገጽ ተመልከት።

**መደምደሚያ -** ደቀ መዛሙርቱን፣ ሌሎችን ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ አዟቸዋል። የኢየሱስ ተከታዮች አዲስ አማኞችን ስለ ኢየሱስ እንዲያስተምሩ የተጠሩ ሲሆን በዚህም ምክንያት አዳዲሶቹ አማኞች በክርስቶስ ላይ ባላቸው እውቀትና እምነት ማደግ ይችላሉ።

# ደቀ መዛሙርትን ማፍራት

ትምህርት 3-13

## አማኞችን ማጠናከርና ማበረታት

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

እንደ አማኞች በእምነታችን ልንበረታና ልንጠነክር ይገባል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ሁላችንም እርስ በራሳችን ልንማማርና ልንበረታታ ይገባል፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፡፡" 1ኛ ጴጥ. 5፡2***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

ጳውሎስና በርናባስ ከከተማ ወደ ከተማ ስለ ኢየሱስ እየሰበኩ ይጓዙ ነበር፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ደቀ መዛሙርት ግን ከበውት ሳሉ፥ ተነስቶ ወደ ከተማ ገባ፡፡ በነገውም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን ወጣ፡፡ በዚያችም ከተማ ወንጌልን ሰብከው እጅግ ደቀ መዛሙርትን ካደረጉ በኋላ፥ የደቀ መዛሙርትን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና፤ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ፥ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም ወደ አንጾኪያም ተመለሱ፡፡ በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ፥ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው፡፡"***
>
> ሐዋ. 14፡20-23

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሐዋ. 18፡23፤ 1 ተሰ. 5፡13-15፤ ሐዋ. 2፡42-47፤ ሐዋ. 11፡25-30፤ ሐዋ. 15፡30-41)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

**መደምደሚያ -** *ታማኝ የሆንን የክርስቶስ ተከታዮች እንሆን ዘንድ ልንጠነክርና እርስ በራሳችን* ልንበረታታ ይገባል፡፡

# የደቀመዝሙር ቡድንን መምራት

## አምልኮና ጸሎት

- እግዚአብሔር በስብሰባው መሃል እንዲሆን በጸሎትና በአምልኮ ጋብዙት፤
- ምስጋናን ለማቅረብና ለምስክርነት ጊዜ መድቡ።

## የትምህርቱ ግኝትና የማዛመድ ጊዜ

### ደረጃ 1 - የትምህርቱ ጭብጥ

- ከቡድኑ ጋር የትምህርቱን ጭብጥና የቁልፍ ቃሉን ሃሳብ ተከፋፈሉ።

### ደረጃ 2 - የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

- የመግቢያውን ነጥብና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን ሃሳብ ከቡድኑ ጋር ተከፋፈሉ።

### ደረጃ 3 - የግኙት ሂደት

- ታሪኩን እወቁት፣
- ታሪኩን ተረዱት፣
- የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ጨብጡ።

### ደረጃ 4 - ተጨማሪ የቃሉ ጥናት

- ቡድኑ ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንዳገኘ ለማወቅ ተገቢው መጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ተግባራዊ ርምጃ መኖሩን ፈትሹ።

### ደረጃ 5 - ማዛመድና መደምደሚያ

ከታሪኩ በተገኘው ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤና ተግባራዊ ርምጃ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ። (ማስተማር)

- እኔ የተሳሳተ ግንዛቤና የተሳሳተ የድርጊት ርምጃ አለኝን; (ወቀሳ)
- እንዴት አስተሳሰቤንና የድርጊት ርምጃዬን ማስተካከል እችላለሁ; (ራስን ማረም)
- እንዴት ትክክለኛ አስተሳሰብና የድርጊት እርምጃን በቋሚነት በመያዝ መቀጠል እችላለሁ? (ሥልጠና)

## በማኅበረሰቡ ውስጥ መኖር

### በክርስቶስ ማደግ

- የቡድኑ አባላት ባለፈው የደቀመዝሙር ትምህርት ላይ የተማሩትን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ጠይቃቸው።

### ከሌሎች ጋር የተማሩትን እውነት መከፋፈል

- የቡድኑ አባላት ባለፈው የደቀመዝሙር ትምህርት ላይ የተማሩትን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ጠይቃቸው። በቡድኑ ውስጥ በአሁኑ ጥናትና በሚቀጥለው የደቀመዝሙር ጥናት መሃከል የሚነሱ ትምህርቶችን እንዴት ለሌሎች የቡድኑ አባላት እንደሚያካፍሉ ጠይቃቸው።

### ርዳታ የሚፈልጉትን መንከባከብ

- ካለፈው የቡድኑ የአገልግሎት ትምህርት በመነሳት ከማኅበረሰቡ እርዳታ የሚፈልጉትን እንዴት ባለ ምላሽ መርዳት እንደሚችሉ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው፤
- በቡድኑ ውስጥ ማናቸውም ዓይነት አዲስ የሆነ ትኩረት የሚሻ ችግር ወይም ማኅበረሰቡ ግንዛቤ ሊያገኝበት የሚያስፈልግ ጉዳይ ካለ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው፤
- ቡድኑ ትኩረት ለሚሻው ጉዳይ ወይም ችግር እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸው።

# ወደ ፍሬያማነትና መብዛት

## መጠራት

በተፈጥሮ ውስጥ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሲፈጥር “ፍሬያማና” “የመባዛት” ችሎታ ያለው አድርጎ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የፍጥረት አሰራር የሚያመላክተን ሁሉም ሕያው ፍጥረታት “ራሳቸውን መሰል ፍጡር” ለመውለድ እንደተፈጠሩ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውንም ሲፈጥረው ይህ የፍሬያማነትና የመባዛት መርህ አልተለወጠም፡፡ ***“እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው። ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።”*** ዘፍ. 1፡27-28

እኛ ከመጀመሪያውም ፍሬን እንድናፈራና ምድርን እንድንሞላ በእግዚአብሔር ተባርከን የተፈጠርን ነን፡፡ ላለፉት 6000 ዓመታት የሰው ልጅ ይህንን ሕግ በመታዘዝና ምድርን በመሙላት እየተጋ ይገኛል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜም የሰው ልጆች ዳግመኛ በመወለድ የሚገኘውን መንፈሳዊነትና እንደገና የመወለድን አስፈላጊነት እንዲለማመዱ አስተማረ፡፡ ዳግመኛ ካልተወለዱ በስተቀር ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት እንደማይቻልም አስረግጦ ተናገረ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሲመልስም፤ ***“ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።”*** ዮሐ. 3፡5-6

ክርስቶስ ወደ አዲስ ሕይወት ጠርቶናል፡፡ ይህ አዲስ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ እንደገና መወለድ ነው፡፡ ዳግመኛ አዲስ መወለዳችንን በሕዝብ ፊት በውኃ በመጠመቅ እናሳያለን፡፡ ፍሬን እንድናፈራና እንድንበዛ የተሰጠን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በእኛ ዳግመኛ በመንፈስ መወለድ ይከናወናል፡፡ በክርስቶስ ባገኘነው አዲስ ሕይወት ውስጥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለመዋለድ ትዕዛዙና እድሉ ተሰጥቶናል፡፡ ***“ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”***

ማቴ. 28፡18-20

ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት በማምጣት ደቀ መዝሙር ለማድረግና ለማጥመቅ በክርስቶስ ተጠርተናል፡፡ መንፈሳዊ ፍሬን የሚያፈራና በመንፈስ ዳግመኛ በመዋለድ የሚበዛ ሕይወት እንዲኖረን ተጠርተናል፡፡ ፍሬያማ የመሆንና ደቀ መዝሙርን የማብዛት ሥርዓተ ትምህርት ስልት የክርስቶስን ተከታዮች ደቀ መዝሙር ለማድረግ የተዘጋጀ ንድፍና እነርሱንም በማባዛት ውስጥ ወዳለ የመንፈሳዊ ፍሬያማነት ውጤት የሚያመራ ነው፡፡ ***“ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።”*** 1ኛ ጴጥ. 1፡23

ጌታ አምላካችን በአስገራሚ ፍሬያማነትና በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ ውስጥም በመንፈስ ዳግም ውልደት መብዛት በእውነት ይባርካችሁ፡፡ ይህች ምድራችንም ለእግዚአብሔር መንግስት በተወለዱ ሰዎች ተሞልታ ለማየት ያብቃን!

| | |
|---|---|
| | |

EveryHome for Christ


www.iBFAM.org

*Version 2.01*

# አፍራ ብዛ

www.iBFAM.org

ፍሬያማና የምትበዛ ሁን!



# ጠቃሚ እውነት

## ትምህርት 4 ባሪያው

# ፍሬያማና የምትበዛ ሁን

**ተግባራዊ የደቀመዝሙርነት ሞዴል እና ሥርዓተ ትምህርት**

**የማዕዘን ድንጋይ ትምህርት ፡ ከ 1-4 የተዘጋጁ ጠቃሚ ትምህርቶች**

**አሳታሚ ፡** EveryHome for Christ

አድራሻ ፡
Every Home for Christ International
640 Chapel Hills Dr., Colorado Springs, CO 80920 USA
(719)-260-8888
BFAM@ehc.org
www.iBFAM.org

Copyright © 2011 by Every Home for Christ

ይህን የጥናት ማቴሪያል ከዚህ በታች በተገለጸው ደንብ መሠረት እንደገና ማባዛትና ማሰራጨት ይፈቀዳል፡፡

- አዘጋጁ "ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል ነው" በማለት ለደራሲው ተገቢውን ዋጋ በመስጠት፤
- ኤቭሪ ሆም ኢቫንጀሊዝም ይህን ማቴሪያል የትና እንዴት መጠቀም እንደሚገባ የሰጠውን ማሳሰቢያ ጠብቆ በመስራት፤
- ለማባዛት ከሚበዛ ወጪ በስተቀር ለሽያጭ ዓላማ ካልዋለ፡፡

አውዱን ጠብቆ የትርጉምና የማዛመድ ሥራ የሚከተሉትን ነጥቦች እንዲያካትት ይበረታታል፡፡

- ትርጉሙ በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል አስተባባሪነት በኩል ይሠራል፤
- የትርጉምና የጥቅስ አጠቃቀም የባለቤትነት መብት የኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት ለመሆኑ እውቅና ለመስጠት ስምምነት ይደረጋል፤
- ማንኛውም ይዘቱን የተመለከተ ከአውዱ ጋር የሚዛመድ ሥራ በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት መጽደቅ ይኖርበታል፤
- የመጨረሻው በኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የጸደቀው ቅጂ ለአርካይቭና ለሥርጭት ዓላማ ይቀመጣል፡፡ (ይህ ቅጂ በህትመት መልክና በዲጂታል ቅጂም ይቀመጣል)፡፡

| |
|---|
| **የቢኤፍኤም ትምህርቶች፣ በደቀመዝሙርነት የማስተማር ዘዴ ላይ ያተኮሩ ሲሆን እያንዳንዱ ትምህርት ተገቢውን ጠቀሜታ አስገኝቶ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል፡፡ የቢኤፍኤምን የማስተማር ዘዴ የሚያስጨብጥ ሥልጠናን አግኝተህ ካልሆነ ወይንም ደግሞ የቢኤፍኤምን የሥልጠና መመሪያ ካላገኘህ፣ ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የሥልጠናውን ጊዜ እንዲያመቻችልህ እባክህን በአድራሻችን አግኘን፡፡** |

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከ1963 ዓ.ም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የተወሰደ ነው፡፡

አከፋፋይ ፡ ኤቭሪሆም ፎር ክራይስት ኢንተርናሽናል

# ጣሪያው

## አራተኛው የትምህርት ማውጫ


መግቢያ ------------------------------------------------------------------------------ ገጽ 4

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የግኝት ሂደት ------------------------------------------ ገጽ 6


## ትምህርቶች


4.1 **እግዚአብሔር** ---------------------------------------------------------- **ገጽ** 8

አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ

4.2 **ኢየሱስ** ---------------------------------------------------------------- **ገጽ** 9

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው

4.3 **መንፈስ ቅዱስ** ---------------------------------------------------------- **ገጽ** 10

የክርስቶስ ተከታዮች መንፈስ ቅዱስ ያስፈልጋቸዋል

4.4 **ፍቅርና ይቅርታ** -------------------------------------------------------- **ገጽ** 11

ጌታ ኢየሱስ ፍቅርና ይቅርታን ለማሳየት መጣ

4.5 **በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት** ---------------------------- **ገጽ** 12

የእግዚአብሔር የፍጽምና ደረጃ የጎደለብን ደካሞች መሆናችንን መቀበል

4.6 **የእግዚአብሔር መንግሥት** ---------------------------------------------- **ገጽ** 13

በመንፈስ ዳግመኛ መወለድ

4.7 **መጽሐፍ ቅዱስ**---------------------------------------------------------- **ገጽ** 14

ከእግዚአብሔር የተጻፈ እውነት

4.8 **ቤተ ክርስቲያን** -------------------------------------------------------- **ገጽ** 15

የክርስቶስ ተከታዮች በአንድነት ይኖራሉ

4.9 **የዓለም ብርሃን** -------------------------------------------------------- **ገጽ** 16

የክርስቶስን ብርሃን ማንጸባረቅ

4.10 **ዘላዓለማዊነት** -------------------------------------------------------- **ገጽ** 17

ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ወይም ለዘለዓለም በስቃይ መኖር

4.11 **ፍርድ** ---------------------------------------------------------------- **ገጽ** 18

ክርስቶስ ኢየሱስ በዓለም ሁሉ ይፈርዳል፤

4.12 **የጌታ እራት** -------------------------------------------------------- **ገጽ** 19

ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን መሞቱን የማሰብ አስፈላጊነት፤

4.13 **ጥምቀት** ------------------------------------------------------------ **ገጽ** 20

በክርስቶስ ያለንን እምነት በአደባባይ ማወጅ

**የደቀ መዝሙር ቡድኖችን መምራት**------------------------------------------ **ገጽ** 21

# ፍሬያማና የምትበዛ ሁን

## መግቢያ

“የፍሬያማና የምትበዛ ሁን” (አፍራ ብዛ) የትምህርት ኮርሶች የደቀመዛሙርነት የማስተማሪያ ስልትና ሥርዓተ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች ከአንዱ እውነተኛ ሕያው እግዚአብሔር ጋር ልዩ የሆነ ኅብረት እንዳላቸው ለማስገንዘብ የተነደፈ ነው። የአፍራ ብዛ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች ከኢየሱስ ጋር ባላቸው ኅብረት የተትረፈረፈ ሕብረት ሊኖራቸው እንደሚችል ለማሳየት የተነደፈ ኮርስ ነው። ሰዎች እርስ በእርስ ኅብረት እንዲኖራቸው ተፈጥረዋል። ከዚህም በላይ፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው ተፈጥረዋል። የኃጢአት ውጤትም ሰዎች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት እንዲቋረጥ አድርጎአል። የተቋረጠው ይህ ኅብረት እኛ ሰዎች እርስ በእርሳችን ከተቋረጠው ተፈጥሮና ከእግዚአብሔር ጋር ውህደት እንዳይኖረን አድርጎአል።

በዚህም ምክንያት በዓለማችን ላይ ጦርነት፣ ረሃብ፣ ግድያ፣ ተላላፊ በሽታ፣ ሕመም፣ ፍርደ ገምድል መሪዎች፣ ፍትህ አልባ ማኅበረሰብም እንዲኖር ሆኖአል። ከኃጢአት የተነሳ ኅብረታችን ተቋርጧል። ኃጢአትን እንዴት እንደምናስወግድና እንዴትስ በተሃድሶ ኅብረትን መመሥረት እንደምንችል እስካልተረዳን ድረስ፣ መልካሙን ሕይወት ለመኖር ከሚያስችለን ሕይወት ርቀናል።

የምስራቹ ቃል እግዚአብሔር ከኃጢአት የመውጫ ያውን መንገድና፣ የተቋረጠውን ኅብረትም ለማደስ ኃላፊነት እንደወሰደ ያመላክተናል። የአፍራ ብዛ ኮርስ ትኩረትም ይህን ማመልከት ነው። አፍራ ብዛ ሰዎች በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የምሥራቹን ቃል እንዴት እንደሚያነቡና እንደሚገነዘቡ ለማስተማር ይፈልጋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በታማኝነት እውነትን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ቃል ገብቶላቸዋል:: ***“ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል”*** (ማቴ. 7፡7-8)። የአፍራ ብዛ ኮርስ ሰዎች እንዴት እንደሚጠይቁ፣ እንደሚፈልጉና እንደሚያንኳኩ ያስተምራል። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንዴት እንደሚያነቡና እውነትን እንዴት እንደሚፈልጉም ያስተምራል። እውነቱም እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ኃላፊነትን እንዲወስድና ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ማደስ እንደሚፈልግ ያስተምራል።

የእግዚአብሔርን እውነት  በታማኝነት ለሚፈልጉ ሁሉ፣ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እውነት ማግኘት ለሚፈልጉ፣ ለእነርሱ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ እርቅ እንዲሆንላቸው ቃል ኪዳን ተገብቶላቸዋል። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት ሲታረቅ ያን ጊዜ የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራሉ።

ይህ ኮርስ “ፍሬያማና የምትበዛ ሁን” የተባለበት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት የምንኖረው የመጀመሪያ ደረጃ፤ እግዚአብሔር ፍሬያማ ሕይወት እንድንኖር አድርጎ እንደፈጠረን ለማሳወቅ ነው። ፍሬያማው ሕይወት በመንፈሳዊነት ወደ መባዛት ሕይወትም ያመራል።

# የደቀመዛሙርት ቡድኖችን መምራት

በዚህ ጥናት መጨረሻ ላይ የአፍራ ብዛ ትናንሽ ቡድን ሞዴሎች ተካተዋል። ትናንሾቹ የደቀመዝሙር ሞዴሎች ቡድን፣ ትናንሽ የቡድን ስብሰባ በአፍራ ብዛ የደቀመዝሙር ሞዴልና ሥርዓተ ትምህርት በመጠቀም እንዴት እንደምንመራ ያሳየናል።

# ጠቃሚ የሆኑት ተከታታይ ትምህርቶች

በአፍራ ብዛ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የተካተቱት የመጀመሪያዎቹ 52 ተከታታይ የሆኑ ትምህርቶች ተከታታይ ጠቃሚ ትምህርቶች ይባላሉ። እነኚህ ተከታታይ ትምህርቶች በአራት ክፍል ትምህርቶች የተመደቡና እያንዳንዳቸው 13 ትምህርቶችን የያዙ የአንድ ዓመት ጥናቶች ናቸው። እነኚህ ጠቃሚ ተከታታይ ትምህርቶች ልክ ቤትን በመገንባት መልክ የተዋቀሩ ናቸው። አራቱ የተለያዩ ክፍለ ትምህርቶችም የማዕዘን ድንጋይ፣ መሠረት፣ ግድግዳና ጣራን ያካትታሉ። ከዚህ በታች የእነኚህ አራት ትምህርቶች ይዘት ተብራርቷል።



## የማዕዘን ድንጋይ ክፍለ ትምህርት - የማስታረቅ ኅብረት

የማዕዘን ድንጋይ ክፍለ ትምህርቶች በማስታረቅ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። እግዚአብሔር እንዴት ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ከሚያስረዳው ፍጥረተ ትምህርትም ይጀምራል። ይህ እውነትም ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ንጽረተ ዓለም ያስጨብጠናል። ሁለተኛው ትምህርትም የሰው ልጅ ከሌላው ፍጥረት የተለየ ሆኖ እንደተፈጠረ ያስጨብጠናል። እኛ የተፈጠርነው ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ኅብረት እንዲኖረን ነው። ሦስተኛውና አራተኛው ትምህርትም የሰው ልጅ እንዴት በሰይጣን እንደተታለለ ያሳያል። የመጀመሪያው ሰው እግዚአብሔርን አልታዘዘም፤ በዚህም ምክንያት እኛ ሁላችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕብረት ተቋረጠ። የቀረው የትምህርቱ ክፍል እግዚአብሔር ይህን የተቋረጠ ኅብረት እንደገና ለማደስና የሰውን ልጅ ለመዋጀት የዘረጋውን የማስታረቅ ዕቅድ ያሳየናል።



## መሠረት የመጣል ክፍለ ትምህርት - ከክርስቶስ ጋር መዝለቅ

ይህ የትምህርት ክፍል መሠረት ያደረገው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዛት የመፈጸምን አስፈላጊነት ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር ***"ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።"*** (ማቴ. 7:24) መሠረት የመጣል ክፍለ ትምህርት በመታዘዝ የአኗኗር ዘዴ ውስጥ የሚገኘውን ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትን ያሳያል።



## የግድግዳ ክፍለ ትምህርት - የተትረፈረፈ ሕይወት

የአንድ ቤት ግድግዳ ከቤቱ ውጪ ያሉ ሰዎች ሁሉ በግልጽ የሚመለከቱት ነው። የክርስቶስ ተከታዮችም ልክ እንደዚሁ ናቸው። የክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔርን በምድር ላይ የሚወክሉ ናቸው። እነኝህ የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔር ተወካይ እንደመሆናቸው መጠን በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች እግዚአብሔርን በመምሰልና በድርጊታቸውም በመግለጽ የሚያሳዩ መሆን ይገባቸዋል። ይህ ክፍለ ትምህርት በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን ቤተሰቦች አስፈላጊነት ዓላማ ላይ ያተኩራል።




## የጣሪያ ክፍለ ትምህርት - ጠቃሚ እውነት

ይህ የመጨረሻ ክፍለ ትምህርት የክርስትናን እምነት መሠረታዊ እውነት ያካትታል። ጣራው ውጫዊ ወይም አላስፈላጊ የሆነውን ነገር እንድንከላከል ተደርጎ ተነድፎአል። የጣሪያ ክፍለ ትምህርት የሐሰት ትምህርትን ለመከላከል የክርስትናን እምነት መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በማሳየት የሐሰትን ትምህርት የመከላከል ንድፍ ነው።




***"እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።"*** ኤፌ. 2:19-22

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማኘት ሂደት






**የትምህርቱ ጭብጥ** - መሬቱን ማዘጋጀት

የትምህርቱ ጭብጥ ደቀመዝሙር ለሚሆኑት ሰዎች ዘር የሚዘራበትን አዕምሮና ልብን በማሳደግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገኘው እውነት እነርሱን ማዘጋጀት ነው፡፡



**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ** - ዘሩን መዝራት

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በለማው መሬት  ውስጥ የሚዘራው ዘር ሲሆን ከተዘራ በኋላ የእውቀትና የአርነት ፍሬን የሚያፈራ ይሆናል፡፡



**የመገንዘብ ሂደት** - ውኃና ማዳበሪያ

የግንዛቤ ሂደት ጥያቄዎች ዘሩን ውኃ እንደማጠጣትና ማዳበሪያ እንደመጠቀም ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል፣ የታሪኩን እውነት ለመግለጥ ይረዳል፡፡



**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት** - ማጣት / መግረዝ

ተጨማሪ የቃሉ ጥናት በታሪኩ ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚገነባ / አስተምህሮ እንዳይኖርም ይከላከላል፡፡



**የተግባር ጥያቄዎችና መደምደሚያ** -

የተግባር ጥያቄዎችና መደምደሚያው በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ያለውን የአዝመራውን ውጤት ለመሰብሰብና በሕይወታችን ውስጥ የተረዳነውን እውነት እንድንተገብረው ይረዳናል፡፡



# የትምህርቱ ቅደም ተከተል

## ደረጃ 1 - መሬቱን ማዘጋጀት የትምህርቱ ጭብጥ

## ደረጃ 2 - ዘር መዝራት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

## ደረጃ 3 - ውኃና ማዳበሪያ የግኝት ሂደት

### ታሪኩን ማወቅ - መጠየቅ

**ማን ነው? ተግባሩ ምንድን ነው? ታሪኩን በጥልቀት ማወቅ፤**

- በታሪኩ ውስጥ ያሉት ገጸ ባሕርያት እነማን ናቸው?
- የገጸ ባሕርያቱ ድርጊት ምንድን ናቸው?
- በታሪክ ውስጥ ያለው ግልጽ የሆነ ጥልቅ ጉዳይ ምንድን ነው?

### ታሪኩን መረዳት - መፈለግ

**ፍልቅ ስሜት፣ የመነሻ ምክንያትና ምርጫ**

- ገጸ ባሕርያቱ የተሰማቸው ፍልቅ ስሜት ምን ይመስላል;
- ገጸ ባሕርያቱን ለድርጊት ያነሳሳቸው መነሻ ምክንያት ምንድን ነው;
- ገጸ ባሕርያቱ የወሰዱአቸው ልዩ ልዩ ምርጫዎች ምንድን ናቸው?

### የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታን ማግኘት - ማንኳኳት

**ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤና ርምጃ**

- የገጸ ባሕርያቱን ድርጊት፣ ጥልቅ ጉዳይ፣ ፍልቅ ስሜት፣ መነሻ ምክንያትና ምርጫ በጥንቃቄ ስትመለከት ምን ትማራለህ?

## ደረጃ 4 - መግረዝ ተጨማሪ የቃሉ ጥናት

## ደረጃ 5 - መከሩን መሰብሰብ የማዛመድ ጥያቄና መደምደሚያ

***"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።"*** 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17

በታሪክ ውስጥ በተዳሰሰው ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳትና ተግባራዊነት መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ (ማስተማር)

- እኔ የተሳሳተ ግንዛቤና ድርጊት አለኝን; (ተግሳጽ)፤
- የተሳሳተ ግንዛቤዬንና ተግባሬን እንዴት ማስተካከል እችላለሁ (ማቅናት)፤
- እንዴት ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታና ግንዛቤ ጨብጬ መጓዝ እችላለሁ? (ሥልጠና)

# እግዚአብሔር

ትምህርት
4-1

## አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

አንድ እግዚአብሔር አለ። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፣ እንዴት እንደምንረዳውና ምን እንደሚመስል ይነግረናል። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች አንዱን እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳለባቸውና ሌላ ጣዖታትን ማምለክ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ መሆኑን ይነግረናል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥" ማር. 12፡29***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ጳውሎስ ታላላቅ ከሚባሉት የመጀመሪያዎቹ የወንጌል ሰባኪዎች አንዱ ነበር። አንድ ቀን ጳውሎስ ለሕዝቡ ስለ አንዱና እርሱ ብቻ አምላክ ስለሆነው ስለ እግዚአብሔር መልዕክት አቀረበ። የከተማው ሕዝብም ጳውሎስን ለመስማት ተሰበሰቡ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ጳውሎስም በአርዮስፋጎስ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፡- የአቴና ሰዎች ሆይ፥ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ እንደምትፈሩ እመለከታለሁ። የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ ለማይታወቅ አምላክ የሚል ጽሕፈት ያለበትን መሠዊያ ደግሞ አግኝቼአለሁና። እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ። ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤ እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም። ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደ ሆነ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው፤ ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም። ከእናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ፤ እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደ ተናገሩ፥ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን።" ሐዋ. 17፡22-31***

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ዘዳ. 6፡4-5፤ 1 ጢሞ. 2፡5-6፤ ዘፍ. 1፡1፤ ራዕ. 1፡8፤ ማር. 12፡32)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - አንድ እውነተኛ አምላክ አለ፤ ሌላ የተሳሳቱ አምላኮችን እንዳናመልክ መጠንቀቅ አለብን።

ትምህርት 4-2

# ኢየሱስ

## ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት በመንግሥተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ ነው። ከሞተና ከሙታን ከተነሳ በኋላ ኢየሱስ በመንግሥተ ሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ሄዷል። ኢየሱስን እንደሚገባ እንድናመልክና መንገዱንም እንድንረዳ እግዚአብሔር አባትና ኢየሱስ አንድ እንደሆኑ መረዳት ይገባል።

ቁልፍ ጥቅስ -*"በነቢይ ከጌታ ዘንድ፡- እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፡- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው። እንግዲህ የእግዚአብሔር ዘመዶች ከሆንን፥ አምላክ በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም። እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል።" ማቴ. 1፡22-23*

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ከእግዚአብሔር የተላኩና በየዘመናቱ በታሪክ ውስጥ የታዩ በርካታ ሰዎች ኢየሱስ አንድ ቀን እንደሚመጣ ሲያውጁ ነበር። እነዚህ ሰዎች ነብይ ተብለው ይጠሩ ነበር። ሙሴና ኤልያስ ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ ረጅም ዘመን በፊት የነበሩ ነብዮች ናቸው።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> *"ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም፥ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፡- ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ። እርሱም ገና ሲናገር፥ እነሆ፥ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፥ እነሆም፥ ከደመናው፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ። ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው በፊታቸው ወደቁ እጅግም ፈርተው ነበር። ኢየሱስም ቀርቦ ዳሰሳቸውና፡- ተነሡ አትፍሩም አላቸው። ዓይናቸውንም አቅንተው ሲያዩ ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም።" ማቴ. 17፡1-8*

### የግኘት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ዕብ. 1፡1-3፤ ዮሐ. 1፡1-5፤ ቆላ. 1፡15-20፣ ቆላ. 2፡9፤ ፊሊ. 2፡5-11፤ ዮሐ. 3፡16)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ -** ኢየሱስና በሰማይ የሚኖረው አባቱ አንድ ናቸው። ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው።

ትምህርት
4-3

# መንፈስ ቅዱስ

## የክርስቶስ ተከታዮች መንፈስ ቅዱስ ያስፈልጋቸዋል፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አስተማረ። ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ነበረው። መንፈስ ቅዱስ ረዳት ተብሎ የሚጠራና የክርስቶስን ተከታዮች ወደ እውነት የሚመራ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ ተከታዮች ኃይልን ይሰጣል። ለአማኞች ይህ መለኮታዊ ኅብረት ጠቃሚ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።" ዮሐ. 14፡16-17*

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ የሰጠው አንዱ የመጨረሻ ትዕዛዝ የእርሱ ተከታዮች መንፈስ ቅዱስን እንዲጠባበቁ ነበር። ይህን ትዕዛዙን በመስማትም በርካታ ሰዎች ያሉበት አንድ ቡድን በኢየሩሳሌም ተሰባስቦ ነበር። ከጥቂት ቀን በኋላ በእነዚህ በተሰባሰቡ ሰዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ መጣ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> *"በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤ ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ፥ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለ ነበር የሚሉትን አጡ። ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ፡- እነሆ፥ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን? የጳርቴና የሜድ የኢላሜጤም ሰዎች፥ በሁለት ወንዝም መካከል በይሁዳም በቀጰዶቅያም በጳንጦስም በእስያም፥ በፍርግያም በጵንፍልያም በግብፅም በቀሬናም በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች የምንኖር፥ በሮሜም የምንቀመጥ፥ አይሁድም ወደ ይሁዲነትም የገባን፥ የቀርጤስና የዓረብ ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን። ሁሉም ተገረሙና አመንትተው እርስ በርሳቸው፡- እንጃ ይህ ምን ይሆን? አሉ። ሌሎች ግን እያፌዙባቸው፡- ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ። ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ፥ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው። አይሁድ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፥ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሎቼንም አድምጡ። ለእናንተ እንደ መሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፥ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና፤ ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው። እግዚአብሔር ይላል፡- በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ . . ."* ሐዋ. 2፡1-17

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ዮሐ. 16፡13፤ ሐዋ. 1፡8፤ ሉቃ. 11፡13፤ 1 ቆሮ. 12፡7-11፤ ገላ. 5፡16፤ ገላ. 22-23)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - የቀድሞዎቹ የኢየሱስ ተከታዮች በሚኖሩባት ምድር ላይ ተጽዕኖን ማምጣት የቻሉት በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞሉ ነበር። ዛሬ እንደ በፊቶቹ የኢየሱስ ተከታዮች እኛም መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገናል።

# ፍቅርና
# ይቅርታ

ትምህርት 4-4

## ጌታ ኢየሱስ ፍቅርና ይቅርታን ለማሳየት መጣ፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ለሁሉም ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅር ባይነት ያሳይ ነበር። እንደ ክርስቶስ ተከታዮች እኛም የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታ ለሰዎች ሁሉ ልናሳይ ይገባል።

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።" ዮሐ. 15:12***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰበት ዘመን ሕዝቡ ይተዳደር የነበረው በሙሴ ሕግ ነበረ። በዚህ ታሪክ፣ ኢየሱስ ለሕዝቡ በፍቅርና በይቅርታ ላይ የተመሰረተ አዲስ አኗኗርን ያሳያቸው ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። ተቀምጦም ያስተምራቸው ነበር። ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርሱዋን አቁመው፦ መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች። ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት። የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ። ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤ መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ፦ ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው። ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ። እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች። ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ። አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት። እርስዋም፦ ጌታ ሆይ፥ አንድ ስንኳ አለች። ኢየሱስም፦ እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።"*** ዮሐ. 8:2-11

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ዮሐ. 2:8-11፣ 1 ዮሐ. 3:16፣ 1 ዮሐ. 4፤ ዮሐ. 15:12-17)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17 ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ* -** ኢየሱስ ፍጹም የሆነ ፍቅርንና ይቅርታን ያሳየን አምላክ ነው። የኢየሱስ ተከታዮች ከሆንን ፍቅርንና ይቅርታን ለሰዎች ሁሉ ማሳየት አለብን።

# በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት

ትምህርት 4-5

## የእግዚአብሔር የፍጽምና ደረጃ የጎደለን ደካሞች መሆናችንን መቀበል፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

በእግዚአብሔር የፍጽምነት ደረጃ ላይ ለመድረስ ሰው ሁሉ ብቃት ያንሰዋል፡፡ መልካም ነገሮችን በማድረግ ብቻ በራሳችን የተሻልን ሰዎች ሆነን መገኘት አንችልም፡፡ ኃጢያተኛነታችንን በመረዳት የእግዚአብሔርን ምህረት እንዲወርድልን መለመን አለብን፡፡ የእግዚአብሔርን ምህረት ስንጠይቅ በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅን እናገኛለን፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤. . ." ሮሜ. 3:23***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

***የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡***

ኢየሱስ ስለ ሁለት ሰዎች አንድ ታሪክ ተናገረ፡፡ አንደኛው ሰው ፈሪሳዊ እየተባለ የሚጠራ የሃይማኖት መሪ ነው፡፡ ሁለተኛው ሰው ደግሞ በሕዝቡ ዘንድ የተጠላ ቀረጥ ሰብሳቢ ነው፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ለማግኘት፤ እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ሲል እንደሆነ እንረዳለን፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ። ፈሪሳዊም ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ፤ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ። ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን፤ አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር። እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል።" ሉቃ.*** 18:10-14

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሮሜ 3:24፣ ሮሜ 4:4-5፣ ሮሜ 4:25፣ ሮሜ 5:1-2፣ ሮሜ 5:8-10፣ ሮሜ 10:10፣ *ያዕ.* 2:20-26)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3:16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት፡፡

***መደምደሚያ*** - ሁሉም ሰው ኃጢአተኛ ከመሆኑ የተነሳ ጽድቅ ያስፈልገዋል፡፡ ጽድቅ የሚጀምረው ከእግዚአብሔር የጽድቅ ደረጃ ጋር የኛ ጽድቅ ሲነፃፀር በኃጢአት መውደቃችንን በደንብ ተረድተን ከእርሱ ከእግዚብሔር ይቅርታ በመጠየቅ ነው፡፡ ለእኛ ጽድቅን ሊሰጠን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

# የእግዚአብሔር መንግሥት

ትምህርት 4-6

**በመንፈስ ዳግመኛ መወለድ፤**

## የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ አብዛኛውን ጊዜ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ይናገር ነበር። የእግዚአብሔር መንግሥት በእግዚአብሔር አስተዳደር ሥር ያለ ነው። የኢየሱስ ተከታዮች የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ናቸው። ማንም ሰው ዳግም ሳይወለድ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያያት አይችልም።

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።" 2ኛ. ቆሮ. 5፡17***

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኒቆዲሞስ የተባለ አንድ ሰው ኢየሱስን አንድ ጥያቄ ሊጠይቀው ወደ እርሱ መጣ። ኒቆዲሞስ ዋና የሃይማኖት መሪ ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ፡- መምህር ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን አለው። ኢየሱስም መልሶ፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው። ኒቆዲሞስም፡- ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው። ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ። ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።"*** ዮሐ. 3፡1-8

## የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

## ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ጴጥ. 1፡23፤ ሮሜ 6፡4፤ ሐዋ. 1፡3፣ ዮሐ. 18፡36፤ 2 ጢሞ. 4፡18፤ 2 ጴጥ. 1፡1)

## የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17) ገጽ ተመልከት።

**መደምደሚያ -** ኢየሱስ ማንም ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም ብሏል። ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ በውኃና በመንፈስ ዳግመኛ መወለድ እንዳለበት ነግሮታል።

# መጽሐፍ ቅዱስ

ትምህርት 4-7

## ከእግዚአብሔር የተጻፈ እውነት፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

የእግዚአብሔር ቃል ኃያል የሆነ ቅዱስ ቃል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ እውነቶች የኛን ልብና አስተሳሰብ ይቀይራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚና የእግዚአብሔርን ማንነት የሚነግረን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የመጣ ብቸኛው መጽሐፍ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።" 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት በሰይጣን ተፈትኖ ነበር። በዚህ የፈተና ሰዓት ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ ተመስርቶ ፈተናዎችን ተቋቁሟል።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው። አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ። ፈታኝም ቀርቦ፡- የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው። እርሱም መልሶ፡- ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው። ከዚህ በኋላ ዲያቢሎስ ወደ ቅድስት ከተማ ወሰደውና እርሱን በመቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ፡- መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፥ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው። ኢየሱስም፡- ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል አለው። ደግሞ ዲያቢሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፡- ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው። ያን ጊዜ ኢየሱስ፡- ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው። ያን ጊዜ ዲያቢሎስ ተወው፥ እነሆም፥ መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር።"*** ማቴ. 4፡1-11

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሮሜ 10፡17፤ ኤፌ. 6፡13-17፤ 2 ጴጥ. 1፡20-21፤ መዝ. 119፤ ያዕ. 1፡21)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - ኢየሱስ ሰይጣንን በእግዚአብሔር ቃል ሊዋጋው መርጦአል። እኛም እንደ ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ከጠላታችን ለሚወረወርብን ፍላጻ / ጦር መዋጊያ መሣሪያ አድርገን መጠቀምና እምነታችንን የምናሳድግበት መሣሪያ አድርገን መጠቀም አለብን።

ትምህርት
4-8

# ቤተ ክርስቲያን

## የክርስቶስ ተከታዮች በአንድነት ይኖራሉ፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ምድርን በመተው በመንግሥተ ሰማይ ወዳለው ወደ አባቱ ሲሄድ ቤተ ክርስቲያንን በምድር ላይ የሱ ምትክ አድርጎ ነው። እኛም እንደ ኢየሱስ ተከታዮች ከሌሎች አማኞች ጋር በሰላምና በፍቅር በመኖር፣ እርስ በርስም በእምነት መበረታታት አለብን። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት፣ ክርስቶስም የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።" ማቴ. 16፡18***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ በሰማይ ወዳለው አባቱ ከሄደና መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ የአማኞች ቁጥር እጅግ በፍጥነት ያድግ ነበር። ከትንሽ ጊዜ በኋላ አማኞች እየተገናኙ እግዚአብሔርን ያመልኩና የእግዚአብሔርንም ቃል በአንድነት ያጠኑ ነበር። እነኚህ አማኞች እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው እርዳታ በመስጠት ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ችግረኛ ሴቶችም እርዳታ እንክብካቤ ያደርጉ ነበር። የመጀመሪያዋ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችው ከሁለት ቡድኖች ነው። አንደኛው ቡድን የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ ሲሆን የሄለናውያን አይሁድ ቡድን በመባል ይታወቃል። ሌላኛው ደግሞ የዕብራይስጥ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሲሆኑ የዕብራውያን አይሁዶች ተብለው ይጠራሉ። በዚህ ታሪክ ላይ ያሉት የአይሁድ እምነት ተከታይ የሆኑ ካህናቶች ናቸው።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"በዚህም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጐራጐሩባቸው፥ በየቀኑ በተሠራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ችላ ይሉባቸው ነበርና። አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው፤ የእግዚአብሔር ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን። ይህም ቃል ሕዝብን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም ኒቃሮናንም ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ። በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው፥ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው። የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፥ በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቍጥር እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ።"*** ሐዋ. 6፡1-7

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(ሐዋ. 2፡42-47፤ 1 ቆሮ. 12፡12-28፤ ዕብ. 10፡25፤ ኤፌ. 2፡19-21፣ ኤፌ. 4፡14-16)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

***መደምደሚያ*** - መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ከሰው አካል ጋር ያመሳስላታል። በሰው አካል ውስጥ እያንዳንዱ ብልት የራሱ የሆነ ሥራ ያለው ሲሆን እያንዳንዱም ብልት ከሌላው የክርስቶስ ተከታዮች ለተሰጣቸው ኃላፊነቶች ታማኞችና ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ጋርም በመተባበር የሚሰሩ ሊሆኑ ይገባቸዋል።

# የዓለም ብርሃን

ትምህርት 4-9

## የክርስቶስን ብርሃን ማንጸባረቅ፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

እንደ ክርስቶስ ተከታዮች የኛ ሕይወት የክርስቶስን ባሕርይ የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት። አኗኗራችንም በዓለም ላሉ ሰዎች የክርስቶስን ማንነት የሚያሳይ መሆን አለበት።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።" ማቴ. 5፡16***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

የኢየሱስን ትምህርት ለመስማት እጅግ ብዙ የሆኑ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> ***"ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና። እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም። እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል። መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።"*** ማቴ. 5፡11-16

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ዮሐ. 1፡7፤ 1 ዮሐ. 2፡10፤ 2 ቆሮ. 4፡6፤ ማቴ. 5፡7)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - ኢየሱስ ለተከታዮቹ መልካም ስነምግባርና በጎ ተግባርን በመፈጸም እንዴት እንደሚኖሩ አስተምሮአቸው ነበር።

# ዘለዓለማዊነት

ትምህርት 4-10

## ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ወይም ለዘለዓለም በስቃይ መኖር

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ሕይወት ከሞት በኋላ አታበቃም። እኛ ለዘለዓለም መኖርን ትቀጥላለች። ሁሉም ሰው በምድር ላይ በነበረ ዘመን ሳረገው ሥራ ዋጋውን በሰማይ ይቀበላል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***"በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።" ዮሐ. 5፡28-29***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ የሃብታሙና የድሃውን ሰው ምሳሌ በመጠቀም ለእርሱ ተከታዮች ስለ ዘለዓለማዊው ሕይወት አስተማረ።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። አልዓዛር የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር። ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ፡- አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን፡- ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ። እርሱም፡- እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ። አብርሃም ግን፡- ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው። እርሱም፡- አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ። ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።" ሉቃ.*** 16፡19-31

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ተሰ. 4፡13-18፤ ሮሜ 6፡20-23፤ ማቴ. 19፡16-26፤ ማቴ. 25፡45-46)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ *ገጽ 7 ተመልከት*)።

**መደምደሚያ** - ሁላችንም ስለ ሕይወታችን በእግዚአብሔር ፊት ቆመን ዋጋችንን እንቀበላለን። የእኛ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለዓለም መኖር ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ኅብረት የሚወሰን ይሆናል።

ትምህርት
4-11

# ፍርድ

## ክርስቶስ ኢየሱስ በዓለም ሁሉ ይፈርዳል

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ኅብረት ለማደስ ወደ ምድር መጣ። ዳግመኛም ወደ ምድር በመምጣት በሰይጣን ሥራና በክፉ ሰዎች ላይ ፍርዱን በመስጠት የዓለም ፍጻሜ ይሆናል። እርሱን አምላክ አድርገው ያልተቀበሉት ላይም ፍርዱን ይሰጣል። በእምነታቸው የጸኑትን ጻድቅ ሰዎችንም ኢየሱስ ይሸልማቸዋል።

**ቁልፍ ጥቅስ** - *"ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን። ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።" 1ኛ ተሰ. 4፡16-18*

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

በዚህ ታሪክ ላይ ኢየሱስ ወደ ፊት በሰዎች ላይ በፍፃሜ ጊዜ ስለሚኖረው የፍርድ ቀን ይናገራል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤*

> *"አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ። አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና። የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው። በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ። እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።"* ዮሐ. 5፡21-30

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(*ራዕ*. 20፡11-15፤ ማር. 9፡41-48፤ 2 ቆሮ. 5፡10፤ 1 ቆሮ. 3፡11-15)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ በኃጢአተኞች ላይ ፍርድን በመስጠት ለጻድቃን ሽልማትን እንደሚሰጥ ተረድተን፤ ተዘጋጅተን እንድንጠብቀው አስጠንቅቆናል።

# የጌታ እራት

## ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን መሞቱን የማሰብ አስፈላጊነት፤

### የትምህርቱ ጭብጥ - *መሬቱን ማዘጋጀት*

ኢየሱስ ለተከታዮቹ አዘውትረው የጌታ እራት እንዲወስዱ አዟቸው ነበር። ይሄ የኢየሱስን ለሰዎች ኃጢአት ሲል በመስዋዕት መሞቱን የሚያመለክት ሥርዓት ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** - ***እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና፦ ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፦ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።" ሉቃ. 22፡19-20***

### የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል።**

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት የመጨረሻውን የእራት ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አሳልፎ ነበር። በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን እርሱ በመስቀል ላይ መሞቱን ዘወትር እንዲያስታውሱት አሳስቧቸው ነበር።

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

> *"ነገር ግን በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለሚከፋ እንጂ ለሚሻል ስላልሆነ ይህን ትእዛዝ ስሰጥ የማመሰግናችሁ አይደለም። በመጀመሪያ ወደ ማኅበር ስትሰበሰቡ በመካከላችሁ መለያየት እንዳለ እሰማለሁና፥ በአንድ በኩልም አምናለሁ። በእናንተ ዘንድ የተፈተኑት እንዲገለጡ በመካከላችሁ ወገኖች ደግሞ ሊሆኑ ግድ ነውና። እንግዲህ አብራችሁ ስትሰበሰቡ የምትበሉት የጌታ እራት አይደለም፤ በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላልና፥ አንዱም ይራባል አንዱ ግን ይሰክራል። የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁን አንዳችም የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን? ምን ልበላችሁ? በዚህ ነገር ላመስግናችሁን? አላመሰግናችሁም። ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፤ ቆርሶም፦ እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፦ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።"* 1ኛ. ቆሮ. 11፡17-26

### የግኝት ሂደት - *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

### ተጨማሪ የቃሉ ጥናት - *መግረዝ*

(1 ቆሮ. 11፡17-34፤ ሉቃ. 22፡7-38፤ ዮሐ. 6፡47-58፤ ራዕ. 19፡9)

### የማዛመድ ጥያቄዎች - *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)።

**መደምደሚያ** - የጌታ እራት ኢየሱስን የምናወድስበትና የእኛ አኗኗር በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳለውና እንደሌለው የምናይበት ጊዜ ነው። ለክርስቶስ ተከታዮች ይሄ ሰዓት ራሱን ለሁሉ ሰው ሲል አሳልፎ የሰጠውን ኢየሱስን የሚያመልኩበትና የሚያመሰግኑበት ነው።

# ጥምቀት

ትምህርት 4-13

**በክርስቶስ ያለንን እምነት በአደባባይ ማወጅ፤**

**የትምህርቱ ጭብጥ -** *መሬቱን ማዘጋጀት*

የውኃ ጥምቀት ለአዲስ አማኝ ሕይወት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ መጠመቅ ማለት አዳዲስ አማኞች በይፋ በክርስቶስ እንዳመኑ የሚገልጹበትና ውኃ ውስጥ ጠልቀው ሲገቡ ለአሮጌው ሕይወታቸው መሞታቸውን የሚያሳዩበት ተምሳሌት ነው፡፡ ከውኃው ሲወጡ ደግሞ በአዲስ ሕይወት ለክርስቶስ እንደሚኖሩ የሚገልጹበት ተምሳሌት ነው፡፡

**ቁልፍ ጥቅስ -** ***ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡" ሐዋ. 2፡38***

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ** - *ዘሩን መዝራት*

**የታሪኩ መግቢያ ታሪኩን እንድትገነዘብ መረጃን ይሰጥሃል፡፡**

ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ የሚባል የአጎት ልጅ ነበረው፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ለሕዝቡ በውኃ መጠመቃቸው ከኃጢአታቸው ንስሃ መግባታቸው እንደሆነ ይናገር ነበር፡፡ ኢየሱስ ምንም ኃጢአት አልነበረበትም፡፡ ነገር ግን የጥምቀትን ስርዓት ተምሳሌነት አስፈላጊ መሆኑን ለሕዝቡ ለማሳየት ሲል መጠመቅ እንደነበረበት ተገንዝቦ ተጠመቀ፡፡

***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቦአል፤***

***"ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡ ዮሐንስ ግን፡- እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር፡፡ ኢየሱስም መልሶ፡- አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው፡፡ ያን ጊዜ ፈቀደለት፡፡ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፥ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፥ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡"*** ማቴ. 3፡13-17

**የግኝት ሂደት -** *ውኃ ማጠጣትና ማዳበሪያ መጠቀም (ገጽ 7 ተመልከት)*

**ተጨማሪ የቃሉ ጥናት -** *መግረዝ*

(ሮሜ 6፡3-13፤ ማቴ. 28፡16-20፤ ቆላ. 2፡9-12፤ ሐዋ. 8፡26-40)

**የማዛመድ ጥያቄዎች -** *ፍሬውን መሰብሰብ* (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ ገጽ 7 ተመልከት)፡፡

***መደምደሚያ*** **-** አዲስ ኪዳን ለአማኞች ሕይወት የውኃ ጥምቀት አስፈላጊ እንደሆነ ያስተምራል፡፡ የውኃ ጥምቀት ለቀድሞው ሕይወት መሞታችንንና በክርስቶስ ላገኘነው አዲስ ሕይወት መኖራችንን የሚያሳይ ተምሳሌት ነው፡፡

# የደቀመዝሙር ቡድንን መምራት

## አምልኮና ጸሎት

- እግዚአብሔር በስብሰባው መሃል እንዲሆን በጸሎትና በአምልኮ ጋብዙት፤
- ምስጋናን ለማቅረብና ለምስክርነት ጊዜ መድቡ።

## የትምህርቱ ግኝትና የማዛመድ ጊዜ

### ደረጃ 1 - የትምህርቱ ጭብጥ

- ከቡድኑ ጋር የትምህርቱን ጭብጥና የቁልፍ ቃሉን ሃሳብ ተከፋፈሉ።

### ደረጃ 2 - የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

- የመግቢያውን ነጥብና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን ሃሳብ ከቡድኑ ጋር ተከፋፈሉ።

### ደረጃ 3 - የግኝት ሂደት

- ታሪኩን እወቁት፣
- ታሪኩን ተረዱት፣
- የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ጨብጡ።

### ደረጃ 4 - ተጨማሪ የቃሉ ጥናት

- ቡድኑ ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንዳገኘ ለማወቅ ተገቢው መጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ተግባራዊ ርምጃ መኖሩን ፈትሹ።

### ደረጃ 5 - ማዛመድና መደምደሚያ

ከታሪኩ በተገኘው ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤና ተግባራዊ ርምጃ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ። (ማስተማር)

- እኔ የተሳሳተ ግንዛቤና የተሳሳተ የድርጊት ርምጃ አለኝን; (ወቀሳ)
- እንዴት አስተሳሰቤንና የድርጊት ርምጃዬን ማስተካከል እችላለሁ; (ራስን ማረም)
- እንዴት ትክክለኛ አስተሳሰብና የድርጊት እርምጃን በቋሚነት በመያዝ መቀጠል እችላለሁ? (ሥልጠና)

## በማኅበረሰቡ ውስጥ መኖር

### በክርስቶስ ማደግ

- የቡድኑ አባላት ባለፈው የደቀመዝሙር ትምህርት ላይ የተማሩትን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ጠይቋቸው።

### ከሌሎች ጋር የተማሩትን እውነት መከፋፈል

- የቡድኑ አባላት ባለፈው የደቀመዝሙር ትምህርት ላይ የተማሩትን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ጠይቋቸው። በቡድኑ ውስጥ በአሁኑ ጥናትና በሚቀጥለው የደቀመዝሙር ጥናት መሃከል የሚነሱ ትምህርቶችን እንዴት ለሌሎች የቡድኑ አባላት እንደሚያካፍሉ ጠይቋቸው።

### ርዳታ የሚፈልጉትን መንከባከብ

- ካለፈው የቡድኑ የአገልግሎት ትምህርት በመነሳት ከማኅበረሰቡ እርዳታ የሚፈልጉትን እንዴት ባለ ምላሽ መርዳት እንደሚችሉ የቡድኑን አባላት ጠይቋቸው፤
- በቡድኑ ውስጥ ማናቸውም ዓይነት አዲስ የሆነ ትኩረት የሚሻ ችግር ወይም ማኅበረሰቡ ግንዛቤ ሊያገኝበት የሚያስፈልግ ጉዳይ ካለ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቋቸው፤
- ቡድኑ ትኩረት ለሚሻው ጉዳይ ወይም ችግር እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቋቸው።

# ወደ ፍሬያማነትና መብዛት

## መጠራት

በተፈጥሮ ውስጥ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሲፈጥር “ፍሬያማና” “የመባዛት” ችሎታ ያለው አድርጎ እንደሆነ እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊው የፍጥረት አሰራር የሚያመላክተን ሁሉም ሕያው ፍጥረታት “ራሳቸውን መሰል ፍጡር” ለመውለድ እንደተፈጠሩ ነው። እግዚአብሔር ሰውንም ሲፈጥረው ይህ የፍሬያማነትና የመባዛት መርህ አልተለወጠም። ***“እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው። ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።”*** ዘፍ. 1፡27-28

እኛ ከመጀመሪያውም ፍሬን እንድናፈራና ምድርን እንድንሞላ በእግዚአብሔር ተባርከን የተፈጠርን ነን። ላለፉት 6000 ዓመታት የሰው ልጅ ይህንን ሕግ በመታዘዝና ምድርን በመሙላት እየተጋ ይገኛል። ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜም የሰው ልጆች ዳግመኛ በመወለድ የሚገኘውን መንፈሳዊነትና እንደገና የመወለድን አስፈላጊነት እንዲለማመዱ አስተማረ። ዳግመኛ ካልተወለዱ በስተቀር ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት እንደማይቻልም አስረግጦ ተናገረ። ጌታ ኢየሱስ ሲመልስም፤ ***“ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።”*** ዮሐ. 3፡5-6

ክርስቶስ ወደ አዲስ ሕይወት ጠርቶናል። ይህ አዲስ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ እንደገና መወለድ ነው። ዳግመኛ አዲስ መወለዳችንን በሕዝብ ፊት በውኃ በመጠመቅ እናሳያለን። ፍሬን እንድናፈራና እንድንበዛ የተሰጠን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በእኛ ዳግመኛ በመንፈስ መወለድ ይከናወናል። በክርስቶስ ባገኘነው አዲስ ሕይወት ውስጥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለመዋለድ ትዕዛዙና እድሉ ተሰጥቶናል። ***“ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”***

ማቴ. 28፡18-20

ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት በማምጣት ደቀ መዝሙር ለማድረግና ለማጥመቅ በክርስቶስ ተጠርተናል። መንፈሳዊ ፍሬን የሚያፈራና በመንፈስ ዳግመኛ በመዋለድ የሚበዛ ሕይወት እንዲኖረን ተጠርተናል። ፍሬያማ የመሆንና ደቀ መዝሙርን የማብዛት ሥርዓተ ትምህርት ስልት የክርስቶስን ተከታዮች ደቀ መዝሙር ለማድረግ የተዘጋጀ ንድፍና እነርሱንም በማባዛት ውስጥ ወዳለ የመንፈሳዊ ፍሬያማነት ውጤት የሚያመራ ነው። ***“ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።”*** 1ኛ ጴጥ. 1፡23

ጌታ አምላካችን በአስገራሚ ፍሬያማነትና በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ ውስጥም በመንፈስ ዳግም ውልደት መብዛት በእውነት ይባርካችሁ። ይህች ምድራችንም ለእግዚአብሔር መንግስት በተወለዱ ሰዎች ተሞልታ ለማየት ያብቃን!

| | |
|---|---|
| | |